የተሰረቀው ስልክ
እና መዘዙ
ገጽ 10

ለሠላም ተገቢውን ዋጋ
በመስጠት ከግጭት
እንውጣ!
ገጽ 15

ነገን -
በጭላንጭል
ገጽ 16



# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 357 ነሐሴ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ያለው የጽንፈኞች እንቅስቃሴ ስጋት ወደማይሆንበት ደረጃ ላይ ደርሷል”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ያለው የፅንፈኞች እንቅስቃሴ ስጋት ወደማይሆንበት ደረጃ ላይ መድረሱን ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ከመከላከያ ሚዲያ ጋር በነበራቸው ቆይታ ስለሀገሪቱ የፀጥታ ሁኔታ በተለይም በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች አሁን ላይ ስጋት ወደማይሆኑበት ደረጃ መድረሳቸውን ተናግረዋል፡፡

የመከላከያ ሠራዊቱ ጥበብ በታከለበት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ተከስተው የነበሩ የፀጥታ ችግሮችን እየቀረፈ መሆኑን የገለጹት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ በአማራ ክልል የሕዝቡን የመብት ጥያቄ ካባ በማድረግ ፍላጎቱን በኃይል ለማሳካት የተንቀሳቀሰው ኃይል ላይ እየተወሰደ ባለው እርምጃ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል ብለዋል።

የተከበረውን የፋኖ ስም መጠቀሚያ በማድረግ የክልሉን ፀጥታ ሲያውኩ የነበሩ ኃይሎችን በተመለከተም ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ፋኖ ከጥንት ጀምሮ ሀገር ተወረረች ሲባል ጦርና ጋሻ ይዞ ለኢትዮጵያ ነፃነት የሚሰለፍ እንጂ መልሶ የሀገሩ ሠራዊት ላይ ጦር የሚመዝ አይደለም ብለዋል።

አሁን ላይ በፋኖ ስም እየተንቀሳቀሰ ያለው ኃይል በዘረፋ ተግባር ላይ የተሰማራና መንገዶችን በመዝጋት የሕዝቡን ሰላም የሚያወክ ነው ብለዋል።

ሕዝቡን ሰላም ሲነሳ የነበረው ኃይልም የሠራው የሀሰት ፕሮፖጋንዳ መልሶ እርቃኑን እንዲቀር እንዳደረገውና ይህን ኃይልም የመከላከያ ሠራዊቱ እግር በእግር

“በአማራና በኦሮሚያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

















ፎቶ እዮብ ተፈራ

ቃሊቲ ቂሊንጦ ድልድይ

## በመዲናዋ በሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ስድስት ተሻጋሪ ድልድዮች እየተገነቡ ነው

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ስድስት ተሻጋሪ ድልድዮች እየተገነቡ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ እንደገለጹት፤በአዲስአበባ የመንገድ መጋጠሚያዎች ላይ የትራፊክ መጨናነቅ የሚታይባቸው በመሆኑ ከሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር

በመዲናዋ በሁስት ነጥብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለዘመን መለወጫ በዓል የአቅርቦት ችግር እንዳይገጥም በቂ ዝግጅት ተደርጓል

- ለኅብረት ሥራ ዩኒየኖች 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ብድር ተዘጋጅቷል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ለዘመን መለወጫ በዓል የአቅርቦት ችግር እንዳይገጥም በቂ ዝግጅት መደረጉን ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ገለጹ፡፡ ለበዓሉ ለኅብረት ሥራ ዩኒየኖች በኦሮሚያ ክልል 6ነጥብ፤ ቢሊዮን ብር ብድር መዘጋጀቱ ተጠቁሟል፡፡

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በጋራ ለዘመን መለወጫ በዓል የአቅርቦት ችግር እንዳይገጥምና አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪ እንዳይከሰት በተደረጉ ዝግጅቶች ላይ ትናንት

ለዘመን መለወጫ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በ2015/16 የመኸር ወቅት 573 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

- እስካሁን ከ15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

ገጽ4










ተማሪ አርሴማ ንብረቱ



ተማሪ እዮስያስ ነብዩ



ተማሪ ሄርሞን ጌታቸው



ናትናኤል ነብዩ፤

# ክረምትና የተማሪዎች ውሎ

**አመለወርቅ ከበደ**

የበጋው ወቅት አልፎ ክረምት ሲመጣ ተማሪና መደበኛ ትምህርት ይለያያሉ፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ ጊዜአቸውን በተለያዩ አልባሌ ስፍራ የሚያሳልፉ ተማሪዎች የመኖራቸውን ያህል ብልጦች ለመጪው ጊዜ ይዘጋጁበታል፤ ነገን ዛሬ ላይ ይሠሩበታል፡፡ አንዳንዶች የመጪውን የትምህርት ዘመን ከወዲሁ በማጥናት ሲያሳልፉ በልዩ ልዩ የመዝናኛ እና የበጎ ሥራ ተግባራት ላይ የሚያሳልፉ ተማሪዎችም በርካታ ናቸው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ4ኛ ዓመት የኤሌክትሪካል ምህንድስናና የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪ ሄርሞን ጌታቸው የክረምት ጊዜአቸውን ለበጎ ሥራ ከሰጡ ተማሪዎች አንዱ ነው፡፡ ተማሪ ሄርሞን፣ የክረምት ጊዜውን ያሳለፈው በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀጣዩ ዓመት የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎችን በማስጠናት እና የፈተና ጥያቄዎችን በማሠራት ነው ያሳለፈው፡፡

ከማስተማር ውጪ ያለውን ሰዓት የተለያዩ ምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት በበይነ መረብ አማካኝነት የሚሰጡ ትምህርቶችን በመከታተልም ያሳልፋል፡፡

ሌሎች ተማሪዎችም የክረምት ወቅቱን በእንደዚህ ዓይነት በጎ ተግባራት ላይ ቢያውሉ ተማሪዎችን ከመደገፍ በተጨማሪ ለራሳቸውም የአዕምሮ እርካታ እንዲያገኙ እና ከሰዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንዲሰፋ ይረዳል ሲል ምክሩን ይለግሳል፡፡

በካራአሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ12 ክፍል ተማሪው አርሴማ ንብረቱ በበኩሏ፤ የክረምት ወቅቱን በ2016 ዓ.ም የብሔራዊ ፈተና ተፈታኝ እንደመሆኔ ትምህርቶችን በመከታተል፣ የፈተና ጥያቄዎችን በመሥራት እና ቤተሰብ በመርዳት አሳልፋለሁ ስትል ገልጻለች፡፡

ተማሪ አርሴማ እንደምትለው፤ተማሪዎች በክረምት ወቅት ከትምህርት ስለሚርቁ የመዘናጋት ነገር ይኖራል፤ ስለዚህ በክረምት ጊዜ ቢያጠኑ እና የክረምት ትምህርቶችን ቢከታተሉ ለቀጣይ የትምህርት ዘመናቸው ይረዳቸዋል፡፡

በተጨማሪም ተማሪ አርሴማ እና ወደ 30 የሚጠጉ ጓደኞቿ በማህበር በመሆን የክረምት ወቅቱን በሁለት ሳምንት አንዴ መቂዶኒያ ሄደው አረጋውያንን በመንከባከብ ግዜያቸውን በበጎ ተግባር ያሳልፋሉ፡፡

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ናትናኤል ነብዩ፤ የክረምት ወቅቱን በፕሮጀክት በመታቀፍ እግር ኳስ በመጫወት እንደሚያሳልፍ ጠቅሶ፤ የቋንቋ ክህሎቱን ለማሳደግ የቋንቋ ትምህርት እንደሚከታተልም አስረድቷል፡፡ በተጨማሪም የኮምፒውተር ሥልጠና በመውሰድ፤ ቤተሰብ በመርዳት እንደሚያሳልፍ አስረድቷል፡፡

በመካነ ኢየሱስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ሳይኒ ረሙዲን በበኩሉ፤ የክረምቱን ወቅት ስፖርት በመሥራት እና ቤተሰብ በመርዳት አሳልፋለሁ ሲል ገልጿል፡፡

የሰባተኛ ክፍል ተማሪ እዮስያስ ነብዩ ፤ የክረምት ጊዜውን እግር ኳስ በመጫወት እና የቋንቋ ትምህርት በመማር እያሳለፍኩ ነው ሲል ተናግሯል፡፡

ሌሎች ተማሪዎች የክረምቱን ወቅት ጤናቸውን ከመጠበቅ በተጨማሪ፤ ወደፊት ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ ስለሚረዳቸው ስፖርት በመሥራት እና ትምህርታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ቢያሳልፉ የተሻለ ነው ሲል መልእክቱን አስተላልፏል፡፡

የተማሪ ወላጅ የሆኑት ወይዘሮ ፀሐይ ዘርጋው ልጆች በክረምት ወቅት እቤት ሲሆኑ ጊዜያቸውን ባልባሌ ቦታ እንዳያጠፉ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እንዲሠሩ እና የተለያዩ ትምህርቶችን እንዲከታተሉ ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርጉላቸው ገልጸዋል፡፡

በክረምት ወቅት ልጆች ያለምንም ሥራ እና ትምህርት ሲቀመጡ ወዳልተገባ ነገር ስለሚሄዱ የቋንቋ ትምህርቶችን እንዲወስዱ፣ ከወላጆቻቸው ጋር ጊዜ እንዲያሳልፉ እና ለቀጣይ ትምህርታቸው የሚያግዟቸውን መጽሐፍት በመግዛት ክረምቱን በንባብ እንዲያሳልፉ እና መንፈሳዊ ትምህርቶችን እንዲከታተሉ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

ወላጆች ተማሪዎች በክረምት ወቅት እቤት ሲሆኑ እንዳይቦዝኑ የተለያዩ ትምህርቶችን እንዲማሩ ሥራም እንዲለምዱ ሥራ በማዘዝ አብረው ቢያሳልፉ፣ ቢመክሯቸው ልጆች ትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ ይረዳቸዋል ሲሉ ከተሞክሯቸው ተነስተው ይናገራሉ፡፡

ልጆች በክረምት ወቅት እንዲያጠኑ አስፈላጊውን መጽሐፍት በመግዛት ከጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው ወዳጅነት ጥሩ እንዲሆን እንደሚመክሯቸው እና ሌሎች ድጋፎችን እንደሚያደርጉላቸው የተማሪ ወላጅ ወይዘሮ ደስታ ፀሐይ ተናግረዋል፡፡

ልጆች ከወላጆች ጋር በተቀራረቡ ቁጥር የወላጆችን ምክር ስለሚሰሙ ወላጆች ከልጆች ጋር ጊዜ ቢያሳልፉ የተሻለ ነው፡፡ በተጨማሪም ከማብላትና ከማጠጣት ባለፈ ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራቸው ለማድረግ ጤናማ በሆነ መልኩ መከታተል ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

# ቴክኒክና ሙያን ምርጫቸው ያደረጉት ውጤታማ ተማሪዎች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ዓለም ወደ ቴክኖሎጂው በፍጥነት እየገሰገሰች ባለችበት በዚህ ወቅት ኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ብቁ ዜጋ ለማፍራት በተግባር የተደገፉ ሙያዊ ሥልጠናዎችን የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ማጎልበት ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።

ያደጉ ሀገራት አሁን ለደረሱበት ደረጃ ለዜጎቻቸው ተግባር ተኮር ሥልጠናዎች መስጠታቸው እንደሆነ ይነገራል።

ዕውነታው ይህ ቢሆንም በሀገራችን ለቴክኒክና ሙያ የሚሰጠው ግምት አነስተኛ በመሆኑ በመደበኛ መልኩ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት አምጥተው ምርጫቸውን ግን ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚያደርጉ ተማሪዎች ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ላይ ያለው የተሳሳተ ግምት እየተቀየረ ለመምጣቱ ማሳያ የሆኑ ወጣቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ አምጥተው ወደቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎች ደግሞ ለዚህ ዋነኛ ምሳሌዎች ናቸው።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ለመጀመሪያ ጊዜ በመደበኛ መልኩ በ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አምጥተው በተቋሙ ሲሰለጥኑ የነበሩ 512 ሠልጣኞች ነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓ.ም አስመርቋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በመደበኛ መልኩ ገብተው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩትን ጨምሮ በአጠቃላይ



ዮናስ አምሳሉ

ሦስት ሺህ 651 ሠልጣኞችን በመጀመሪያና በድህረ ምረቃ ዘርፎች ነው ያስመረቀው፡፡

ከተመራቂዎች መካከል ሁለት ሺህ 786 በመጀመሪያ ዲግሪ፣ 865 በሁለተኛ ዲግሪ ሲሆን፤ ከነዚህም በመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቁት ተማሪዎች መካከል ዮናስ አምሳሉና ጽዮን ግዛቸው የኢንስቲትዩቱ የማዕረግ ተመራቂዎች ናቸው፡፡

ከኤሌክትሪካል አውቶሜሽንና ኮንትሮል የትምህርት



ጽዮን ግዛቸው

ዘርፍ ከአጠቃላይ ተመራቂዎች መካከል ሦስት ነጥብ 98 በማምጣት የዋንጫ ተሸላሚ የሆነው ዮናስ አምሳሉ 12ኛ ክፍልን ሲያጠናቅቅ ባገኘው ነጥብ ውጤት ዩኒቨርሲቲ ተመድቦ እንደነበር ያስታውሳል።

ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲ ከመግባት ይልቅ ተግባር ተኮር ትምህርት ለመማር በነበረው ፍላጎት የተነሳ ወደቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት እንደተቀላቀለ ይናገራል፡፡

ሀገራችን አሁን ላይ ከቴክኖሎጂው ጋር ወዳጅ የሆነና ሙያ ያለው ምሩቅ የምትፈልግበት ወቅት ነው የሚለው ዮናስ፤ ዩኒቨርሲቲውን ትቶ ቴክኒክና ሙያ ላይ በኤሌክትሪካል አውቶሜሽንና ኮንትሮል የተሻለ ልምድ አገኛለሁ ብሎ በመማሩ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ እንዳላሳደረበት ይገልጻል።

አዲስ ነገር ለመፍጠርም ሆነ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ብቁ ዜጋ ለማፍራት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ወሳኝ ናቸው፤ አሁን ላይ ብቁ ሙያተኛ የሚያደርገኝን በቂ የልምምድና የትምህርት ዕውቀት በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ ይላል፡፡

ብቁና የተሻለ ሥራ ለማከናወን በጽንሰ ሃሳብ ብቻ መማር በቂ ባለመሆኑ ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ለማግኘት የቴክኒክና ሙያ በሮችን ቢያንኳኩ ተጠቃሚ ይሆናሉ ሲል ይናገራል።

በኢንስቲትዩቱ ከመጀመሪያ ዲግሪ ሴት ተመራቂዎች መካከል በቴክስታይልና ማሽን ዲዛይን ኮሌጅ ሦስት ነጥብ 78 በማግኘት የዋንጫ ተሸላሚ የሆነችው ጽዮን ግዛቸው በበኩሏ፤ በሀገራችን ለቴክኒክና ሙያ በተለመደ መልኩ የሚሰጠው አመለካከት የተሳሳተ ቢሆንም ለሙያው ካለኝ ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ዘርፉን ልቀላቀል ችያለሁ ብላለች።

ከተመደበችበት ዩኒቨርሲቲ ቀርታ የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩቱን በመቀላቀሏ በመረጠችው ዘርፍ በቂ ክህሎት ማግኘቷንና የራሷን ሥራ ለመጀመር የሚያስችላትን እውቀት ማግኘቷን ትናገራለች።

በቀጣይም በተማረችበት ዘርፍ ጠንክራ በመሥራት ለሌሎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ እንዳላት ነው ተመራቂዋ ያስረዳችው።

# በመዲናዋ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሰዎች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተሳተፉ ነው

## - ከ628 ሺህ በላይ ሰዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ እስካሁን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የኅብረተሰብ ክፍሎች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተሳተፉ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

ስድስት መቶ 28 ሺህ 597 ሰዎች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ አገልግሎቱ በገንዘብ ሲተመን ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ነው ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፍቃድ ግንዛቤ ማስረፅ ቡድን መሪ አቶ ቢንያም ግቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በተያዘው ክረምት ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የኅብረተሰብ ክፍሎች በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተሳተፉ ነው፡፡

በከተማ አስተዳደሩ በአጠቃላይ በአገልግሎት ዘርፎች እስካሁን ድረስ 628 ሺህ 597 ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ በማዕድ ማጋራት መርሀ-ግብር ከ147 ሺህ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

አቶ ቢንያም አክለውም በ145 ትምህርት ቤቶች አንድ ሺህ 780 የሚደርሱ በጎ ፈቃደኞች በማሳተፍ ለ50 ሺህ 972 ለሚደርሱ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት እንደተቻለ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ቢንያም ገለጻ፤ ከነዚህም በተጨማሪ አንድ ቤተሰብ ለአንድ ሰው መርሀ-ግብር፣አንድ ቤተሰብ ለአንድ ሕፃን፣ የቤት እድሳት፣ በትምህርትና ሥልጠና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ለአዲሱ ትውልድ የሕይወት ተሞክሮ ከመስጠት ረገድ፣ መሠረታዊ የኮምፒውተር ሥልጠናዎች፣ የአፋን ኦሮሞና ግዕዝ ቋንቋዎች ሥልጠና፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በከተማ ግብርና፣ ከተማ ጽዳትና ውብት፣ በጎርፍ ስጋት መከላከል እንዲሁም ደም ልገሳ በክረምቱ በጎ ፈቃድ እየተሠሩ ነው፡፡

በተጨማሪም በጎነት በሆስፒታል መርሀ- ግብር በሆስፒታሎች ላይ በጎ ፈቃደኞችን በማሳተፍ አገልግሎቱ እንዲሳለጥ ተደርጎ አቅጣጫን ማመላከትና አስታማሚ የሌላቸውን የማስታመም ሥራዎች ላይ 1970 በጎ ፈቃደኞች እንደተሳተፉም ጠቁመዋል፡፡

ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲሁም የግልና የመንግሥት የሕክምና ተቋማትን በማሳተፍ በተደረገ የሰባት ቀን የነጻ ሕክምና በከተማው 57 ሺህ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ ቢንያም፤ የመንገድ ትራፊክ መርሀ- ግብር ላይ 5 ሺህ በጎ ፈቃደኞችን በማሳተፍ በ130 አደባባዮች ላይ በማሰማራት የትራፊክ አደጋዎች ለመከላከል ሥራዎች እንደተሠሩ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ቢንያም ገለጻ፤ ከአካባቢ ሰላም ከማስጠበቅ አኳያ 218 ሺህ በጎ ፈቃደኞች ተሳትፈዋል፤ ሙያዬ ለሀገሬ በሚል ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ በጎ ፈቃደኞችን በማሰማራትም ሙያዊ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

# ኮሚሽኑ የሚዲያ አየር ሰዓት ይዞ ሕዝቡ ሃሳቡን በሚገባ እንዲረዳ መሥራት አለበት

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽኑ የሚዲያ አየር ሰዓት ኖሮት ሕዝቡ ሃሳቡን በሚገባ እንዲረዳ መሥራት እንዳለበት በ33ኛው የጉሚ በለል ውይይት መድረክ ላይ መነሻ ሃሳብ ያቀረቡት ዶክተር ሮባ ጴጥሮስ ገለጹ፡፡

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት አዘጋጅነት የሚካሄደው የጉሚ በለል 33ኛው የውይይት መድረክ በትናንትናው እለት "ሀገራዊ ምክክር፤ ዕድሎችና ስጋቶች" በሚል መሪ ሃሳብ ተካሂዷል።

በመድረኩም የሕግ መምህር የሆኑት ዶክተር ሮባ ጴጥሮስ ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጽሑፍ ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሚዲያ አየር ሰዓት ኖሮት ሕዝቡ ሃሳቡን በሚገባ እንዲረዳ መሥራት አለበት፤ ይሄንንም ከሩዋንዳ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡

ኮሚሽኑ በየክልሉ አጀንዳ የሚመርጡና ሕዝብ የሚያወያዩትን መርጦ ወደሥራ መግባቱ መልካም ጅማሮ ቢሆንም፤ ሃሳቡን ሕዝብ እንዲገዛው ወደ ሕዝቡ ማውረድ ላይ ክፍተት እየታየ ነው ያሉት ዶክተር ሮባ፤ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ በሂደቱ ስኬታማ ከሆኑ ሀገራት ልምድ በመውሰድ አወያዮቹ ከተጽዕኖ ውጪ ሆነው ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሮባ ገለጻ፤ ያልተመለሱ በርካታ ጥያቄዎች በመኖራቸው ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠትና ለሀገር ግንባታ መነጋገር እንጂ ማበድ አያስፈልግም፤ ከትርክትና ታሪክ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት በአፈሙዝ ሳይሆን በአፍ ቁጭ ብሎ መነጋገር ያስፈልጋል፡፡

መንግሥት ለብሔራዊ ምክክሩ ለኮሚሽኑ ድጋፍ ማድረግ፣ ሕግ የማውጣትና የማስከበር ኃላፊነቱ የተጠበቀ ሆኖ ከማንኛውም አካል ጋር የመወያየት እንጂ በኮሚሽኑ ሥራ ላይ ጣልቃ መግባት የለበትም ነው ያሉት፡፡

የተዛነፈው የቀድሞ ታሪክና ትርክት አለመስተካከሉ የሀገር ግንባታ ፕሮጀክቶች ሳይጠናቀቁ በእንጥልጥል መቅረታቸው ዜጎችን እየጎዳ ይገኛል ያሉት ጽሑፍ አቅራቢው፤ ወደ ጽንፈኝነት የሚያመራና የትናንትናው የፖለቲካ ስጋት አድሮበት ራሱን በገዛ ፈቃዱ የሚያገል ኃይል ለምክክሩ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል አንስተዋል።

እነኝህ ስጋቶች ተደምረው ሕዝብ በሃሳቡ በሚገባ ካልተገዛ ምክክሩ በተወሰኑ አካላት አጀንዳ ብቻ እንዳይመራ መንግሥት የሕግ የበላይነት ማስከበርና ኮሚሽኑ ሃሳቡን በመሸጥ ስጋቱን መቅረፍ አለበት ነው ያሉት።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የክልሉ የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ፤ ተቀራርቦ መነጋገር ባለመቻሉ በሀገሪቱ ችግሮች እንዲበራከቱ


ዶክተር ሮባ ጴጥሮስ

ምክንያት ሆኗል፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን እየፈተኑ የሚገኙ ችግሮች መንስኤዎቻቸው "እኔ ብቻ" ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኃይሉ ገለጻ፤ እንደ ኢትዮጵያ ተመሳሳይ ችግር የተስተዋለባቸው ሀገራት በምክክር ሀገራዊ መግባባት ላይ ደርሰው የፖለቲካ ችግሮቻቸውን መፍታት ችለዋል፤ በተለያዩ ጎራዎች መካከል የሚደረጉ ሀገራዊ ውይይቶች ባለመነጋገርና ባለመግባባት ምክንያት ለሚፈጠሩ የፖለቲካ ግጭቶች ዕልባት የሚሰጡ የመግባቢያ ድልድዮች ናቸው።

ሀገራዊ ምክክሩ ግጭቶችን በፖለቲካዊ ሂደትና ውይይት በመፍታት የፖለቲካ ሽግግርን ዕውን ለማድረግ አስቻይ ሁኔታን እንደሚፈጥርና ለዚህም የምሁራን ድርሻ የጎላ መሆኑን ያነሱት ኃላፊው፤ ሕዝቡም በመድረኩ ተሳትፎ የሚጠበቅበትን እንዲወጣና በሀገር ግንባታ የበኩሉን አሻራ እንዲያሳርፍ ጠይቀዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ በግንዛቤ ማነስ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶችንና የፖለቲካ ቀውስን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ገልጸው፤ የሃሳብ ልዩነት እንደችግር በሚታይበት፣ ለረጅም ዓመታት እየተንከባለለ የመጣ የፖለቲካ ችግርና የእኔ ይበልጣል የሚል የፖለቲካ እሳቤ ባለባት ሀገር ሀገራዊ ምክክር አስፈላጊ መሆኑን አቶ ኃይሉ ተናግረዋል፡፡

የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው፤ የሀገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ፤የጋራ መግባባትን ማምጣት፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን በሚገባ መጠቀምና ስር እየሰደደ የመጣውን የእኔ ይበልጣል አስተሳሰብ ማስወገድ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳን ጨምሮ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ምሁራን፣ ፖለቲከኞችና ባድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

# ክልሉ በ2016 ከ11 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ለማስተማር ምዝገባ እያካሄደ ነው

## - ከሚያስፈልገው 27 ሚሊዮን መጽሐፍት ማሰራጨት የተቻለው 11 ሚሊዮን ብቻ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 የትምህርት ዘመን ከ11 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ምዝገባ እየተከናወነ መሆኑን የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ አንድ ለሁለት የመጽሐፍ ጥምርታን ለማዳረስ ከታቀደው 27 ሚሊዮን መጽሐፍት እስካሁን ማሰራጨት የተቻለው 11 ሚሊዮን ብቻ ነው፡፡ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ተማሪዎችን የምገባ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለማድረግም እየተሠራ ነው፡፡

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የ2016 የትምህርት ዘመን የኮቪድ-19 ካለፈ በኋላ የትምህርት ካሌንደሩ ተስተካክሎ ትምህርት የሚጀመርበት ዓመት ነው፡፡

በክልሉ ትምህርትን ጥራት ባለው መልኩ ተደራሽ ለማድረግ ባለፉት ወራት በሀገር አቀፍ ደረጃ በተጀመረው የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ሥራ የሦስት ሺ 410 ትምህርት ቤቶችን መሠረተ ልማት በማሟላት ደረጃቸውን የማሻሻል ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ቶላ ገለጻ፤ የ2016 ትምህርት ዘመን ቅድመ ዝግጅት ቀደም ብሎ ተጀምሯል፡፡ መምህራን ወደየተመደቡበት ትምህርት ቤት በመሄድ ተማሪዎችን እየመዘገቡ ነው፡፡ ምዝገባው ከባለፈው ነሐሴ 23 ጀምሮ እስከ ጳጉሜን አምስት ድረስ የሚከናወን ሲሆን፤ ምዝገባ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎቹ በብዛት በየትምህርት ቤቶች እየተመዘገቡ ነው፡፡

በክልሉ በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለማድረግ ከክልሉ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን የመማሪያ ቁሳቁስ በማሰባሰብ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በተከናወነው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማሩ ዝግጁ ሆነዋል ብለዋል፡፡

በክልሉ ባለፈው ዓመት የተጀመረው የምገባ ፕሮግራም ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ትምህርት ቢሮ ኃላፊው፤ በ2015 ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ተማሪዎችን ለመመገብ ታቅዶ አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ተማሪዎች መመገብ ተችሏል ብለዋል፡፡ በ2016 የባለፈውን ዓመት ዕቅድ በማሳደግ ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ተማሪዎች ለመመገብ እቅድ መያዙንና በትምህርት ዘመኑ ስኬታማ ትምህርት ለመስጠት በተገቢው ጊዜ ትምህርት እንደሚጀምርም ገልጸዋል፡፡

በ2015 የትምህርት ዘመን 10 ነጥብ 2 ሚሊዮን ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው እንደነበሩ የጠቆሙት ዶክተር ቶላ፤ በ2016 የትምህርት ዘመን 11 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡ ይህም በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ገበታቸው ያቋረጡ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ገበታቸው በመመለስና ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ አዳዲስ ተማሪዎችን በማስገባት ቁጥሩን ለመጨመር በዕቅድ


ዶክተር ቶላ በሪሶ

እየተሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡

ክልሉ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ ውጤታማ ሥራ እየሠራ መሆኑን የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ ባለፈው ዓመት 11 ሺ 12 ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ የተደረጉ ሲሆን፤ በ2016 ወደ 15 ሺ ከፍ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በ2015 የትምህርት ዘመን ለተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆን የታቀደው 27 ሚሊዮን መጽሐፍት እንደነበር ያስታወሱት ቢሮ ኃላፊው፤ የመጽሐፍ ችግር እንደ ሀገር ያለ እጥረት በመሆኑ ከታቀደው ማድረስ የተቻለው ስምንት ሚሊዮን ሲሆን፤ በተያዘው ክረምት ሦስት ሚሊዮን በድምሩ እስካሁን በክልል ከተያዘው ዕቅድ 11 ሚሊዮን ብቻ ነው ብለዋል፡፡ አንድ ለሁለት ስሌት ተሠርቶ እቅድ ቢያዝም ችግሩ በ2016 ፈተና ሆኖ ይቀጥላል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የመጽሐፍ ችግሩ ከውጭ ምንዛሪ ጋር የሚያያዝ ነው ያሉት ዶክተር ቶላ፤ ማተሚያ ቤት ቢኖርም የማተሚያ ወረቀት ተገዝቶ የሚገባው ከውጭ በመሆኑ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ስላልተቻለ እቅዱን ለማሳካት እንቅፋት ፈጥሯል ነው ያሉት፡፡

የተጀመረው አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ከ9 እስከ 12 ባለው የትምህርት እርከን በዚህ ዓመት ይተገበራል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ለመምህራን የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እየተዘጋጀ መሆኑንና የመምህራን ሙያ ማሳደጊያ ማዕከል አዳማ ላይ እየተገነባ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ቶላ ገለጻ፤ በክልሉ 27 ሺ ትምህርት ቤቶችና ሁለት መቶ74 ሺ መምህራን ይገኛሉ፡፡ በእንግሊዝኛ፣ በሂሳብና በአማርኛ ትምህርት ከፍተኛ የመምህራን እጥረት አለ፡፡ ይህን ለመቅረፍ ካሉት ሦስት ሺ ሱፐር ቫይዘሮች ሁለት ሺ ሁለት መቶ የሚሆኑትን ወደ መምህርነት የመመለስና 9 ሺ መምህራን የቅጥር ሥራ ተፈጽሟል፡፡

# "በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ አስከፊ እየሆነ መጥቷል"

## - የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ከማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛና ችግሩም አስከፊ እየሆነ መምጣቱን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ደሴ ከፋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና በዚያው ልክ ጉዳቱም እየከፋ መጥቷል፡፡ በተለይ ደግሞ ከማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ጋር በተገናኘ ሀሰተኛ መረጃ በስፋት እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

የሀሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግር ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ሀገር አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ዳይሬክተሩ አንስተዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ችግር እያመጣ እንዳለ በመጥቀስ፤ በኢትዮጵያም ግለሰቦችና ተቋማትን ጨምሮ እንደ ሀገርም "እየተፈተንበት" እንገኛለን ብለዋል።

ዳይሬክተሩ፤ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ከጊዜ ወደጊዜ እየበዛና ችግሩም አስከፊ እየሆነ መምጣቱን በመጥቀስ፤ ይህ የሆነውም ከማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋትና የተጠቃሚዎች ቁጥር እያደገ ከመምጣት ጋር በተያያዘ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በርካታ ሀገራት ችግሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሕግ አውጥተው በመተግበር ላይ ናቸው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያም በ2012 ዓ.ም ጥላቻ ንግግርንና ሀሰተኛ መረጃ ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዋጅ ማውጣቷን አውስተዋል።

ማንኛውም ሰው የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ እንዳለበትም አዋጁ እንደሚደነግግ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ጉዳዮች በአዋጁ እንደተቀመጡ ጠቁመዋል፡፡

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በዋናነትም የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ አስከፊነትና መከላከያ መንገዱን በተመለከተ ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎችና ለማኅበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሠራ ኃላፊነት እንደተጣለበት አንስተዋል፡፡ በዚህም መሠረት ባለሥልጣኑ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ለመስጠት የተለያዩ መድረኮችን ሲያካሂድ መቆየቱን አስታውቀዋል። በ2015 ዓ.ም ብቻ ከ30 በላይ መድረኮችን ማዘጋጀት እንደቻለ ጠቅሰዋል፡፡ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራው በቂ እንዳልሆነና ይህ ወደፊት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አዋጁ እንደሚደነግግ ጠቅሰዋል፡፡ እነዚሁ ተቋማት የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ጉዳይ በደረሳቸው በ24 ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ከአውታራቸው ላይ ማስወገድ እንዳለባቸው በአዋጁ ላይ መቀመጡን ገልጸዋል። ባለሥልጣኑም ይሄንን ጉዳይ እየተከታተለ ሪፖርት እንደሚያዘጋጅና ለሚመለከተው የፍትህ አካል እንዲሚሰጥ ነው የተናገሩት።

የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን የሚያስተላልፉ አካላት የወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆኑ በመጥቀስ፤ ድርጊቱን ሲፈጽሙ የተገኙ አካላትን ኅብረተሰቡ በ9192




ነጻ የስልክ መስመር ጥቆማ በመስጠት የዜግነት ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት አመላክተዋል፡፡ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች መረጃን አጥርተው መጠቀም እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

# ኮርፖሬሽኑ በኬንያና በደቡብ ሱዳን የከፈታቸው አዳዲስ ቅርንጫፎች በቅርቡ ሥራ ይጀምራሉ

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ኢንጅነር ዮናስ አያሌው

አዲስ አበባ፡- ኮርፖሬሽኑ በኬንያና በደቡብ ሱዳን የከፈታቸው አዳዲስ ቅርንጫፎች በመጪው መስከረም ወር 2016 ዓ.ም ሥራ እንደሚጀምሩ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጅነር ዮናስ አያሌው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኮርፖሬሽኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ተወዳዳሪ ለመሆን ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡ ከጅቡቲ በተጨማሪ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ቅርንጫፎችን ለመክፈት እየሠራ ይገኛል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በኬንያና በደቡብ ሱዳን የከፈታቸው አዳዲስ ቅርንጫፎች በቅርቡ ሥራ ይጀምራሉ፡፡

ኮርፖሬሽኑ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች በሆኑት በኬንያና በደቡብ ሱዳን አዳዲስ ቅርንጫፎችን በመክፈት ላይ ይገኛል ያሉት ኢንጅነር ዮናስ፤ እነዚህ ቅርንጫፎች በመጪው መስከረም ወር 2016 ዓ.ም ድረስ የሕጋዊነት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ወደ ሥራ የሚገቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከእነዚህ ሀገሮች በተጨማሪም በግብጽ፣ በሩዋንዳ፣ በኢኳቶሪያል ጊኒና በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችም ቅርንጫፎችን በመክፈት ለመሥራት ዕቅድ እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡

በአህጉሪቷ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስምምነቶችን ለማድረግ አፍሪካዊ የሆነ ተቋም ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ እንደነበረ አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ ኤምባሲ አማካኝነት ጅቡቲ ውስጥ ከአንድ የኮንስትራክሽን ተቋም ጋር ስምምነት በመፈጸም የ60 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ግንባታ ለማካሄድ እየተጫረትን ነው ብለዋል።

ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋስኑ የመንገድ ግንባታዎችን ኮርፖሬሽኑ በማከናወን ላይ እንደሚገኝና ከዚህ በተጨማሪ የስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዶላር የሕንፃ ግንባታ ውል በመግባት እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በስፋት የእስያና የአውሮፓ ሀገራት የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በአፍሪካ ሀገራት ላይ እየሰሩ ናቸው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ከእነዚህ ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆንና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በጋራ ለመሥራት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት አምባሳደሮች ጋር ውይይት መደረጉን ገልጸዋል፡፡ በዚህም መሠረትም ሀገሮች ገብተን የግንባታ ሥራዎችን እንድንሠራ ጥያቄ አቅርበዋል ነው ያሉት፡፡

የሪፎርም ሥራዎችን በመሥራት ተቋሙን ለተቀረው ዓለም ለማስተዋወቅ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ተቋሙን የለውጥ ሥራዎች መጥተው እንደጎበኙም ተናግረዋል፡፡

ተቋሙ አቅሙን እያሻሻለ በመምጣቱ ከኢትዮጵያም አልፎ በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ማሠልጠኛ ማዕከል ግንባታ በማጠናቀቅ በቅርቡ ሥራ ለማስጀመር በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ አንስተዋል፡፡

በአፍሪካ ውስጥ አፍሪካዊ የሆነ የኮንስትራክሽን ተቋም እምብዛም መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ኢትዮጵያን ለየት የሚያደርጋት ከ90 በመቶ በላይ የሆነው የኮንስትራክሽን ሥራ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የሚሠራ መሆኑ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በውጭ ሀገራት ተቋራጮች ይሠሩ የነበሩ ግንባታዎችንም በሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች መሥራት እየተቻለ መሆኑን አንስተው፤ ለአብነትም በአዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ አራት የምድር ቤትና ባለ 21 ፎቅ ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የምድር ቤቱን ግንባታ በማጠናቀቅ አምስተኛ ፎቅ ላይ መድረስ ተችሏል ነው ያሉት፡፡

ኮርፖሬሽኑ ከኢትዮጵያም አልፎ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ተቋማት ጋር ውድድር የሚያደርግ መሆኑን ገልጸው፤ ለመንገድ፣ ለውሃና ለሕንፃ ግንባታ የሚውል ሶፍት ዌርና ሀርድ ዌር በመግዛት ተግባራዊ እያደረገ እንደሆነ ኢንጅነር ዮናስ አብራርተዋል፡፡

# በ2015/16 የመኸር ወቅት 573 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

### - እስካሁን ከ15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በ2015/16 የመኸር ወቅት 573 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ እስካሁን ከ15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር እንደተሸፈነም ተገልጿል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር) ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በመኸር እርሻ ለማረስ ከታሰበው 17 ነጥብ 39 ሚሊዮን ሄክታር መሬት 573 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት 17 ነጥብ 59 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማረስ የተቻለ ሲሆን፤ 15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር ያህሉ በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከ7 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በላይ እርሻም በኩታ ገጠም ለምቷል፡፡

ሀገሪቷ የመስኖ፣ የበልግና የመኸር ወሳኝ የምርት ወቅቶች እንዳሏት የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በሦስቱም ወቅቶች በርካታ ሰብሎች ተዘርተው እንደሚመረቱ ተናግረዋል፡፡ እንደ ሀገር በቤተሰብና በሀገር ደረጃ የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ለውጭ ገበያ ሊውሉ የሚችሉ በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት የተለዩ ምርቶችን በበቂ ሁኔታ ማምረትና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን መተካት የሚሉ ሦስት የስትራቴጂክ ዓላማዎች ተቀምጠው እየተሠራባቸው እንዳለም ጠቅሰዋል፡፡

ግብርና ከ80 በመቶ በላይ ለሚሆኑ የሀገሪቱ ዜጎች የኑሮ መሠረት መሆኑን በመጥቀስ፤ በመስኖ፣ በበልግና በመኸር ምርትን በጥራትና በብዛት ለማምረት በልዩ ትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተለይ በ2015/16 የመኸር ወቅት ለስንዴ ልማት 3 ነጥብ 66 ሚሊዮን ሄክታር ለማረስ ታቅዶ እስካሁን ከ2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ ዘር መሸፈን እንደተቻለ ተናግረዋል፡፡

በ2015/16 የመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈኑት ውስጥ ጤፍ 1ነጥብ 4 ሚሊዮን፣ ሩዝ 990ሺህ፣ አኩሪ አተር 705 ሺህ ሄክታር መሬት መሆናቸውን ነው የገለጹት። አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ ባሉት የሆርቲካልቸር ምርቶች ደግሞ 390 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጸዋል፡፡ የሩዝ ምርትን እንደ ሀገር በስፋት ለማምረት ባለሙያዎችን የማደራጀት ሥራ መሠራቱንም ጠቁመዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንደገለጹት፤ በተለይ በስንዴ ልማት በበልግ፣ በመስኖና በመኸር ወቅቶች በመሬትና በምርት ብዛት እድገት እያሳየ መጥቷል። ልማቱ በሦስቱ የምርት ወቅቶች በ2014/15 በአጠቃላይ ከነበረበት 4 ነጥብ 47 ሄክታር መሬት 23 በመቶ በመጨመር 5 ነጥብ 5 ሄክታር ማድረስ ተችሏል፡፡ ስንዴን በ2014/15 የምርት ዘመን ከተደረሰበት 154 ነጥብ 82 ሚሊዮን ኩንታል በ26 በመቶ በማሳደግ 195 ነጥብ 35 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማድረስ ታቅዷል፡፡

በአማራ ክልል ባለው የፀጥታ ሁኔታ በመኸር ወቅት የሚስተጓጎሉ የግብርና ሥራዎች በሌሎች አማራጮች ሊካካሱ እንደሚችሉም ነው ሚኒስትር ዴኤታው የገለጹት፡፡

አንበጣ፣ ግሪስ ወፍና ሌሎች የሰብል ተባዮች ለምርት ዘመኑ ተግዳሮት እንዳይሆኑ በአውሮፕላን አሰሳ በማድረግ የመከላከል ሥራው እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በምርት ዘመኑ መንግሥት 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ በማድረግ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ በአነስተኛ ዋጋ ማከፋፈሉንም ጠቁመዋል፡፡

# በመዲናዋ በሁለት ነጥብ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በላይ በሆነ ወጪ ስድስት ተሻጋሪ ድልድዮች እየተገነቡ ይገኛል፡፡

እንደ ኢንጂነር ሞገስ ገለጻ፤በመዲናዋ ከሁለት ነጥብ ሦስት ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው ትልልቅ የወንዝና ተሻጋሪ ድልድዮች እየተገነቡ ይገኛል፡፡

ፕሮጀክቱ ከሚገኙባቸው መንገዶች መካከል የኢምፔሪያል፣ቦሌ ሚካኤል፣ቃሊቲን ጨምሮ ጥሩነሽ ቤጂንግና ለቡ ተሻጋሪ ድልድዮች ይገኙበታል ያሉት ኢንጂነር ሞገስ፤ ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ በቀለበት መንገድ የሚታየውን ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ መጨናነቅ ለመፍታት ያስችላሉ ብለዋል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከአንድ ሺህ አስራ አራት ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታና ጥገኛ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፤ በተለይም የትራፊክ ፍሰትን በማሳለጥ ፤ የመንገድ ደኅንነትን በማረጋገጥ የጉዞ ጊዜና ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ኢንጂነር ሞገስ አስረድተዋል፡፡

በከተማዋ የመንገድ መሠረተ ልማት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን በመግለጽ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ82 በላይ የአስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለትራፊክ ክፍት መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ ፍሰቱን ለማስተካከል የሚረዱ መሆናቸውን የገለጹት ኢንጂነር ሞገስ፤ ለሚቀጥሉት ዓመታት የትራፊክ ፍሰቱን ለማሳለጥ የሚያስችሉ የትራንስፖርት ማስተር ፕላን እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በመዲናዋ ለሚቀጥሉት አስር ዓመታት የሚሠሩት መንገዶች ዲዛይን እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከ500 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሊጠይቅ የሚችል መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ ለካፒታል ፕሮጀክት ልዩ ትኩረት በመስጠት ከበጀቱ ከ60 በመቶ በላይ የሚመድብ መሆኑን ጠቅሰው፤ በበጀት ዓመቱ ከ11 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ በጀት መመደቡን ገልጸዋል፡፡

# ለዘመን መለወጫ በዓል...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል።

ለበዓሉ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች የዘይት፣ ዶሮ፣ ስጋና እንቁላል እንደሚያቀርቡ የተናገሩት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ፤ ለዚህም የገንዘብ አቅርቦት ችግር እንዳይገጥማቸው በኦሮሚያ 6.1 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በአዲስ አበባ 1.4 ቢሊዮን ብር ብድር መቅረቡንና በሌሎችም ክልሎች ብድሮች መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

የምግብ ዘይት አቅርቦት ላይ በመንግሥት በኩል በቂ ዝግጅት መደረጉን ተናግረው፤ በቂ አቅርቦት በመኖሩ በበዓሉ ምክንያት የዋጋ ጭማሪ እንደማያጋጥም ጠቁመዋል፡፡ የግብርና ውጤቶች ላይ የሌማት ትሩፋት ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውን ተናግረው፤ በአዲስ አበባ ለበዓሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንቁላሎች መዘጋጀታቸውንና ዋጋቸውም ከአስር ብር በታች እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡

ምንም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሳይኖር በዓሉን ምክንያት አድርገው ዋጋን የሚያንሩ ነጋዴዎች ሲያጋጥሙ ኅብረተሰቡ ጥቆማ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የተፈጠረው የኑሮ ውድነት ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች አሉት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የአቅርቦት ከፍላጎት ጋር ያለመጣጣም አንዱ ሲሆን፤ ያለውን ለማቅረብ በየአካባቢው ያሉ የጸጥታ ችግሮች ሌላው ምክንያት ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃም የሸቀጦች ዋጋ ከፍ ማለቱ እንደ ስኳር፣ዘይት ፣ሩዝና የሕፃናት ወተት የመሳሰሉ ምርቶች ከውጭ በግዢ የሚገቡ በመሆኑ የዋጋ ንረት እንዲፈጠርና የኑሮ ውድነቱ ከፍ እያለ እንዲመጣ ምክንያት መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማስተካከል እርምጃ እየወሰደ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

የኑሮ ውድነቱ እንዲቀንስ የቅዳሜና የእሁድ ገበያ መደበኛ እየተደረገ መሆኑን ተናግረው፤ በየከተሞቹ ሸማቹ በቀጥታ ከአምራቹ የሚያገኝበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመላክተዋል። በአዲስ አበባ 170 የሚጠጉ የቅዳሜና የእሁድ ገበያዎች መደራጀታቸውን እና ከአቅርቦት ሰንሰለቱ ደላሎች እንዲወጡ መደረጉን አስታውሰዋል።

በሦስት ወር ውስጥም አላግባብ በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ በመግባት ኅብረተሰቡን ለአላስፈላጊ ችግር በዳረጉ 395ሺ ሕገወጦች ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ ርምጃ መወሰዱንም ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ቀጸላ ሸዋረጋ በበኩላቸው፤ የፓልም ዘይት በበቂ ሁኔታ እየገባ መሆኑን ተናግረው፤ ባለ 3ሊትር 324ብር፣ ባለ 5 ሊትር 526 ብር እንዲሁም ባለ 20 ሊትር 2064 ብር ለሸያጭ መቅረቡን ተናግረዋል።

መንግሥት ከዚህ ቀደም ያስገባውን ሩዝ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ በአዲስ አበባ፣ሻሸመኔ፣ባህር ዳርና ደሴ ላይ በኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣በአለ በጅምላ መጋዘንና በኢትፍሩት በኩል እየተሰራጨ መሆኑን ጠቁመው፤ ከፍተኛ የዋጋ ቅናሽ ያለው በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብአት ልማት ድርጅት በኩል የዳቦ ዱቄት መዘጋጀቱንና በአለ በጅምላ መጋዘኖች ፓስታ፣ መኮረኒ እና የወጥ ማጣፈጫዎች አቅርቦት ላይ በቂ ዝግጅት መደረጉ ተገልጿል።

# "በአማራና በኦሮሚያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እየተከታተለና እያሳደደው እንደሆነ ገልጸዋል። አሁን ከሕዝቡ እየተነጠለ ያለውን ይህን ኃይል አቅሙን በማዳከም ስጋት ከማይሆንበት ደረጃ ማድረስ ተችሏልም ሲሉ ገልጸዋል።

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ሆነው የሀሰት ፕሮፖጋንዳ የሚነዙ ኃይሎች ለሀገርና ለሕዝብ ሲል ውድ ሕይወቱን እየከፈለ ሰላም የሚያረጋግጠውን ሠራዊት ሥነ-ልቦና ያልተረዱ ናቸው ያሉት ኢታማዦር ሹሙ፤ ሠራዊቱ በተሰማራባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ሁሉ ሕገ-መንግሥታዊ ተልዕኮውን በአስተማማኝ ሁኔታ እየተወጣ ነው ብለዋል፡፡

የፅንፈኞች የሀሰት ፕሮፖጋንዳን የተገነዘበው ሕዝባችን ከመከላከያ ሠራዊቱ ጎን በመሆን ለሰላሙ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ መሆኑን የተናገሩት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ በሀሰተኞች ሴራ ተታለው ከፅንፈኞች ጋር የተሰለፉ ወጣቶች በሰላማዊ መንገድ ወደ ሕዝቡ እንዲመለሱም ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡


መከላከያ በ2015 የበጀት ዓመት ተልዕኮውን በሚገባ መፈጸሙን የገለጹት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ በ2016 የበጀት ዓመትም እንደ ተቋም የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ከምንጊዜውም በላይ ዝግጁ ነው ብለዋል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት


የውስጥ ገጾች

## የጉበት በሽታ፡- ዝምተኛው ገዳይ




ገጽ 8

## ‹‹ ሁለት የጥንቅሽ ዝርያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እንዲመዘገቡም አድርጌያለሁ››

- ዶክተር ፋንታሁን ወልደሰንበት
የኢንዱስትሪያል ባዮቴክኖሎጂ ዳይሬክተር



ገጽ 6

## ቁጭት የወለደው ስኬት ከሳውዲ እስከ ባቢሌ



ገጽ 18


ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አዲስ አበባ
The Vibrant Hub of Africa


አፍሪቃዊቷ መልጎቅ

# የሥነ - ጥበብ ጥቁሩ መልክ

ዳንኤል ዘነበ

ሥነ-ጥበብ፣ የሰው ልጅ የሚኖርበትን ዘመንና ጊዜ መሠረት አድርጐ፣ አኗኗሩን ልዩ በሆነ መንገድና ሁኔታ፣ ሥነ-ጽሑፍን፣ ሙዚቃን፣ ሥነ-ጥበብን፣ ቴያትርን፣ ሲኒማን... ወዘተ በመጠቀም የሚገልጽበት ዘርፍ ነው። ከሥነ-ጥበብ ጋር ተያይዞ በሥነ ውበት የፍልስፍና ጥናት (philosophy of art) ውስጥ መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ ከሚነሳ ጥያቄ መካከል፣ የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራ ዐቢይ ፋይዳው ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ፣ በተለያዩ ከያኒያንና የኪነ-ጥበብ ምሁራን መልስ ሆነው የቀረቡ ሁለት አስተምህሮዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አስተምህሮ፣ ሥነ-ጥበብ ለጥበብነቱ ፋይዳ ብቻ መሠራት አለበት የሚል ነው። የዚህ አስተምህሮ ዐቢይ አቀንቃኝ ከያኒያንና ምሁራን እሳቤ፣ የሥነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራ፣ የራሱ ተፈጥሮአዊ ጥበባዊ አላማ ስላለው ፣ ለሌሎች ዓለማዊ ጉዳዮች (ፖለቲካ፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ ባህል... ወዘተ) ያለውን ቀጥተኛ ግልጋሎት ግብ ሳያደርግ መሠራት አለበት የሚል ነው ፡፡

ሁለተኛው አስተምህሮ፣ ከያኒ የኪነ-ጥበብ ሥራን መሥራት ያለበት የፈጠራ ሥራው ከብዙኃኑ ኅብረተሰብ ኑሮ አንፃር የሚሰጠውን ጥቅም (utility) ግብ አድርጎ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ በዚህኛው አስተምህሮ ፣ ከያኒው በጥበባዊ የፈጠራ ሥራው ውስጥ፣ የማኅበረሰቡን ነባራዊ አኗኗር የመዳሰስና በተለያየ አቅጣጫ ተጨባጭ የሆነ ግልጋሎት እንዲሰጥ አድርጐ የመሥራት ኃላፊነት አለበት ይላል፡፡ ከዚሁ ሃሳብ ጋር በርካታ ልሂቃን የሚስማሙ ሲሆን፤ በሀገራችን እውቅ የሙዚቃ ባለሙያዎች ውስጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነው የሙዚቃ ባለሙያ እና የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የኪነ-ጥበብ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሰርፀ ፍሬስብሐት አንዱ ነው። ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ "የአሉታዊ መጤ ባህሎች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች ተጽዕኖን




መከላከል ላይ የባለድርሻ አካላት ሚና" በሚል መሪ ቃል 8ኛው ባዘጋጀው ቶክሾ ላይ የሙዚቃ ባለሙያው ሰርፀ ፍሬስብሐት ባቀረበው የመነሻ ሃሳብ ላይ በጥልቀት ተመልክቶታል።

የሙዚቃ ባለሙያው ሰርፀ እንደሚናገረው፤ሥነ-ጥበብ ጥላቻን በፍቅር ፣ መነቃቀፍን በመተራረም፣ መለያየትን በመገናኘት፣ ቂምና በቀልን በይቅርታ የማከም ምትሀታዊ ኃይል አላት፡፡ ነገር ግን በሥነ ጥበብ ውስጥ የሚቀረጽ አስተሳሰብ ትክክለኛ የሆነ የአመለካከት ለውጥ እንደሚያመጣ ሁሉ ፤ አስቸጋሪ የሆነ የአመለካከት ጥመትም ያመጣል። በተለይ በያዝነው ካፒታሊስት እና ግሎባላይዜሽን መገለጫው ባደረገው በዚህ ዘመን አሉታዊ ጎኑ ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ይናገራል። የሥነ-ጥበብ ሥራዎች የአሉታዊ መጤ ባህሎች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና አስተሳሰቦች እንዲሰርፅ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑን ያብራራል።የሥነ ጥበብ ሥራ በጣም በረቀቀ መንገድ የሚሠራ በመሆኑ ጉዳቱ የሚታወቀው ቆይቶ ነው። በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚደረግ እንቅስቃሴን በዓይናችን እንታዘበዋለን። ይሁን እንጂ አንድ ሥነ ጥበባዊ ሥራ አስተሳሰባችንን ቀርፆን ፣ ተግባር ውስጥ ከገባን ፣ ቤታችንን ከቀያየረው ፣ ከጎዳን በኋላም አናውቀውም ። ልክ ጦር ሜዳ ላይ ፈሪ የነበረን ሰው ፣ አንድ ሽላይ ድንገት ጀግና ያደርገዋል ። ጎራዴ ይዞ ጦርነት መሀል ገብቶ ታላቅ ጀብድ ፈጽሞ ይወጣል። ይህ የሥነ ጥበብ ኃይሏ፤ የሰውን ልጅ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ከተፈጠረበት ጸባይ ውጪ እንዲሆን የማድረግ አቅም እንዳላት አመላካች ነው። ለዚህ ነው ሥነ ጥበብ ምን መልክ መያዝ አለባት የሚል ክርክር መምጣት ያለበት መሆኑን ይገልጻል። ሥነ ጥበብ የምትሸከመው ሃሳብ ምንድነው የሚለው ጉዳይ ሊያስጨንቅ ይገባል። በተለይ የዚህ ዘመን ሥነ ጥበብ መፈተሽ ያለባት ፈላስፎቹ 'ኤግዚዮሎጂካል አጠያየቅ' በሚሉት የፍልስፍና ዘይቤ አንጻር መሆን እንዳለበትም ይጠቁማል። "ኤግዚዮሎጂ ማለት ነገረ ፋይዳ ፣ ነገረእሴት ሲሆን፤ የሥነ ጥበብ ፋይዳን ግብረ ገብን ፣ ሥነ ምግባርን ፣ ሥነ ውበትን መሠረት አድርጎ ይጠይቃል። የሥነ ጥበብ የውበት ደረጃው ከተሟላ በኋላ ደግሞ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድነው፣ በውስጡ የያዘው ጭብጥ ምንድነው ብሎ የሚሞግት ነው። ስለዚህ የኤግዚዮሎጂ ሃሳብ መጥቶ ምንነታችንን ማንነታችንን የምንሠራውን ሥራ ፋይዳ ዋጋ ሊመዘን ይገባል" ሲል ያብራራል።

ሥነ ጥበብ የምትሠራው ለሥነ ጥበባዊ ፋይዳ ነው የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችል ያመላከተው ሰርጸ፤ በርግጥ ሥነ ጥበብ በፈጠራ መንገዷ ምናብን በማርቀቅ ሰማየ ሰማያት ድረስ ያለ ከልካይ የምትጓዝ ፣ ነጻነቷ ሊገደብ የማይችል ናት። የሙያ መራቀቅና የማስደነቅ ጉዞዋ በፍጹም ሊገደብ አይገባውም። ይሁን እንጂ በሥነ ጥበባዊ ነጻነት ሰበብ ማኅበረሰብን አጽንተው ያቆሙ የግብረ ገብና የሰብዓዊነት ፣ የባህል ፣ የሃይማኖት ሥርዓቶች ሁሉ እንዲናዱ መፍቀድ አስፈላጊ አይደለም። ስለዚህ የሥነ-ጥበብ ሥራ መሠራት ያለበት የብዙኃኑን ኅብረተሰብ ማንነት መሠረት አድርጎ እንጂ ጥበባዊ ፋይዳውን ብቻ መሠረት ተደርጎ ሊሠራ እንደማይገባም ይጠቁማል።

በመሆኑም፣ ሥነ- ጥበብ በከፍተኛ ጥንቃቄ መታየት አለባት። የኤግዚዮሎጂ ሃሳብ መጥቶ ምንነታችንን ማንነታችንን የምንሠራውን ሥራ ፋይዳ ዋጋ ሊመዘን ይገባል። በሁሉም ጥበቦች ውስጥ ሊኖር ይገባል። የፈጠራ ሰዎች በሥነ - ጥበብ ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ሁሉ ሊያምኑ አይገባም። ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። የሥነ ጥበብ የሙያ ማኅበራት ፣ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ፣ የሥነ ጥበብ ከፍተኛ እና መለስተኛ ማሠልጠኛ ኮሌጆች የሥነ ጥበብ ምን ደረጃ ላይ ነው ያለው የሚለውን ወደ ርዕስ ነገር ማምጣት ይኖርባቸዋልም ይላል ።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «ሁለት የጥንቅሽ ዝርያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እንዲመዘገቡም አድርጌያለሁ»

- ዶክተር ፋንታሁን ወልደሰንበት
የኢንዱስትሪያል ባዮቴክኖሎጂ ዳይሬክተር

ጽጌረዳ ጫንያለው

**ዶክተር ፋንታሁን ወልደሰንበት ይባላሉ፡፡ በመምህርነት፣ በኮሌጅ ሬጅስትራርነት፣ በኮሌጅ ዲንነት፣ በምርምር ዳይሬክተርነት፣ በዓለምአቀፍ ምርምር ፕሮግራሞች ማኔጀርነት ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ናቸው፡፡ በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም ደረጃ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን አስተባብረዋል፡፡ በምርምር ዘርፉም የባለቤትነት መብትን ያረጋገጡበት ሥራዎችን አበርክተዋል።**

**በ2009 ዓ.ም የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን በመስራችነት የተቀላቀሉ ሲሆን፤ አሁን ላይ በኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪያል ባዮቴክኖሎጂ ዳይሬክተር ናቸው፡፡ በተመራማሪነት እና መሪ ሥራ አስፈጻሚነት በማገልገል ላይም ይገኛሉ። ተቋሙ ከብዙ ዓመታት ቆይታና ጥናት በኋላ በሥራቸው ከተመረጡ ሰዎች መካከል አንዱ አድርጎ የመሪ ተመራማሪነት ወይም ፕሮፌሰር የሚባለውን ማዕረግ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሰጥቷቸዋል፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- የት ተወለዱ፤ ያደጉበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** አዲስ አበባ በተለምዶ ስድስትኪሎ ምስካዬ ኀዙናን ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው የተወለድኩት፡፡ አስተዳደጌም እንደማንኛውም ልጅ ነው። በወቅቱ እኔን ከእኩዮቼ ለየት ያደርገኛል ብዬ የማስበው ለነገሮች ያለኝ ምልከታ ነው፡፡ አንድን ነገር ካየሁና ካነበብኩ መቼም አልረሳውም፡፡ ተግባራትን ስፈጽም ለነገሮች ምላሽ የምሰጥበት ሁኔታም ፈጣንና ብዙዎች የሚፈልጉትን ዓይነት ነው፡፡

በተጨማሪም ቀልድ አዋቂ ልጅ ነበርኩ፡፡ እናም ነገሮችን በማስረዳት በኩል የተካንኩ ዓይነት ልጅ እንደሆንኩ ይነገረኛል፡፡ ሰዎች እንዳይረሱት እያዋዛሁም የመናገር ባህል አለኝ፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ ድረስ የተከተለኝና በቀላሉ ሰዎች ሀሳቦቼን እንዲቀበሉ የማደርግበት ልዩ ተሰጥኦዬ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትምህርትዎን የት ተማሩ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** ትምህርቴን እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ የተከታተልኩት የተወለድኩበት ቀዬ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ነው፡፡ የመጀመሪያውንም ሆነ ሁለተኛ ዲግሪዬን የተማርኩትም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪዬን በባዮሎጂ የትምህርት መስክ ሲሆን፤ ሁለተኛው አፕላይድ ማይክሮባዮሎጂ ነው፡፡

ከአዲስ አበባ በትምህርት ጉዳይ የወጣሁት ደግሞ ሦስተኛ ዲግሪዬን ለመማር ሲሆን፤ የሄድኩትም ባህር አቋርጬ ሕንድ ሀገር ነው፡፡ በዚያም ከፑንጃብ ዩኒቨርሲቲ በማይክሮባዮሎጂ መመረቅ ችያለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የትና በምን በምን ዘርፎች ላይ ሠርተዋል፤ የነበርዎት ኃላፊነትስ ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** ሥራዬ የሚጀምረው በመምህርነት ሲሆን፤ ቡርጂ ልዩ ወረዳ ነበር የተመደብኩት። የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ባህል በስፋት ያየሁበት ነው፡፡ ከዚያ ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ ከንባታ ጠንባሮ ዞን አንጋጫ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዛውሬ ማገልገል ቀጠልኩ፡፡ የትምህርት ዕድል አገኘሁና ዩኒቨርሲቲ ገባሁ፡፡ ቀጣዩ ሥራዬ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ የገባሁበት ሲሆን፤ በመምህርነት፣ በኮሌጅ ሬጅስትራርነት፣ በኮሌጅ ዲንነት፣ በምርምር ዳይሬክተርነት፣ በዓለም አቀፍ ምርምር ፕሮግራሞች ማኔጀርነት ለረጅም ጊዜ አገልግያለሁ፡፡

በወቅቱ የሳተላይት የምርምር ማዕከላትን ከጓደኞቼ ጋር በመሆን አቋቁሜያለሁ፡፡ በዓለም አቀፍ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ላብራቶሪዎች እንዲደራጁ አድርጌያለሁ፡፡ በባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከተቀላቀልኩ በኋላም የባዮኢኖቬት አፍሪካ ሁለተኛ ዙር የምርምር እና ልማት ድጋፍ በጥንቅሽ ዕሴት መጨመር ላይ በሦስት የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በተከናወነ ምርምር ዋና የፕሮጀክት መሪ ሆኜ ሠርቻለሁ፡፡

ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በተገኘ ድጋፍ በኢንስቲትዩቱ በተካሄዱ የአፍላቶክሲን ባዮኮንትሮል እና ማይክሮ አልጌ ምርምር ፕሮጀክቶች ላይም ተሳትፌያለሁ፡፡ በዚህም አመርቂ የምርምር ውጤቶችን እና የመጀመሪያውን ብሔራዊ የማይክሮ አልጌ ምርምር ላብራቶሪ ለማቋቋም የተቻለበት ነበር፡፡ በኮቪድ-19 ላይም በተከናወኑ ምርምሮች ከባዮኢኖቬት አፍሪካ እና ከቮልክስዋገን ፋውንዴሽን በተደገፉ የምርምር ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍም ችያለሁ፡፡

ከምርምር አጋሮቼ ጋር በመሆን ሁለት የጥንቅሽ ዝርያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ እንዲመዘገቡም አድርጌያለሁ፡፡ በእንሰት ቴክኖሎጂዎች ላይ አንድ ኢንዱስትሪያል ዲዛይን እና አራት ዩቲሊቲ ሞዴሎች በአጠቃላይ አምስት የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችን ማስጠበቅ ችያለሁ፡፡ የእንሰት መፋቂያ፤ መጭመቂያ እና ማብላያ ቴክኖሎጂዎች ለማኅበረሰቡ እንዲደርሱ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉም ከፍተኛ ጥረቶችን አድርጌያለሁ። እነዚህ ሥራዎቼም በዓለምአቀፍ ጆርናሎች ላይ የታተሙ ናቸው፡፡ በዚህና መሰል ሥራዎቼ ደግሞ በባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመሪ ተመራማሪነት ማዕረግን በቅርቡ ሰጥቶኛል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ፕሮፌሰር እንደማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢንዱስትሪ ባዮቴክኖሎጂ ምንድን ነው? ፋይዳውስ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** የኢንዱስትሪ ባዮቴክኖሎጂ ወይም ነጭ ባዮቴክኖሎጂ ማለት ባዮቴክኖሎጂን ለኢንዱስትሪ ሂደት እና ለኬሚካሎች፣ ቁሳቁሶች እና ነዳጆች ማምረቻነት መጠቀም ማለት ነው። በዚህም በሂደቱ ውስጥ ፋርማሲዩቲካልስ፣ ኢንዛይሞች፣ ባዮፊውል እና አሚሚዎች፣ ቫይታሚኖችን፣ አልሚ ምግቦች እና አዲስ ፖሊመሮች ይካተታሉ፡፡ ወደ ፋይዳው ሲገባ ደግሞ ኢንዱስትሪያል ባዮቴክኖሎጂ ሚናው ብዙ ነው። ለአብነት ምርታማነትን ያሳድጋል፡፡ አነስተኛ ሀብቶችን (ውሃ እና ባህላዊ የኬሚካል ምርቶችን) ለመጠቀም የሚረዳ ነው፡፡ መርዛማ አየርን ልቀት በመቀነስ በኩልም የማይተካ ሚና አለው፡፡ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ጨምሮ የቅሪተ አካል ነዳጆችን አጠቃቀም ይቀንሳል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢንዱስትሪ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እንደ ሀገር ምን እያከናወነ ነው?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** ዋናው በኢንዱስትሪ ባዮቴክኖሎጂ ዘርፍ ምርምር እና ልማት ማካሄድ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የሰውና መሠረተ-ልማት አቅምን መገንባት እና በዘርፉ የማማከር አገልግሎት መስጠት ሲሆን፤ በዚህም የሥራ ክፍሉ በሦስት የምርምር ቡድኖች ተዋቅሮ ይሠራል፡፡ እነዚህም የምግብ ባዮቴክኖሎጂ እና ማቀነባበር፣ የኢንዱስትሪ ባዮኬሚካሎች ምርምር እና ኢንዛይም ቴክኖሎጂና ሥነሕይወታዊ ምርት ሂደት የሚባሉት ናቸው፡፡

ሥራዎቹ ለምግብ፤ ለቆዳ እና ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃዎች እና የሂደት ግብዓቶችን ለማምረት ይረዳሉ፡፡ በዚህም በውጭ ምንዛሪ የሚገዙ ግብዓቶችን መተካት፤ ወደ ውጭ ሀገራት ተፈላጊ ምርቶችን በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት እና ሀገርን ባላት ሥነሕይወታዊ ሀብት እንድትጠቀም ማስቻል ነው፡፡ በተለይም ሀብቶችን ለልማት በማዋል ዕድገትን ማምጣት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንዳነሱት ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ናት፡፡ ሆኖም በምርምር ደግፎ ሥራዎችን ከማከናወን አኳያ ክፍተቶች እንዳሉበት ይነሳል፡፡ ምክንያቱ ምን ሲሆን ይችላል?**

**ዶክተር ፋንታሁን ፡-** እኔ ሕንድ እና ቤልጂየም እንዲሁም በአፍሪካ ሀገራት ደቡብ አፍሪካ፤ ኬንያ፣ ታንዛኒያ እና ሌሎች ሀገራትን አይቻለሁ፡፡ እነኝህ ሀገራት ምንም ከእኛ የተለየ ነገር የላቸውም፡፡ አንዳንድ ቦታ ላይ እንዲያውም ከእኛ ሀገር ያነሰ መሠረተ ልማት ጭምር አላቸው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የዓለም ፐብሊኬሽን በማተም በጣም ጉልህ ተጽዕኖ ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን።

የእኛ ችግር ታዲያ ምንድነው ከተባለ ብዙ ነገሮችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ አንደኛው አንድን ነገር ሥራዬ ብሎ እስከመጨረሻው የመሥራት ችግር አለብን፡፡ ያለንን ደግሞ ባለው አቅም ልክ የመጠቀም ችግርም ጎልቶ ይታይብናል።

ለአብነት አሁን ባለው ደረጃ ዩኒቨርሲቲዎች በጣም ብዙ ላብራቶሪዎች አሏቸው፡፡ በጥሩ ደረጃ ተደራጅተውም ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሥራ ለመቀጠል የሚቸገሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንመለከታለን፡፡ ይህ ደግሞ የሥራ ባህላችን ብዙ እንደሚቀረው የሚያሳይ ነው። መንግሥት ብዙ ነገሮችን ይገዛል፡፡ ነገር ግን ዕቃዎች ተገዝተው ጥቅም ላይ ሳይውሉ እንዲሁ የሚቀመጡበት ሁኔታ አለ፡፡ መንግሥት አካባቢ ያሉ ሰዎችም ስለ ሥራው ብዙም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች አይሠሩም፡፡ የሚሠሩ ሰዎችንም ማበረታታት ላይ ብዙ አይገፉበትም፡፡

ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱ በኋላ ለምን ውጤታማ ይሆናሉ፤ በምርምሩም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ላይ የተሳካላቸው ሆነው ናሳ ላይ ሳይቀር ሲሠሩ ለምን እንመለከታለን ቢባል መልሱ አንድ እና አንድ ነው፡፡ የሚያሠራቸው ሲስተም እንጂ እውቀት ብቻ አይደለም። ከሲስተሙ ጋር ተያይዞ የሚተገበረው አስገዳጅ ሁኔታ በቀጥታ መሥራትን ልምድ እንድናደርገው ዕድል ይሰጠናል፡፡ ስለዚህም የሌላ ዓለማት ተመራማሪዎች ኢትዮጵያ ካሉት የሚለዩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሲስተም ውስጥ የገባ ሰውና ያልገባ በሚል መውሰድም ይቻላል፡፡

አንድ ሥራ ሲተገበር ግልጽ የሆኑ እና መሳካት ያለባቸው እቅዶች ይቀመጣሉ፡፡ ያን እቅድ እንዲሳካ ለማድረግ በጀት እና አስፈላጊ ግብዓቶችም ይሟላሉ፡፡ ጊዜ ይመደብለታል፤ በዚያ ጊዜ መሠረት ደግሞ የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ተግባራቱም ቼክ የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡ ምንድን ነው መጨረሻ ላይ ማሳካት የሚጠበቅብህ ? ያንን በተባለው ጊዜ እና ሀብት ተጠቅመህ አሳክተሃል ወይ ? የሚልና መሰል ነገሮች ሞኒተሪንግ ይደረጋሉ፡፡ በመጨረሻም ውጤቱ ጥቅም ላይ ውሏል ወይ የሚለው ይታል፡፡ የወጣው ወጪና የተገኘው ጥቅም ይቀራረባል ወይ ተብሎ ይገመገማል፡፡ እኛ ሀገር ግን ይህ ሁሉ ነገር የለም፡፡ መቼ ተጀመረ? የት ደረሰ ? ከዚያ በኋላ ምንድን ነው የሚጠበቀው የሚሉት ነገሮች ከፕሮፖዛል አያልፉም፡፡ ጥብቅ የሆነ ክትትልም አይደረግባቸውም፡፡

ኦዲት ብንመለከት እንኳን በእኛ ሀገር የፋይናንሺያል ኦዲት እንጂ የፐርፎርማንስ ኦዲት አናይም፡፡ ምርምር በምንሠራበት ጊዜ ከራሳችን ፍላጎት እና ጥቅም አንጻር የምርምር ፕሮጀክቶች እንዲነድፉ ማድረግ ተገቢ ነው የሚለውም አይታይም፡፡ ለምሳሌ፡- ፕሮፖዛል ሲጻፍ በእንግሊዝኛ ነው፡፡ ሪፖርት ሲደረግም በእንግሊዝኛ ነው፡፡ ነገር ግን ስንት በመቶ የሚሆን ሕዝባችን እንግሊዝኛ ይናገራል? ስንል መልሱ ግልጽ ነው፡፡ እናም ለማን እንደምንሠራው እንኳን ሳናውቅ ነው ተግባሩን የምናከናውነው፡፡

ስለዚህ ምርምሮችን ስንሠራ የራሳችንን ሁኔታ ማየት እና ራሳችንን የሚጠቅመንን ነገር ለይተን መውሰድ ካልቻልን መቼም ቢሆን ችግሮች ሊፈቱ አይችሉም፡፡ የምንሠራው ደግሞ ለዓለም ከሆነ እኛን ሳይሆን እነርሱን ነው የምንጠቅመው፡፡ ምክንያቱም ዓለም ያለምንም ጥቅም ሊሠራ ፤ ሊደግፍና እውቅና ሊሰጥ አይችልም። እኛ ላይም ያለው ነገር ይህ ነው፡፡ ዓለምአቀፍ እውቅና ያለማግኘታችን ምስጢር አሠራሩንም፤ ተጠቃሚነቱንም ሳንገነዘብ መስራታችን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በምርምሩ ዘርፍ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተባብራ የምትሠራበት ሁኔታ ተፈጥሯል?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** አዎ፤ ብዙ ባይባልም ከተለያዩ የውጭ ተቋማት ጋር ምርምሮች ይሠራሉ፡፡ እንግዲህ በብዙ ዘርፎች ነው ምርምር የሚደረገው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህም በትብብር ምርምሮች ውስጥ በርካታ ዕድሎች ይኖራሉ፡፡ አንደኛው ምርምሩ የሚያካትታቸው ቦታዎች ሰፋ ስለሚሉ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብዙ ልፋትን አይጠይቅም፡፡ ዓለምአቀፍ የምርምር ፕሮጀክቶች ውስጥም ተካተን እንሠራለን። በዚህ ውስጥ መካተት በራሱ በርካታ ተሞክሮዎችን ለመጋራት ያስችላል፡፡ ሁሉም የየራሳቸውን ጥንካሬ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «ሁለት የጥንቅሽ ዝርያዎች...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ይዘው ስለሚመጡ በቀላሉ ሥልጠና ለማግኘትም ዕድል ይሰጣል፡፡

ሁለተኛ ላብራቶሪዎችን የግድ እዚህ መገንባት ሳያስፈልግ የትኛውም ቦታ ላይ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ሰፊ ፕሮጀክት ሲሆን ተሳታፊ ሰዎችም ስለሚበዙ ለችግሮቹ ጥሩ የሆነ የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብም ጥሩ ዕድል ነው፡፡ እንዲሁም የመረጃ ስርጭቱ የተሻለ እንዲሆን ያስችላል፡፡ ከዚህ አንጻር እስካሁን እኛ ብዙ የተጠቀምንባቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ባዮ ኢኮኖሚን በማበልጸግ በኩል፤ አሁን ደግሞ የተሻለ ሪጂናል አፐሬተሮች እንዲኖረን ከማድረግ አኳያ ምርምርን በጋራ መሥራቱ ብዙ አራምዶናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛ መንስኤው ሀገራት የሚጋሯቸው ነገሮች መኖራቸው ነው፡፡

እንደባዮ ቴክኖሎጂ የጥንቅሽ ፕሮጀክትን ብቻ ብናነሳ ዑጋንዳን፣ ኬንያ እና ኢትዮጵያን ያቀፈ ነው። በአጋጣሚ የፕሮጀክቱ መሪ እኔ ነበርኩና ጥቅሙን በሚገባ ማስተዋል ችያለሁ፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ ብዙ ብዝሃ ሕይወት ያላት ሀገር ናት፡፡ ይህ ብዝሀ ሕይወት ደግሞ ትልቅ ሀብት ነውና ከማንኛውም የዓለም ሀገራት ጋር ተቀናጅታ በምርምሩ ዘርፍ እንድትሠራ ያደርጋታል። ጥቅሟም የሚታየው ከዚህ አኳያ ነው፡፡ ስለዚህም መመልከት ያለብን በግለሰብ ደረጃ የተሠሩትን ምርምሮች ብቻ ሳይሆን በአጋርነት የተሠሩትንም ሊሆን ይገባል። ይህ ሲደረግ ግን አንድ ነገር ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡ ይህም የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በአደረገ መልኩ ነገሮች ቢከናወኑም ቅድሚያ ለሀገር መወገን ላይ መደራደር አይገባም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ፕሮጀክቶች ምን መልክ አላቸው፤ ምን ያህል ተጠቃሚ አድርገዋል ብሎ መውሰድ ይቻላል? ከችግሮቹ በመነሳት ምን ምን ነገሮች መሻሻል አለባቸው ይላሉ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-**የፕሮጀክት ሥራ ሰጥቶ መቀበል መርህ የሚታይበት ነው፡፡ በተለይም በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚመጡ ፕሮጀክቶች የተወሰነ የራሳቸውን ፍላጎት ይዘው የሚመጡ ናቸው፡፡ ፍላጎታቸው እስኪሳካ ሰጥቶ መቀበል መርህን ይከተላሉ። ስለሆነም ያለሽን ይዘሽ ስትቀርቢ ነው ሌላው ላንቺ ሊሰጥሽ የሚችለው፡፡ ወደ ጥቅሙ ሲገባ ከላይ እንዳልነው ነው፡፡ በምርምሩ ላይ የተመለከትናቸው ዕድሎች እዚህም ላይ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ፕሮጀክቶች ብቻቸውን የሚከወኑ ስላልሆኑ የሥልጠና ዕድል ይሰጣሉ፤ ድጋፍ ለማግኘትም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡ በተመሳሳይ መልካም ተሞክሮዎችን ከሌሎች ሀገራት ለመቅሰም መልካም አጋጣሚዎችን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-እንሰት ላይ አንድ ፕሮጀክት ነበረን፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ሁለት የፒኤች ዲ ተማሪዎች ተመርቀውበታል፡፡ ጥሩ እውቀትም ተገኝቶበታል፡፡

እንሰት በማብላላት ሂደት ውስጥ ቆጮ ሲሠራ ትንሽ በተወሰነ መልኩ ለተጠቃሚው የማይመቹ ነገሮች አሉት፡፡ እሱን ለማስተካከል የተሞከረበት ሁኔታ ነበር። ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ እንሰትን እንዴት ነው የሚጠቀምበት? ካልሽ መልሱ ቀላል ነው፡፡ በታዳጊ ሀገራት ያለውን የባህላዊ ምግብ አሠራሮች የዘመናዊው ማኅበረሰብም ማድረግ ነው፡፡ ይህንን አሠራር ሙሉ ለሙሉ ወስዶ ተፈጥሯዊው መንገድ ይታከልበታል፡፡ ያ ደግሞ የአኗኗር ዘይቤውን ከማሻሻል አኳያ የማይተካ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህንን የሚያደርጉበት ምክንያትም እንሰት በልቶ ያደገ ሰው ስታይ አጥንቱ ሰፋፊ ነው፤ ቁመቱም ረዥም ነው፡፡ ጤናማ ከመሆንም አኳያ ማንም አይደርስበትም፡፡

እነርሱ ጤናቸውን፤ የተለየ ሀብታችንን ለመጠቀም ስለሚሹ ትንሹን ድጋፋቸውን ያደርጋሉ፡፡ እኛ ደግሞ ያለንን አሟጠን እንሰጣቸዋለን፡፡ ስለዚህም አንድ መማር ያለብን ነገር አለ የሚል እምነት አለኝ፡፡ እኛ ከፕሮጀክቱ ውስጥ የምናገኘው ምንድነው የሚለውን በጥልቀት ማየት ነው፡፡ የመጠቀም እንድላችንን ከሁሉም አቅጣጫ ልንመረምረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነሱ ለምን መጡ?፤ ድጋፍ የሚሰጡን ምን ፈልገው ነው፤ በእነርሱ ፍላጎት ውስጥ የእኛን ጥቅም እንዴት አድርገን ማሳደግ አለብን? የሚሉ ነገሮችን ማጤን ይገባናል፡፡ ከዚያ ወደ ሥራው መግባት አዋጭነት ይኖረዋል፡፡

አንድ ፕሮጀክት ውጤት ማምጣቱ በትክክል የሚረጋገጠው ወደ ማኅበረሰቡ ዘንድ ሂዶ ኢኮኖሚ ውስጥ ገብቶ ለውጥ ሲያመጣ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል ሲፈጥር፣ ሀገርን ከነበረችበት ሁኔታ አንድ ደረጃ ከፍ ሲያደርግ ነው። ካልሆነ ግን ፕሮጀክቱ ልክ እንደምርምሮች ለይስሙላ ተሠርተው የመደርደሪያ ማሞቂያ ነው የሚሆኑት፡፡ ይህ ደግሞ የዘመኑ አስተሳሰብ የሚቀበለው አይደለም፡፡ ዘመኑ ለውጥና ምርት ይፈልጋል፡፡ ምርቱ አገልግሎት ሆኖ ሲቀየር ማረጋገጥን ይሻል፡፡ እናም በዓለም አቀፋዊ ጥናት የምወስደው ሼር እንዳለ ሆኖ ጥቅማችንንም አሁን ባልኩሽ አቅጣጫ ማስተካከል ይኖርብናል፡፡ እስከመጨረሻ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ላይ መሥራት የግድ ይለናል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- እንደ ሀገር በርካታ ጥቅም ሳይ ሳይውሉ የሚቀሩ በርካታ ፕሮጀክቶች ይስተዋላሉ፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** የሰለጠኑት ሀገራት ገንዘብ እንሰጣችኋለን ሲሉ እነሱ የሚፈልጉት ነገር አለ ማለት ነው፡፡ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ገንዘብ አንድ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘብ ብቻውን የነገሮች አንቀሳቃሽ ሊሆንም አይችልም፡፡ አስቻይ ሁኔታ የግድ ያስፈልጋል፡፡ የተሳለጠ አሠራር ለፕሮጀክቶች መሳካት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቢኖሩ ግብዓቶች የሚቀርቡበት የተሳለጠ ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረ የፕሮጀክቱ ጉዞ መንገድ ላይ ይቆማል፡፡

አንድ ፕሮጀክት ለማሳካት ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው በጀት ሲሆን፤ ሌላኛው አቅም ያለው የሰው ኃይል ነው፡፡ የማይሆን ሰው ፕሮጀክቱ ውስጥ ብታስገቢ "ኮንፊውዥን" እና ሌላ ግጭት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ለዚህ ሁነኛ ሰዎች መኖር አለባቸው፡፡ የተቆረጠ ጊዜ መኖርም አለበት፡፡ ከዚያ የፕሮጀክቱ መከታተያ እና በምን ጠነከረ? ምን ውድቅ ሆነ፣ እንዲስተካከል ምን ያስፈልጋልና መሰል ነገሮችን መመልከት ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት ከተሄደ ስኬቱ ላይ ይደረሳል፡፡ ሆኖም ብዙ ፕሮጀክቶች በወረቀት ደረጃ ጥሩ ሆነው፤ ገንዘብ የሚለግሱ ሰዎችን ቀልብ መሳብ ችለው በመጨረሻ ግን በመፈጸም ብቃት ጉድለት የወረቀት ጌጥ ሆነው ይቀራሉ፡፡ ለዚህም ነው እንደሀገር ስኬታማ ፕሮጀክቶች እንዳይታዩ የሆኑት፡፡ ወረቀት ላይ ያለው በተግባሩ ባለመታየቱ ማኅበረሰቡን ሲጠቅም አይታይም፡፡

በእርግጥ እንደሀገር ያለው ይህ ብቻ ችግር አይደለም። የመሠረተ ልማት፤ ተሳታፊ ሰዎች፤ የግዢ ሥርዓቱ፤ የሠራተኞች ሞራል፤ ከሰዎች ተጠቃሚነት አንጻር፤ ከአሠራር ሁኔታዎች፤ ከሥራ ባህል ጋር ያሉ አስቻይ ሁኔታዎች አኳያ የፕሮጀክቶች ስኬት ይለካል፡፡ ለዚህም አንድ ማሳያ ላንሳ፡፡ ለተሰጠው ገንዘብ የሚመጥን ሪፖርት ካልተደረገ በድጋሜ ገንዘብ የሚለው አካል አይኖርም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ፕሮጀክቱ በገንዘብ እጦት እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

አሁን እንደ ሀገር ከፕሮጀክት አተገባበር አኳያ ብዙ ልናስተካክላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ፡፡ የማስተካለል ዕድላችንም ሰፊ ነው፡፡ አንዱ ደግሞ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ከችግሮች ተምሮ ዳግም ስህተት ላለመሥራት

**በደሀና በሀብታም መካከል ሰፊ ልዩነት የሚታየው በፍጥረታቸው ሳይሆን በነገሮች የመጠቀም ብቃታቸው ነው፡፡ ድሃ ሕንፃን ያያል፡፡ ውስጡ ግን ማደር አይችልም፡፡ ምግብ ሰዎች ሲበሉ ይመለከታል፡፡ እርሱ ግን ከፍሉና መርጦ ሲመገብ አይቻለውም። ስለሆነም ሀብታም ነን ማለት የሚቻለው ያለንን ሀብት ስንጠቀምበት ነው**

መሞከር ነው፡፡ መሥራትን ባህል ማድረግና ለሀገር ሲባል የራስን ጥቅም መተውን ልምድ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች እንደሆነች ይታወቃል፡፡ ያለንን ሀብት በአግባቡ ተጠቅመናል ብሎ መውሰድ ይቻላል?**

**ዶክተር ፋንታሁን ፡-** ኢትዮጵያ በብዝኃ ሕይወትም፣ በማዕድንም፣ በሰው ሀብት እና መሰል ሁኔታዎች ሀብታም ነች፡፡ ነገር ግን ሀብት ሰዎችን ሀብታም የሚያደርገው ያለውን አውቆ ሲጠቀምበት ነው፡፡ በድሃ እና በሀብታም መካከል ሰፊ ልዩነት የሚታየው በፍጥረታቸው ሳይሆን በነገሮች የመጠቀም ብቃታቸው ነው፡፡ ድሃ ሕንፃን ያያል፡፡ ውስጡ ግን ማደር አይችልም፡፡ ምግብ ሰዎች ሲበሉ ይመለከታል፡፡ እርሱ ግን ከፍሎና መርጦ ሊመገብ አይቻለውም፡፡ ስለሆነም ሀብታም ነን ማለት የሚቻለው ያለንን ሀብት ስንጠቀምበት ነው፡፡ እናም ኢትዮጵያውያን ተፈጥሮ የቸረችን ባለጠጎች ብንሆንም ካልተጠቀምንበት ድሃ መባላችን አይቀርም፡፡ ከዚህ አንጻርም ሀብታም ነን ይባል እንጂ ያለንን ሀብት እንኳንስ መጠቀም ይቅርና ነክተነዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡

እንዳንጠቀም ያደረጉንን ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለተባለው ደግሞ ምላሹ ልዩ ልዩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ጣታችን ወደሌሎች መጠቆምን ብቻ የምንፈልግ መሆኑ ነው፡፡ በሌሎች ከማመካኘት ወደ ውስጥ ራስን መመልከት አንፈልግም፡፡ ሌላው የሥራ ባህላችን ውስን ነው፡፡ ለቀጣዩ ትውልድ ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲኖረው አላሳየነውም። ሠርተን አርአያ መሆን አልቻልንም፡፡ ያለንን ሀብት ለመጠቀም የተለያዩ ሥልጠናዎች የመውሰድ ክፍተት ይታይብናል፡፡ የግንዛቤ ሁኔታም እንዲሁ ችግራችን ነው።

አሁን ላይ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ ስለሆነም ሀገራችን የምትፈልገው እንካስላንትያ ሳይሆን የተግባር ሰው ነው፡፡ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደማኅበረሰብ አሁን ላይ ማተኮር ያለብን ሥራ ላይ መሆን ይገባዋል፡፡ ካልሆነ ግን የሚገጥመን ችግር እጅግ አደገኛ ይሆናል፡፡ ዋጋም ያስከፍለናል፡፡ እውነቱን ለመናገር አሁን ባለን ሥራ ባህል፤ አሁን ባለን ከሥራ የተገነጠለ ትኩረት የትም አንደርስም፡፡ ለመኖር ጭምር እንፈተናለን፡፡ ህልውናችንን አደጋ ውስጥ ይከተዋል፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሰው ከግለሰብ ጀምሮ እስከ መንግሥት ነገሮችን ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እሴት መጨመር እንደ ሀገር የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው ?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** እሴት መጨመር ማለት ከጥሬው ውጪ በጥራትና በተለየ መልኩ ምርትን አምርቶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በብዛት ከታዳጊ ሀገር ጥቅም ጋር ይያያዛል፡፡ ሀገራቱ ምርቶችን ሲያመርቱ እሴት ሳይጨምሩባቸው በመርከብ እየተጫኑ በርካሽ ዋጋ ወይም በነፃ በሚባል ዋጋ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ሲሉ ይሸጧቸዋል፡፡ ተጠቃሚዎቹ ጥሬ ዕቃዎቹን የሚረከቡት አካላት ናቸው፡፡

ስለዚህም ተጠቃሚ ለመሆን ጥሬ ዕቃዎቻችን ላይ እሴት መጨመር አለብን፡፡ ከዚህ አኳያም እሴት መጨመር ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

ከእነኝህ መካከልም የመጀመሪያው ለአምራቹ ገበሬ አንድ ምርት እሴት ተጨምሮበት ሲሸጥ የተሻለ ገቢ ያስገኛል፡፡ ሁለተኛ እሴት የመጨመር ሂደቱ የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ ለምሳሌ፡- የተወሰነ ምርት በትንሹ መጭመቅ እና ማጣራት ቢኖርበት መጭመቂያ ላይ የሚሠሩ ፤ መጭመቂያውን የሚጠብቁ ፤ የሚያጸዱ የተለያዩ ሰዎች የሥራ ዕድል ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ እሴት የተጨመረበት ምርት ከፍ ባለ ዋጋ ይሸጣል፡፡ ለምሳሌ፡- ሰሊጥ በኩንታል 12 ሺህ ብር የሚሸጥ ቢሆን እና ዘይቱን ጨምቆ እና አጣርቶ ቢሸጥ ከአንድ ኩንታል 10 ሊትር ዘይት ቢወጣ 10 ሊትሩ ዘይት ከ10 እጥፍ ባላነሰ ዋጋ ይሻጣል፡፡ በተጨማሪም የመጓጓዣውን ዋጋ ይቀንሳል፡፡ ሌላኛው እሴት ሲጨምር የሚጠቅመው ነገር በእሴት መጨመር ሂደት ውስጥ የምግብ ዕቃዎች ከሆኑ ይዘታቸው ይሻሻላል፡፡ ስለዚህ ለተጠቃሚው ራሱ የተሻለ የምግብ ይዘት ያለው ምርት ገበያ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡ የተጠቃሚውንም እርካታ እና ተጠቃሚነት ይጨምራልም፡፡

እሴት በጨመር ከውጭ ሀገር የምናስመጣቸውን ነገሮች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንድንተካም ያደርገናል። ለአብነት በተቋም ደረጃ እየሠራን ያለውን ነገር ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህም የጾም ማኪያቶ ከኖርማል ማኪያቶ ዋጋው ከእጥፍ በላይ ነው፡፡ ይሄን ከውጭ በብዙ ዶላር ከፍለን እናመጣዋለን፡፡ ነገር ግን በቀላሉ መሥራት የምንችለው ነው፡፡ እሴት መጨመር ወደ ውጭ ሀገር እስከመላክ የሚያደርስ ሥራ የሚሠራበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አትክልት እና ፍራፍሬን ማንሳት ይቻላል፡፡ ወደ ውጭ በጥሬው ጭምር በስፋት በማምረት ይላካል፡፡ ከዚያም አልፎ አሁን አሁን አቮካዶን ዘይቱን እየጨመቁ በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጡ አሉ፡ ፡ በዚህም የውጭ ምንዛሬ ወደ ሀገራችን እየገባ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ስለ ተቋማችሁ ሥራ ብዙ ሰዎች አይረዱም፡፡ እስኪ ትንሽ ይበሉን?**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ሥራዎች ያከናወነ ተቋም ነው፡፡ ለአብነት የእኔን ዘርፍ ብቻ ብትወስጂ እንደሀገር ብዙ ሥራዎች የተከናወኑበት ነው፡፡ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የእኛ ድርሻ ተደርጎ የተሰጠን በምርምር ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ማውጣት ነው። በሰዎች ስልጠናና አቅም ግንባታ እንዲሁም በመሠረተ ልማት ማበልጸግ ዙሪያ እንድንሠራ ኃላፊነት ተሰጥቶናል፡፡ ይህንንም በሚገባ እያከናወንን እንገኛለን፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የምርምር ሥራ ዋነኛ ትኩረት ተደርጎ ተሰጥቶናልና በምርምር ምርት እና አገልግሎቶችን እናወጣለን፡፡

የማመከር ሥራ እንሠራለን፡፡ ከዚህም በላይ በምርምር የወጡትን ምርቶች ሌሎች ጥቅም ላይ እንዲያውሏቸው ለማድረግና ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ እንዲገቡ ዕድል ለመስጠት የማስተዋወቅ ሥራ እንሠራለን፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ልክ ተቀብሎ ወደተግባር የሚገባ አካል እምብዛም ነው፡፡ ምክንያቱም በምርምር የተገኘው ምርት ከዚያም በኋላ ብዙ ልፋትን ይጠይቃል። ስለዚህም እንደመንግሥት የመተጋገዝ ሰንሰለቱን ካልዘረጋና ተቋማት እርስ በእርስ እንዲሠሩ ካላደረገ ተቋማችን የሚሠራቸው የምርምር ውጤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም፡፡ እናም መንግሥትም ሆነ የግሉ ዘርፍ በትብብር ለመሥራትና ሀገርን ለመለወጥ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን፡፡**

**ዶክተር ፋንታሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡



# ማህደረ ጤና

# የጉበት በሽታ፡- ዝምተኛው ገዳይ

አስናቀ ፀጋዬ

የጉበት በሽታ በዓይን በማይታዩ ተህዋስያን በተለይ ደግሞ ‹‹ሄፒታይተስ›› በሚባሉ ጥቃቅን ቫይረሶች ይከሰታል፡፡ የጉበት በሽታን ሊያስከትሉ የሚችሉት ቫይረሶች አምስት ቢሆኑም ዋናዎቹና የተለመዱት ግን ‹‹ሄፒታይተስ ቢ እና ሲ›› ናቸው፡፡ ይሁንና የጉበት በሽታ በሄፒታይተስ ቫይረስ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል፡፡ በተለይ በሽታው በተለያዩ መርዛማ መድኃኒቶችና ኬሚካሎች እንዲሁም ከመጠን በላይ አልኮል በመውሰድ የሚከሰትበት ዕድል ይኖራል። ከአምስቱ የሄፒታይተስ ቫይረሶች ውስጥ በአብዛኛው የረጅም ጊዜ የጉበት በሽታ ሊያመጡ የሚችሉት ‹‹ሄፒታይተስ ቢ እና ሲ›› ናቸው፡፡ በዓለምአቀፍ ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያም በአብዛኛው የሚታዩት እነዚሁ ቫይረሶች ናቸው፡፡

የጉበት በሽታ በዓለምአቀፍ ደረጃ፣ በአፍሪካና በኢትዮጵያ ከፍተኛ የጤና፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል፡፡ በተለይ ደግሞ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ስርጭቱ እየተስፋፋ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ጊዜ በዓለምአቀፍ ደረጃ በየቀኑ ከ8ሺ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በጉበት በሽታ ይጠቃሉ፡፡ ይህም ምን ያህል በሽታው እየተስፋፋና ስጋቱ እየጨመረ እንደመጣ ያመለክታል፡፡ በየአመቱ ደግሞ በዓለምአቀፍ ደረጃ ከ1 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን በዚሁ የጉበት በሽታ ምክንያት እንደሚያጡ መረጃዎቹ ያሳያሉ። ይህም በሽታው ምን ያህል በከፍተኛ ደረጃ የሰዎችን ሕይወት እየቀጠፈ እንዳለ ማሳያ ነው፡፡


የጉበት በሽታ ከኤች አይ ኤድስ ጋር ሲነፃፀር ዜጎችን የመጉዳት አቅሙ በጣም ከፍተኛ እንደሆነም ነው መረጃዎች የሚያሳዩት፡፡ ከዘጠኝ እጥፍ በላይ የዜጎችን ሕይወት የሚጎዳና የመተላለፍ አቅሙም፤ ስርጭቱም ከፍተኛ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራትና በደቡብ አሜሪካ የበሽታው ስርጭት ከፍተኛ እንደሆነና ስርጭቱም እየጨመረ እንደመጣ የዓለም ጤና ድርጅትና የተለያዩ አጋር ድርጅቶች የሚሠሯቸው ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

በኢትዮጵያም ከጉበት በሽታ ጋር በተያያዘ የተሠሩ ዝርዝር ያሉ ጥናቶች ባይኖሩም እ.ኤ.አ በ2017 በተጠና ጥናት መሠረት 9 ነጥብ 4 ከመቶ የሚሆኑ ዜጎች በሄፒታይተስ ቢ የተጠቁ መሆናቸውንና 3 ነጥብ 1 ከመቶ ያህሉ ደግሞ በሄፒታይተስ ሲ እንደተጠቁ ያመለክታል። ይህም በሽታው አንድ አስረኛ ያህል ስርጭት በሀገሪቱ እንዳለው ያሳያል፡፡ ትኩረት የሚሻ በሽታ እንደሆነም ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

በዚህም የተነሳ በሽታው ‹‹ዝምተኛው በካይ›› የሚል ተቀፅላ ስም ተሰጥቶታል፡፡ ይህም የሆነው አብዛኛው በዚህ በሽታ የተጠቃ ሰው ምንም ምልክት ሳያሳይ ለረጅም ጊዜ ስለሚቆይ ነው፡፡ ተጠቂው ሊድን ለማይችል የጉበትና የካንሰር በሽታ ተጋላጭ ከሆነ በኋላ ራሱን ሊያውቅ ይችላል፡፡ በርካታ ሰዎችም ለሌላ ምርመራ ሲሄዱ ነው ሄፒታይተስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ እንዳለ የሚያውቁት፡፡

ለሄፒታይተስ ቫይረስ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሄፒታይተስ ቫይረስ ተጠቅተው የጉበት በሽታ ካላቸው ሰዎች ጋር ረጅም ጊዜ አብረው የሚኖሩና ከታመሙ ሰዎች ከሚወጡ ደምና ሌሎችም ፈሳሾች ጋር ንክኪ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ በሽታ ከተጠቁ ሰዎች ጋር ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲኖርም በሽታው በቀላሉ የመተላለፍ ዕድል ይኖረዋል፡፡ በዚህ በሽታ የተጠቁ እናቶችም ወደ ልጆቻቸው ቫይረሱን የማስተላለፍ ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የጤና ባለሞያዎችም ለዚሁ በሽታ ተጋላጭ ናቸው፡፡ አደንዛዥ እፅ በመርፌ የሚጠቀሙ ሰዎችም ለጉበት በሽታ የመጋለጥ ዕድል አላቸው፡፡ ንፅህናቸው ያልተጠበቀ የስለት መሣሪያዎችን መጠቀምም ለበሽታው ያጋልጣል፡፡

የጉበት በሽታ ስርጭቱንና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የተለያዩ የመከላከያና የመቆጣጠሪያ መንገዶች እንዳሉ በሕክምና ባለሞያዎች ይገለፃል፡፡ እነዚህንም አውቆ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የጤና ባለሞያዎች ይመክራሉ፡፡ በተለይ ከታማሚዎች በኩል ያለውን ፈሳሾችና የደም ንክኪ ማስወገድና




መከላከያ ዘዴዎችን መጠቀም በዋናነት ያስፈልጋል። ጥንቃቄ የተሞላው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ በተለይ ደግሞ ጉበትን የሚጎዱ የተለያዩ ኬሚካሎችን፣ ምንነታቸው የማይታወቅ ሕገወጥ መድኃኒቶችን አለመጠቀምና ከልክ በላይ አልኮል መጠጣትን ማስወገድ ያስፈልጋል፤ ንፅህናቸው ያልተጠበቀ ስለታማ ነገሮችን አለመጠቀምም ይመከራል፡፡

ወይዘሮ ሰብለወንጌል አባተ የዓለም ጤና ድርጅት ተወካይ ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ የዓለም ጤና ድርጅት የበሽታውን ግዝፈት በመገንዘብ እ.ኤ.አ በ2030 በሄፒታይተስ ቫይረስ ምክንያት የሚመጡ የጉበት በሽታዎች በኅብረተሰቡ ላይ የሚፈጥሩትን የጤና አደጋ ለመቀነስ የተለያዩ ግቦችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ግቦች አብዛኛው ሰው በምርመራ ራሱን እንዲያውቅ፣ ቫይረሱ በውስጡ እንዳለበት ካወቀም በኋላ በቶሎ ወደጤና ተቋም ሄዶ ሕክምና እንዲያደርግና ከሄፒታይተስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጉበት በሽታዎችንና ያለ ዕድሜ የሚከሰት ሞትን ለመቀነስ የተቀመጡ ናቸው፡፡

እነዚህን ግቦች ኢትዮጵያም እንደሀገር ተቀብላ እየሠራችበት ትገኛለች፡፡ በዚሁ መሠረት እንደ ዓለም ጤና ድርጅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሠሩ ሥራዎች ወደሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ተቀይረው እንዲሠራባቸው እየተረደገ ይገኛል፡፡ የጉበት በሽታ መድኃኒቶች ውድ ከመሆናቸው አኳያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለታዳጊ ሀገሮች ዋጋቸው እንዴት መቀነስና መድረስ እንዳለባቸው የዓለም ጤና ድርጅት ከመድኃኒት አምራቾች ጋር ይሠራል፡፡

እንደ ተወካዩዋ ማብራሪያ፣ የዓለም ጤና ድርጅት የጉበት በሽታን ለመከላከል ካስቀመጣቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ ክትባት ሲሆን ይህም የጨቅላና የሕፃናት ክትባትን ያጠቃልላል፡፡ የሕፃናት የጉበት በሽታ ክትባት ወደሀገር ውስጥ ገብቶ መሥራት ከተጀመረ አስር አመት አልፎታል፡፡ ከ90 በመቶ በላይ ጥሩ ውጤት አምጥቷል። ነገር ግን የዓለም ጤና ድርጅት ይህን ክትባት ካቀረበ በኋላ የክትባቱን ውጤታማነት ይበልጥ ለማሳደግ ሕፃናት ወዲያው እንደተወለዱ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ቢከተቡ የሚል አዲስ መመሪያ አምጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የጉበት በሽታ ስርጭት አለባቸው በተባሉ ሞቃታማና ቀዝቃዛ አራት ወረዳዎች ላይ የአንድ አመት የክትባት ሙከራ ተካሂዷል፡፡ ይህም ሙከራ ውጤታማ መሆኑ በምዘና ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አኳያ ‹‹ሄፒታይተስ በርዝ ዶዝ›› የተሰኘውን ክትባት ለማስፋት ከዓለም ክትባት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ንግግሮች እየተካሄዱ ነው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወነች ነው፡፡ በቀጣዩ አንድ አመት ክትባቱ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሰጥ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

በሽታውን ከመከላከል አኳያ ጥሩ ጅምሮች አሉ። በፖሊሲ ደረጃም የሁለተኛው የጤናው ሴክተር ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ገብቷል፡፡ ራሱን የቻለ የአምስት አመት እቅድ አለው፡፡ ራሱን የቻለ የአምስት

> «በሽታውን ከመከላከል አኳያ ጥሩ ጅምሮች አሉ፡፡ በፖሊሲ ደረጃም የሁለተኛው የጤናው ሴክተር ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ገብቷል። ራሱን የቻለ የአምስት አመት እቅድ አለው፡፡ ራሱን የቻለ የአምስት አመት መመሪያም ተዘጋጅቶለታል። በዚሁ መሠረት በትንሽ ጤና ተቋማት ሲሰጥ የነበረው የጉበት በሽታ ሕክምና አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ ወደ ዘጠና ጤና ተቋማት አድጓል፡፡ ሕክምናው በሁሉም ክልሎች እንዲሰጥም ተመሳሳይ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይ ደግሞ አሁን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በማጠናከር የሕክምና አገልግሎቱ እንዲያድግ ሥራዎች ይሠራሉ»

አመት መመሪያም ተዘጋጅቶለታል፡፡ በዚሁ መሠረት በትንሽ ጤና ተቋማት ሲሰጥ የነበረው የጉበት በሽታ ሕክምና አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ ወደ ዘጠና ጤና ተቋማት አድጓል፡፡ ሕክምናው በሁሉም ክልሎች እንዲሰጥም ተመሳሳይ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በቀጣይ ደግሞ አሁን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በማጠናከር የሕክምና አገልግሎቱ እንዲያድግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ እንደሚናገሩት፣ በኢትዮጵያ በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ሲሆኑ፣ እነዚህ ሥራዎች በሚዲያዎች በኩል፣ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ በማካተትና በጤና ተቋማት የተለያዩ የተግባቦት ሥራዎች ውስጥ በማስገባት ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ሥራው በቂ ነው ባይባልም በዚህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አብዛኛዎቹ ዜጎች ጋር መድረስ ተችሏል፡፡

በቀጣይም ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ሚዲያዎችም የበሽታውን መተላለፊያ መንገዶችን በተመለከተና መከላከያ ዘዴዎቹ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራውን በአግባቡ ሊሠሩ ይገባል፡፡ በተለይ ኅብረተሰቡ ከታመመ በኋላ ለሕክምና ከፍተኛ ወጪ የሚያወጣ በመሆኑና ሕክምናውንም በቀላሉ ስለማያገኝ በሽታውን አስቀድሞ የመከላከሉን ሥራ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ምርመራና የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን ማጠናከር ይገባል፡፡ በተለይ በግልም ሆነ በመንግሥት ጤና ተቋማት ምርመራ ማድረግ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ነገር ግን አሁንም ይህ በቂ ባለመሆኑ በየጊዜው ምርመራውን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ለጉበት በሽታ ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰቡ በየአመቱ አንዴና ሁለቴ አጠቃላይ የጤና ምርመራ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተለይ ደግሞ የበሽታውን ምልክት ሲያይ በአፋጣኝ ወደጤና ተቋም ሄዶ መመርመር ይኖርበታል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች የጉበት በሽታ እንዳለባቸው የሚያውቁት ለሌላ ሕክምና ሲመጡ ነው። ከዚህ አንፃር በተለይ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች በየጊዜው ምርመራ ማድረግ አለባቸው፡፡ በሽታው ሳይስፋፋና ጉበት ሳይጎዳ ከተገኘ ሕክምናው በቀላሉ ሊሰጥና ወደ ካንሰር ሳይቀየር የመዳን አቅሙም ከፍተኛ ስለሆነ እያንዳንዱ ሰው ምርመራ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንደሚሉት፣ የጉበት በሽታ መድኃኒት በቀላሉ የሚገኝ አይደለም፡፡ የመድኃኒት እጥረቱ የሚታየው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ጭምር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የተወሰኑ መድኃኒቶች ብቻ ናቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት፡፡ የጤና ሚኒስቴርም የተወሰኑ መድኃኒቶችን ገዝቶ ዜጎች መድኃኒቶቹን እንዲያገኙ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ይህ በጣም ያንሳል፡፡

ስለዚህ በቀጣይ ጤና ሚኒስቴር በግሉ የሚሠራው ሥራ እንዳለ ሆኖ የተለያዩ የግልና የመንግሥት ተቋማት በራሳቸው በጀት የጉበት በሽታ መድኃኒቶችን መግዛትና ማስገባት ብሎም ለዜጎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመድኃኒቶቹን ዋጋ ቀንሶ ለዜጎች ማቅረብ ደግሞ ከጤና ሚኒስቴር ይጠበቃል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

በሽታውን ከመከላከል ጋር የተያያዘ ቢሆንም የክትባት ፕሮግራሞችም አሉ፡፡ እ.ኤ.አ ከ2007 ጀምሮ ከመደበኛዎቹ የክትባት መርሃ ግብሮች ጋር በማያያዝ የጉበት በሽታ ክትባት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ጨቅላ ሕፃናትም በ45 ቀናቸው ክትባቱን ይወስዳሉ፡፡ ክትባቱን በወሰዱት ላይ የበሽታው ስርጭት ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ክትባቱ በጣም ጠቃሚ መሆኑ በጥናትም ጭምር የተረጋገጠ እንደመሆኑ ይህን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ እናቶችም ልጆቻቸው ይህን ክትባት እንዲወስዱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በቀጣይ ‹‹ሄፒታይተስ በርዝ ዶዝ›› የተሰኘውና ሕፃናት ገና እንደተወለዱ የሚወስዱት ክትባት አለ። ይህም ክትባት በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ እየተሞከረ ይገኛል፡፡ አዋጭነትና ውጤታማነቱ ጥሩ እንደሆነም ታይቷል፡፡ ይህን ክትባት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ለማስፋት በጀት ተይዞ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ይህም የጉበት በሽታ እንዳይስፋፋና ስርጭቱን ለመቀነስ ከሚያስችሉ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ የጤና ባለሞያዎችም ለዚህ በሽታ ተጋላጭ በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ክትባት እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡ ይህንንም ለማዳረስ በቀጣይ ጥረት ይደረጋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## «ፍርሃት የእኛ ጌታ!»

**ፈራን! «ለምን ፈራችሁ አትበሉን»፤**

የምናከብረው የሥነ ጽሑፍ አርአያችንና የመምህራችን የሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን «እሳት ወይ አበባ» የግጥም መድበል (1966 ዓ.ም) ለእኔና ለዘመነ አቻዎቼ ብቻ ሳይሆን በተከታዮቻችንም ዘንድ ቢሆን በርካታ የእኛነታችንን ጉዳዮች ለመፈተሽ ሲፈለግ ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡ እኔውም ብሆን በዚህ አንጋፋ ጋዜጣ ላይ በተወዳጀሁበት በሦስት ዐሥርት ተኩል ዓመታት ውስጥ ባስነበብኳቸው በሺህ በሚቆጠሩ አርቲክሎቼ ውስጥ ከዚህቺው ዕድሜ ጠገብ ተጠቃሽ መድበል ላይ ምን ያህል ጊዜያት ለበጎነት የሚጠቀሱ የሃሳብ ፍሞችን እንደ ጫርኩና አእምሮ የሚያነቁና በአበባ የሚመሰሉ አዳዲስ «እምቡጥ» ምልከታዎችን እንዳጋራሁ በርግጡ የቁጥሩን ልክ አላውቀውም፡፡

በተለይም ሎሬቱ ታትሞ ባላገኘነው አንድ ሥራው ውስጥ ረቂቅ የፍርሃት ባህርይን የገለጸበት ቋንቋውም ሆነ ምልከታው ለወቅታዊ እህህታችን መገለጫነት ብቻ ሳይሆን ዘመንንና የጊዜን ውቂያኖስ እያቆራረጠ በትውልዶች ቅብብሎሽ ውስጥም ሳይቀር ስሜትን እየበረበረ «ፍርሃትን» ገሃድ የመግለጥ አቅሙ ከፍ ያለ አንድ ግጥም እናስታውሳለን፡፡ ግጥሙ ትናንት የተነበበ፣ ዛሬ የተጠቀሰ ብቻ ሳይሆን ለነገውም ቢሆን ሰዋዊ ስንቃችን እንደሆነ የሚቀጥል ዓይነት ስለሆነ ዕድሜው እንደ ማቱሳላ የረዘመ ነው፡፡ ይህ «ፈራን» የሚለው ግጥሙ እየሞቅናት ባለነው የዛሬዋ ጀንበር የወረሰንን ወቅታዊ የፍርሃት ስሜት በገሃድ የሚገልጽ ስለመሰለን እነሆ ሙሉውን የግጥሙን ይዘት ከእነ ወዙና ላህይው እንዲህ እናስታውሳለን፡፡

**«ፈራን» - ፍቅርን ፈራን፣መቀራረብ ፈራን፣**
**እንዳልተሳመድን እንዳልተዋለድን፣**
**ፈርተን መዋደድን፤ ጉርብትናን ናድን፣**
**እኛነትን ትተን እኔነትን ስመድን፡፡**

**«ፈራን» - ፍቅርን ፈራን፤ ጥላቻን ሠራን፣ ብቸኝነትን ጠራን፣**
**በጋራ ቤታችን አጥር ድንበር ሠራን፡፡**

**«ናቅን» - በልዩነት ደምቀን ይበጅን ይመስል በአልህ ተናነቅን፡፡**
**«ናቅን» - መቻቻልን ናቅን ለፀብ ተሟሟቅን፣**
**ለአመጽ በርትተን ለሰላም ወደቅን፣**
**ሀገር ስትቃጠል ከዳር ሆነን ሞቅን፡፡**

**«ጠላን» - መወያየት ጠላን፤ መነጋገር ጠላን፣**
**መደማመጥ ጠፍቶ፤ መነቋቆር ሰፍቶ፣ መናናቅ በርክቶ፤**
**መመካከርን ስንረሳ፤ መከባበርን ስንረሳ፣**
**እጆችን በወንድማችን ላይ ዱላ አነሳ፤**
**የቃየል ምቀኝነት በልባችን ነግሳ፡፡**

**«ራቅን» - የተስፋችን ሻማ ተለኩሶ፣**
**ወጋገኑ መታየት ሲጀምር፤ አድማሱን ጥሶ፣**
**እኛ ግን ራቅን ብሩህ ነገን ናቅን፣**
**ከዛሬ ተጣብቀን ትናንትን ናፈቅን፡፡**

ሎሬቱ ይህን የግጥም አዝመራ በምን ስሜት ውስጥ ሆኖ እንዳዘመረውና መቼ እንደጻፈው አቅጩን ለመንገር ይህ አምደኛ መረጃ የለውም፡፡ ጥቅል አስተያየት ለመስጠት ካስፈለገ ግን ደራሲው በቃላት አሳክቶ ያደረሰን ይህ «ውብ ግጥም» ትናንትን ብቻ ሳይሆን በዓመታት ላይ እየተረማመደ ነገንና ተነገወዲያንም የመግለጽ አቅሙ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን ቀደም ሲል ስለገለጽን የዓመት ዕድሜ ተገድቦለትና ተወስኖለት በዚህ ዓመት ተጻፈ ባይባል ይመረጣል፡፡ ለምን ቢሉ ይህ ከነፍስ የመነጨ «እሪታና ጩኸት» ሰዎች በምድር ላይ እስከኖሩ ድረስ አብሮ የሚከርም ስለሆነ ነው፡፡ «በዚህ ዘመን ለዚህ ጉዳይ ተጻፈ» ብሎ መደምደሙ እጅግም ተመራጭ የማይሆነውም ስለዚሁ ምክንያት ነው፡፡

ስለዚህ «ብዙ ወጀቦች ስለከበቡን» ለምን ፈራችሁ ተብለን ከቶውንም ልንጠየቅ ተገቢም አግባብም አይደለም፡፡ በሀገሬ ምድር የማያስፈራው «ፍርሃትን ራሱን እንዳንፈራ ሆነን መፈጠራችን» ሳይሆን አይቀርም፡፡ «ፍርሃት እንደምን የእኛ ጌታ ሊሆን ቻለ?» ተብዬ ብሞገት ደግሜ የምከራከረው ከዚያው ከሎሬቱ «የእሳት ወይ አበባ» የግጥም መድበል ኩልል ያለና «ማነው…‹ምንትስ› » በሚል ርእስ ከተለየው የጥበብ ምንጭ በመጥቀስ ይሆናል፡፡

**«ያው መቼም እኔም እንደ ሰው፣**
**አንዳንዴ፣ አንዳንዴ ብቻ ሕሊናዬን እውነት ሲያምረው፣**
**ሰብሰብ ብዬ የማስበው፣**
**ተጨብጬ የማብሳሳው፣**
**ያው መቼም እኔም እንደ ሰው፣**
**የሐቅ ርሃብ ነፍሴን ሲያከው፣**
**ልቤ ልቤን ሲሞግተው፣**
**እውነትስ ምንትስ ማነው? እያልኩ እጠይቃለሁ።**
**እስቲ እንጠያየቅ እላለሁ፡፡**
**ዳኝነት የእግዜር ነውና እስቲ እንፋረድ እላለሁ።»**

ቀጥለን የምንዘልቀው ወደ መሟገቱ ይሆናል።

**መሟገቻ አንድ፡-** «ሀገራዊ ችግሮቻችንን በውይይት፣ በመመካከርና በስክነት ስለምን መፍታት ተሳነን?» ክርክሩ በአደባባይና በይፋ እንዲካሄድ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ በመከራከሪያ ጭብጡ ላይ በሩን ዘግቶ ከልቦናው ጋር «ቢሟገትበት» የጸሐፊው ምርጫ ነው፡፡

**መሟገቻውን እናብራራው፡-** መቼም የግጭትና የጦርነት ትርፉ ማሸነፍና መሸነፍ ሳይሆን «መሸናነፍ» መሆኑን የራሳችንም ሆኑ የዓለም የታሪክ መዛግብት እውነታውን ፍንትው አድርገው ያሳዩናል፡፡ በትምህርት ሥርዓታችን ውስጥ የዓለም ታሪክ፣ የአፍሪካ ታሪክና የኢትዮጵያ ታሪክ እያልን «የኮርስ ስም ሰጥተን» የምንሸመድዳቸው የታላቋ ምድራችን የትናንት ዜና መዋዕሎች በሙሉ የሚያረጋግጡልን በጀግንነት የሚያስጨበጭበው የሰላም ሰው ሆኖ መከራን መሻገር እንጂ «የደም መስዋዕትነት አስከፍሎ»ማሸነፍ ትርፉ ማቅ ለብሶ በጸጸት መቀጣት እንደሆነ ነው፡፡

> **በትምህርት ሥርዓታችን ውስጥ የዓለም ታሪክ፣ የአፍሪካ ታሪክና የኢትዮጵያ ታሪክ እያልን «የኮርስ ስም ሰጥተን» የምንሸመድዳቸው የታላቋ ምድራችን የትናንት ዜና መዋዕሎች በሙሉ የሚያረጋግጡልን በጀግንነት የሚያስጨበጭበው የሰላም ሰው ሆኖ መከራን መሻገር እንጂ «የደም መስዋዕትነት አስከፍሎ»ማሸነፍ ትርፉ ማቅ ለብሶ በጸጸት መቀጣት እንደሆነ ነው**

እንኳንስ በደካማ የሰው ልጆች ብኩን ዓለም ቀርቶ በሰማይ ሠራዊት መካከል እንኳን ጠብና ግጭት እንደሚካሄድ የክርስቲያኖች ቅዱስ መጽሐፍ በሚገባ ይተርክልናል፡፡ በሰው ልጆች መካከልም ጠብና ክርክር መነሳቱ ከቶውንም የሚቀር አይደለም። በትናንቷም ሆነ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል ጊዜ እርስ በርስ ግጭትና መጠፋፋት እንደተደረገ ብንተርከው ስለሚሰለች አስታውሶ ብቻ ማለፉ ይሻላል፡፡ የዛሬው ሀገራዊ ችግራችን በርዶ ስለምን ሰላምን መምረጥ ተሳነን? ገድሎ ባለድል ከመሆን ለሰላም ተሸንፎ መዘመሩስ አይሻልም? አንዱ የፍርሃታችን ምንጭ ከሰላም ጋር መፈራራታችን ነው፡፡ ስለዚህ «ፈራን!» ብለን «በፍርሃታችን ብንርድ ይፈረድብናል?»

**መሟገቻ ሁለት፡-** ሙስና ይሉት ክፉ የሕዝብና የሀገር ደዌ በአደባባይ ነግሶ ዱታ ነኝ እያለ ሕዝብ ሲያስለቅስ ስለምን ይህንን ክፉ ነቀርሳ የሚነቅል «ዋግምት» ሊጠፋ ቻለ? እየተፈራራንና «ካብ ለካብ እየተያየን» እስከ መቼ እንዘልቀዋለን? ሀገራችንን ማዲያት ያለበሰው ይህ ክፉ ሥራይ እስከ መቼ እንደ መዥገር ተጣብቆብን እየመጠጠን ይኖራል፡፡ ስለዚህም «ሀገር እንደ ሀገር፤ እኛም ዜጎች እንደ ዜጋ» የመኖር ዋስትናችን ስለሚያጠራጥረን ፈርተናል፡፡ ስለምን ፈራችሁ የሚለን ራሱ ፈሪ ነው፡፡

**መሟገቻ ሦስት፡-** ላባችንን ጠብ አድርገን እንዳቅማችን የዕለት ጉሮሯችንን የምንደፍንበት «የደም ወዛችን - ደሞዛችን» እንኳን ኑሯችንን አሸንፎ በልተን ልናድር ቀርቶ እስከነአካቴው ጭንቀት ላይ ወድቀን «ወየው ለነገ!» እያልን በመቃተት ብቻ ደማችን ቀጥኖ እስትንፋሳችን ልትወጣ ጫፍ ላይ ደርሳለች፡፡ በጡንቻችን የምንፋለምበትን ወላንሶ እርግፍ አድርገን በመተው የግብርና ማሳችን ላይ ጉልበታችንን በማዋል ለማዕዳችን ሙላት መጨነቅ ሲገባን ስለምን መጨካከንን መርጠን ጦር እንደምንወራወር አልገባንም፡፡

የገባቸው ካሉ ያስረዱን፤ ወይንም የነገውን ተስፋችንን በእጃቸው ላይ ያኖርነው «እንደራሴዎቻችን» እንደራሳቸው ሳይሆን እንደራሳችን ሆነው እውነቱን ይግለጹልን፡፡ ዛሬ ያላረሰ ገበሬ ነገ ምኑን አቅርቦልን ነፍሳችንንና ነፍሱን ይታደጋል? ስለዚህም ነገን ስናስብ ፈርተናል፤ ለምን ፈራችሁ ተብለን ብንጠየቅ መልስ የለንም። መልስ የማንሰጠው መልሱ ጠፍቶን ሳይሆን «ጌታው ፍርሃት» እያንዘፈዘፈን ቃላት እንዳናወጣ ስለሚያንዘረዝረን ብቻ ነው፡፡

**መሟገቻ አራት፡-** ሳንወድ የተገኘንበትን፣ ሳንመርጥ የተወለድንበት ምንጫችንን ብቻ «ለእኔ ብቻ» በሚል አጥር ከልለን የሌሎችን «ምንጭ» እያንቦጫረቅን ማደፍረሱ ጦሱ የት አድርሶ የት እንደሚጥለን ስናስብ እንደነግጣለን፣ «ወዬው ለነጋችን!» እያልንም እንጨነቃለን፡፡ እስከ ዛሬ የተጓዝንበትን ኮረኮንች ጎዳና ምርጫን አድርገን ወዳሰብነው መዳረሻ ስለመቃረባችንም ጥርጥር ገብቶናል፡፡ ስለዚህም «ፈርተናል፤ ምን ያስፈራችኋል!» ብንባልም ተብለን ብንገሰጽም የመስሚያ ጆሯችን ስለተደፈነ ማንንም አንሰማም፡፡

**መሟገቻ አምስት፡-** እንደ ፈረሰኛ ጎርፍ ድንገት ደርሶብን ላጥለቀለቀን ዘመነ ሉላዊነት ቀድመን የሥነ ልቦና ዝግጅት በማድረግ «ታጥቀን ስላልቆየነው» እነሆ እንደ ሌባ ከተፍ ብሎ እጅ በማስጠት ምርኮኛ አድርጎናል፡፡ «እህል ውሃችን፣ የጠብና የመነታረኪያ አጀንዳችን፣ የመፋዘዣ ማደንዘዣ፣ የልጆቻችን ማኮላሻ፣ የግንኙነታችን ፀር፣ የንጽህናችን ማርከሻ ወዘተ.» እየሆነ ያለውን ማኅበራዊ ሚዲያ ያለመፍራት እንደምን ይቻላል?» እንድንካድመው ከማረከን እኮ ቆይቷል፡፡ ስለዚህም ነጋችንን ስናልም ከፊታችን ያለው ጨለማ ስለሚያስደነግጠን ፈርተናል - ለምን ፈራችሁ ተብለን ልንወቀስም ሆነ ልንከሰስ አይገባም።

**መሟገቻ ስድስት፡-** የሃይማኖት ክብር ሚዛኑ ተዛብቶ፣ የአባቶች ምክር ሰሚ ጆሮ አጥቶ፣ የአረጋዊነት ሽበት አቅሙ ዝሎ ስንመለከት «ሽማግሌ ይገላግላል፤ የተጠቃ አቤት ይላል» የሚለው ጥንታዊ ብሂል ዋጋ እንዳጣ ገብቶን ፈርተናል፡፡ ስለምን ፈራችሁ ባንባል ደስ ይለናል፡፡

«ሽምግልናን ከኡኡታ በፊት» ባለማስቀደማችን «ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ፣ የእምቧይ ካብ» ሲሆን እያስተዋልን እንኳን ወደ ቀልባችን ለመመለስ ያለመጨከናችን ለተጠናወተን አዚም ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡ ስለዚህም አስገባሪያችን «ፍርሃት የእኛ ጌታ» እጅ ተወርች ጠፍሮ ወህኒው ውስጥ ስለከተተን ኡኡታችንም ሆነ ተማጽኗችንን ሰምቶ የሚታደገን የክፉ ቀን አለሁ ባይ አላገኘንም፡፡ ስለዚህ ፈራን፤ ፈርተንም ተሸነፍን፡፡

**መሟገቻ ሰባት፡-** የከበቡን ጠላቶቻችን እርስ በእርሳችን «ጥለን ስንወድቅ» እያዩ ደስ በመሰኘት አታሞ በመደለቅ ይፍነከነካሉ፡፡ ሰይፍ በመሞሻለቅ ተሳዳጅና አሳዳጅ ሆነን አንዳችን አንዳችንን ስናባርር እነዚያው ወደረኞቻችን እየተሳለቁ ያሾፉብናል፡፡ ክብራችን ወድቆ፣ አንድነታችን ላልቶ ሲያስተውሉም ገፍትረው ሊጥሉን ቀን ከሌት ያደባሉ፡፡ ስለዚህ ፈርተናል - «ለምን ፈራችሁ» ተብለን ባንገሰጽ መልካም ነው፡፡ እንደውም ቁስላችን ላይ ጨው የመነስነስ ያህል ስለሚቆጠቁጠን ይከፋናል፡፡

እህህታችን ስለማያልቅ ለማጠቃለያ እንዲረዳን ከሎሬታችን የግጥም ማዕድ የመጨረሻውን የስንኞች ጉርሻ እንዋስ፡፡

**«ይቅር ብቻ አንናገርም፤ ለውይይት አልታደልንም፣**
**እንዲያው ዝም፣ እንዲያው ዝም…ዝም፡፡**
**አበባ አንሆን ወይ እሳት፣ ተጠምደን በቅዝት ቅጣት፣**
**ሰመመን ባጫረው መዓት፤ አድሚያችንን እንዳማጥናት፣**
**እሳት አንሆን ወይ አበባ፤ በሐቅ እንቅ ስንባባ፣**
**ባከነች እኛነታችን እየቃተትን ስናነባ፡፡**
**ሳንፈጠር በሞትንባት፤ ሳናብብ በረገፍንባት፣**
**ሳንጠና ባረጀንባት፤**
**አበባ ወይንም እሳት መሆኑን ብቻ አጣንባት፡፡»**

አይ ኢትዮጵያ! ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም በጎ ፈቃድ፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

## የተሰረቀው ስልክ እና መዘዙ

**ሶሎሞን በየነ**

የተሻለ ሥራ፣ ትምህርት፣ ኑሮ፣ ህክምና፣ ... ወዘተ ፍለጋ በአራቱም አቅጣጫ ወደ መዲናዋ ሰዎች ይጎርፋሉ። በዚህ የተነሳ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ክፉና ደጉን በውል ያልለዩ ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ታዳጊዎችን ጭምር በከተማዋ ጎዳናዎች ማየት የተለመደ ነው። እነዚህ ታዳጊዎች የሚጠጉበት ዘመድ፣ አይዟችሁ የሚላቸው ወገን ከአጠገባቸው ባለመኖሩ ውሎ አዳራቸው ጎዳና ላይ ነው። ከጎዳና ሕይወት ወጥተው የተሻለ ኑሮ ለመምራት የቀን ሥራ በመሥራት፣ ጫማ በመጥረግ፣ ቆሎ፣ ማስቲካ፣ ሎተሪ ... ወዘተ እያዞሩ በመሸጥ፣ የሚዛን አገልግሎት መስጠት የመሳሰሉ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው እራሳቸውን ለመቀየር ሲታትሩ ይስተዋላሉ።

በአንጻሩ በልጅነታቸው ከቤተሰብ ተለይተው ጎዳና ላይ የወደቁ አብዛኞቹ ታዳጊዎች ገና በለጋ እድሜያቸው የሱስ ምርኮኛ ሆነው፣ ነገ ላይ ሠርቶ የተሻለ ሕይወት የመምራት ህልም ሆነ ሞራል አጥተው ይታያሉ። ታዳጊዎቹ ተሯሩጠው ሠርተው በሚያተርፉበት የወጣትነት እድሜያቸው በተለይ በከተማዋ የትራፊክ መብራት ያለባቸው አካባቢዎች ተሸከርካሪዎች መብራት ይዟቸው ሲቆሙ እጃቸውን ለምጽዋት ሲዘረጉ በየጎዳናው ማየት የተለመደ ነው። ከዚህ ባለፈም ሱሳቸውን የሚያስታግሱበት ገንዘብ በቀላሉ ለማግኘት ሲሉ የተለያየ የወንጀል አዘቅት ውስጥ ተዘፍቀው የሚዳክሩም ብዙዎች ናቸው።

በተመሳሳይ ወጣት ተስፋዬ መሃመድ (በቅጽል ስሙ ፋራው) እና አማኑኤል መሰለ (በቅጽል ስሙ ባሪያው) ገና በታዳጊነት እድሜያቸው ከደቡብ ክልል የተሻለ ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ። እንደመጡም የሚያርፉበት ዘመድ ስለሌላቸው ኑሯቸውን ጎዳና ላይ አድርገው በወዛደርነትና ያገኙትን የቀን ሥራ በመሥራት ሕይወታቸውን መግፋት ጀመሩ። እንዲህ ዓመታትን በጎዳና ሕይወት ያሳለፉት ወጣቶቹ፤ ቀስ በቀስ ሱስ ተለማመዱ። ይህኔ የቀን ሥራ ሠርተው የሚያገኙት ገቢ ጉሮሮን ከመሸፈን አልፎ ሱሳቸውን ሊያረካላቸው አልቻለም። በዚህም ሳይወጡ፣ ሳይወርዱ በቀላሉ ገንዘብ አግኝተው ሕይወታቸውን የሚቀይሩበት እንዲሁም ሱሳቸውን የሚያረኩበት ሌብነት ውስጥ ለመግባት ይወስናሉ።

ይህን ከጀመሩ በኋላ ሌሎች ጓደኞቻቸው በጠዋት ተነስተው ወደ ሥራ ሲያመሩ፤ እነሱ ግን ተኝተው ያረፍዳሉ። ከመኝታቸው አርፍደው ከተነሱ በኋለ ቀን ላይ ጫት ሲቅሙና ሲጠጡ ይውላሉ። ማታ ማታ የሌብነት ወንጀል ለመፈጸም ይሠማራሉ። እንዲህ የሰዎችን ላብ እየነጠቁና የሰው ደም እያፈሰሱ ባገኙት ገንዘብ ዛሬን ሱሳቸውን አርክተው፣ ያማራቸውን በልተው፣ ጠጥተው ተደስተው ይውላሉ። ነገን አያስቡም። ምን ይገጥመናል? ምን ላይ እንወድቃለን? ብለው አይጨነቁም።

እንዲህ እንደወትሮው ሁሉ ጓደኛማቾቹ ሦስት ሆነው (ተስፋዬ፣ አማኑኤል እና በረከት) በቀን 15/06/2011 ዓ.ም የሌብነት ወንጀል ለመፈጸም በማሰብ ቀን ጫት ሲቅሙ፣ ሲያጨሱ፣ ሲጠጡ ውለዋል። በዚሁ ዕለት ማታ በፕላስቲክ የውሃ መያዣ (ሀይላንድ) አረቄ ገዝተው ይዘው እየጠጡ የሌብነት ወንጀል ለመፈጸም በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ጀሞ አንድ የጋራ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ገብተው ይዘዋወራሉ።

ከምሽቱ በግምት ሶስት ሰዓት ከ15 ደቂቃ አካባቢ ሲሆን፤ እሰይ ገ/ሕይወት የተባለ ግለሰብ ብቻውን ስልክ እያወራ ከዋናው አስፓልት ወደ ጀሞ የጋራ መኖሪያ ቤት አንደኛ በር በኩል እየሄደ ይመለከቱታል። ከሶስቱ ጓደኛማቾች አንደኛው ተስፋዬ የተባለው ቀስ ብሎ መንገደኛ መስሎ ወደ ግለሰቡ ተጠግቶ በጠረባ ሲመታው የእግረኛ መንገድ ጠርዝ ላይ ይወድቃል። ይህኔ ሰውየው ለብቻ፣ ስልኩ ለብቻ ይወድቃል። ሰውየው እያወራበት የነበረውን ቴክኖ ተች እስክሪን የእጅ ስልክ አማኑኤል እንዳነሳው፤ ሰው ሲመጣባቸው ሶስቱ ጓደኛማቾች ስልኩን ይዘው በተለያየ አቅጣጫ እሮጠው ይሠወራሉ።

እግር ጥሏቸው በአካባቢው የደረሱ ሰዎችም "እዚህ አካባቢ ሰው ወድቋል" ብለው ጀሞ አንድ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ያመለክታሉ። በወቅቱ ተረኛ የነበረው ፖሊስም ወደ ስፍራው አቅንቶ ተጠግቶ ሲመለከት ፈርጠም ያለ፣ የሱፍ ልብስ የለበሰ ሰው በፊት ለፊቱ በአፉ ተደፍቶ ወድቆ፤ በጀርባው፣ በአፍና በአፍንጫው ከፍተኛ ደም እየፈሰሰው ሕይወቱ አልፎ ይመለከታል። ፖሊስም በወቅቱ በቅርብ እርቀት የነበሩ የተከፈቱ የሽቀጣ ሸቀጥ ሱቆች ባለቤቶችን ስለሁኔታው እንዲያስረዱት ቢጠይቅም ይሄነው የሚል ፍንጭ ያጣል።



በኋላም በአካባቢው የተሰበሰቡ ሲቪል ሰዎች "የሟች ኪስ ውስጥ መታወቂያ ካለ ለቅርብ ተጠሪው እንደውል" ብለው አንድ ሰው ከሟች ኪስ ዋሌት ቦርሳ አውጥቶ ለቅርብ ተጠሪው "እሰይ እንደዚህ ያለአካባቢ ታሞ ወድቋል" ብሎ በስልክ ደውሎ ይነግራል። ሟች የቅርብ ተጠሪዬ ብሎ መታወቂያው ላይ አስመዝግቦ የነበረው የባለቤቱ የወይዘሮ እሌኒ ከፍቶ ስልክ ቁጥር ነበር። ወይዘሮ እሌኒም በስልክ ተደውሎ ባለቤቷ ታሞ ወድቋል ተብሎ የተነገራት ቦታ በራ ደረሰች። እንደዋዛ የልጆቿ አባት አውላላ አስፓልት ላይ ወድቆ ሕይወቱ አልፎ ስታገኝ፣ ቦታ አልበቃት ብሎ መሬት ላይ እየተንከባለለች ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ልክ ሰውን ከእንቅልፍ እንደሚቀሰቅስ በድኑን በእጇ እየነካች በስሙ ብትጠራ አቤት የሚላት የለም። ባለቤቷ ላይመለስ አሸልቧል። በመጨረሻም የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አምቡላንስ መጥቶ አስከሬኑን ከስፍራው አንስቶ ለምርመራ ይዞ ይሄዳል።

### ባልንጀራአማቾቹ ወዴት ተሰወሩ

ባልንጀራአማቾቹ ይህንን ወንጀል ሲፈጽሙ ሰው መጥቶባቸው በየፊናቸው ተበታትነው ነበር። በኋላ ከየአቅጣጫቸው ወጥተው ጀሞ 67 የአውቶብስ ማዞሪያ አካባቢ ሶስቱም ጓደኛማቾች ተገናኝተው በእግራቸው ወደ ዘነበወርቅ አካባቢ አመሩ። በዚያም ሁሌ ወደ ሚጠጡበት ታዬ ግሮሰሪ ቤት ጎራ ብለው ቢራ አዘው መጠጣት ጀመሩ። አማኑኤል የተባለው ከሟች የቀማውን ስልክ አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ እየጠጣ እያለ፤ የግሮሰሪውን ባለቤት አቶ ታዬ ለምለምን ጠርቶ "ይህንን ስልክ ትገዛለህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። የግሮሰሪው ባለቤትም ስልኩን አገላብጦ ካየ በኋላ "አልገዛም" ብሎ መልሶ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጣል።

አማኑኤልና የግሮሰሪው ባለቤት እንዲህ እየተነጋገሩ እያለ በዚህ መሀል ተስፋዬ ከተቀመጠበት ተነስቶ እየጠጡበት ካለው ግሮሰሪ ጎን ወደ ሚገኘው በላይ ግሮሰሪ በመሄድ አንዲት ሴተኛ አዳሪ ይዞ ይመጣል። እሷም ከነሱ ጋር ቁጭ ብላ ቢራ አዛ አንድ ቢራ ከጠጣች በኋላ ተነስታ ቀድማ ወደ ነበረችበት በላይ ግሮሰሪ አመራች። ይህኔ ተስፋዬ ሴተኛ አዳሪዋን እግር በእግር ተከታትሏት ወደ በላይ ግሮሰሪ ይሄዳል። በዚያ ሲጠጣ ከነበረ አንድ ግለሰብ ጋር በሴቷ የተነሳ ተጣልቶ ሰውየውን በቢራ ጠርሙስ ፈንክቶ ወደ ታዬ ግሮሰሪ ይመለሳል። ተስፋዬን ብዛት ያላቸው ሰዎች ተከታትለውት ታዬ ግሮሰሪ ውስጥ ገብተው ሊመቱት ሲሉ፤ የግሮሰሪው ባለቤት "አትመቱትም፣ ለሕግ አሳልፌ ነው የምሰጠው" ብሎ እንዳይመቱት ተከላከለለት።

የግሮሰሪው ባለቤት ታዬ ፀቡን ለማብረድና ሰዎቹን ለመገላገል እንዲያመቻው ሲል በእጁ ቆጥሮ የያዘውን አንድ ሺ ስድስት መቶ (1,600) ብር ሶስቱ ጓደኛማቾች ተቀምጠው ይጠጡበት የነበረው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ለመገላገል ከግሮሰሪው ወጥቶ ነበር። ፖሊስም ተደውሎለት በቦታው ላይ እንደደረሰ ተስፋዬና ተጎጂውን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዞ ይሄዳል። ይህኔ ታዬ ወደ ቤቱ ገብቶ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ገንዘብ ለማንሳት ሲሄድ ብሩ ካስቀመጠበት ቦታ የለም። ነገር ግን "ትገዛዋለህ ወይ?" ብለው ያሳዩት ስልክ እዛው ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል። አማኑኤልም ከተቀመጠበት ስላልተነሳ "ብሩስ?" ብሎ አቶ ታዬ ሲጠይቀው፤ "እኔ አላየሁም" ብሎ ይመልስለታል።

"እንግዳውስ ካንተውጭ እዚህ ቦታ የተቀመጠ ሰው የለም፤ ገንዘቡን አንተነህ የወሰድኸው፤ ገንዘቡን ካልሰጠኸኝ ይሄን ስልክ አልሰጥኽም" ብሎ አቶ ታዬ ከሟች የነጠቁትን ስልክ ከጠረጴዛው ላይ አፈፍ አድርጎ አንስቶ ያዘ። አማኑኤልና በረከት የተባሉት ጓደኛማቾች ደጋግመው "ስልኩን ስጠን" ብለው አቶ ታዬን ሲጠይቁት፤ እሱም በምላሹ "ቆሜ ውዬ የሠራሁት ብር ነው። መጀመሪያ ገንዘቤን መልሱልኝና ስልካችሁን ልመልስላችሁ" ሲላቸው ጥለውት ሄዱ። በነጋታው አማኑኤልና በረከት ደግመው "ስልኩን መልስልን" ብለው ሲጠይቁት በተመሳሳይ "ብሬን መልሱልኝና ስልካችሁን ልመልስላችሀ" ሲላቸው፤ "እኛ ያንተን ብር አልወሰድንም፤ ከወሰድከው ውሰደው" ብለው ስልኩን ለታዬ ትተውለት ሄዱ። ከዛ በኋላም ተስፋዬ ከፖሊስ ጣቢያ ተፈትቶ ሶስቱ ጓደኛማቾች አንድ ላይ መጥተው በእሱ ግሮሰሪ ውስጥ እየተጠቀሙ አይቷቸዋል። ነገር ግን ስልኩን ስጠን ብለው ግን ታዬን አልጠየቁትም።

አቶ ታዬም፤ አቶ መዝገቡ ይልቃል ለተባለ ግለሰብ በሁለት ሺ ሶስት መቶ (2,300) ብር ስልኩን በመሸጥ የጠፋበትን ብር ይተካል። አቶ መዝገቡ ይልቃል ደግሞ የቤት ኪራይ የሚከፍለው ገንዘብ ሲቸግረው የገዛውን ስልክ ለአቶ ሰለሞን ጌታነህ በሶስት ሺ (3,000) ብር ይሸጥለታል። አቶ ሰለሞንም ከቴሌ ያወጣውን የራሱን የስልክ መስመር (ሲም) የገዛው የስልክ ቀፎ ላይ አስገብቶ መገልገል ጀመረ።

በመዲናዋ የብዙዎች ደም በከንቱ ፈሶ ደመ ክልብ ሆኖ እንዳይቀር ጠዋት ማታ ሳይታክት የሚሠራው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፤ አቶ እሰይ ገ/ሕይወት ሞቶ ከተገኘበት ቀን ጀምሮ ገዳዩን ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ የገዳዩን ዱካ መከታተሉን ተያይዟል። በዚህም ፖሊስ የሟችን ስልክ ማን ይዞ እየተገለገለበት እንደሚገኝ ባደረገው ሙያዊ ክትትል፤ በቀን 04/07/2011 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 1:00 ስዓት አካባቢ የሟችን ስልክ ይዞ እየተገለገለ የሚገኘውን ተጠርጣሪ አቶ ሰለሞንን በቁጥጥር ስር አዋለ።

ፖሊስም ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አውሎ "ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ስትል ሟችን ገድለሃል" በሚል ፖሊስ ክስ ሲያቀርብበት፤ አቶ ሰለሞን በምላሹ "እኔ ስልኩን ያገኘሁት ወንጀል ሰርቼ ሳይሆን በገንዘቤ ገዝቼ ነው" በማለት ለሱ የሸጠለትን ሰው አቶ መዝገቡ ይልቃልን ለፖሊስ መርቶ ያስይዛል። አቶ መዝገቡም በተመሳሳይ የሸጠለትን አቶ ታዬን ለፖሊስ መርቶ ያስይዛል። አቶ ታዬም ከላይ በተገለጸው መሰረት እንዴት ስልኩን ከወንጀሉ ፈጻሚዎች እንደተቀበለ ለፖሊስ በማስረዳቱ፤ የወንጀሉ ፈጻሚ የሆኑትን አማኑኤልና ተስፋዬን ፖሊስ አድኖ በቁጥጥር ሥር ሊያውል ችሏል።

### የገዳዮች ቃል

ሁለቱም ተጠርጣሪዎች ከላይ ታሪኩ በተገለጸው መሰረት የወንጀል ድርጊቱን መፈጸማቸውንና በፈጸሙት ወንጀል መጸጸታቸውን ለፖሊስ ገልጸዋል። ተጠርጣሪ አማኑኤል መሠለ "ጓደኛው ተስፋዬ ሟችን እግሩን በጠረባ በመምታት ገፍትሮ እንዲወድቅ እንዳደረገ ጠቁሞ፤ የእርሱ ድርሻ ሟች ሲወድቅ ስልኩን አንስቶ መውሰድ እንደሆነ ለፖሊስ አስረድቷል። ተስፋዬ መሃመድ በበኩሉ ሟችን በጠረባ በመምታት መሬት ላይ እንዲወድቅ ማድረጉን አምኖ ለፖሊስ ተናግሯል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንም ተጠርጣሪዎቹን ከ05/07/2011 ዓ.ም ጀምሮ በቁጥጥር ሥር አውሎ፤ የተጠርጣሪዋን የእምነት ክህደት ቃል፣ የምስክሮችን የምስክርነት ቃል፣ የሟች አስከሬን የህክምና ውጤትና የአማሟት ሁኔታ የሚያሳይ ምስሎችና መረጃዎች አደራጅቶ ዐቃቢ ሕግ በተጠርጣሪዎቹ ላይ ክስ እንዲመሰርትባቸው መረጃውን አቅርቧል።

### የሚስት የምስክርነት ቃል

ወይዘሮ እሌኒ ከፍቶ፤ ከሟች ባለቤቷ እሰይ ገ/ሕይወት ጋር ለሰባት ዓመት ያህል በትዳር አብረው ሲኖሩ ምንም አይነት መጠጥ ጠጥቶ እንደማያውቅ እንዲሁም ከሰው ጋርም ጸብ እንደሌለው ገልፃ፤ በትዳር ሕይወታቸው ልጆች ማፍራታቸውንም ትናገራለች።

ወንጀሉ በተፈጸመበት ቀን ቤተሰብ ለመጠየቅ ወደ ቤተሰብ ቤት ሂዳ ቤት እንዳልነበረች ወይዘሮ እሌኒ ጠቁማ፤ ወንጀሉ በተፈጸመበት ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ባለቤቷ ወደ እሷ ስልክ ቁጥር ይደውልላታል። እሷም ባለቤቷን "ለምን እስካሁን ወደ ቤትህ አልገባህም?" ስትለው፤ ጀሞ አንደኛ በር አካባቢ ከወላጅ አባቱ ጋር በስልክ እያወራ ቆይቶ ወደ ቤቱ እየገባ እንደሆነ ይገልጽላታል። እሱም "ልጆቼን አገናኚኝ" ብሎ ሁለቱንም ልጆቹን አገናኘቼው። ልጆቹን አውርቶ ከጨረሰ በኋላ ሰልኩን ከልጇቿ ተቀብላ እያዋራችው እያለ ድንገት ስልኩ ተቋረጠ። እሷም "ሳንቲም አልቆበት ይሆናል ቆይቶ ይደውላል" ብላ እየተጠባበቀች እያለ፤ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ከዚህ ቀደም ተደውሎላት በማያውቅ ስልክ ቁጥር ወደ ስልኳ ተደውሎ ኤልያስ ገ/ሕይወት ጀሞ አካባቢ ወድቋል ይሏታል።

እሷም የባለቤቷ ስም በትክክል ስላልተገለጸላት፤ ተሳስተሃል ብላ መለሰችለት። ከዛም በድንጋጤ መልሳ በደወለላት ሰው ስልክ ስትደውል፤ "እሰይ ገ/ሕይወት" በሚል የባለቤቷን ስም አስተካክሎ ጠርቶ ጀሞ አንድ አካባቢ ወድቋል ብሎ ይነግራታል። እሷም "ምንሆኖ ነው?" ብላ ስትጠይቅ ታሞ ወድቆ ይሏታል። ወይዘሮ እሌኒ እየበረረች የተባለው አካባቢ ስትደርስ ሰዎች ተሰብስበው አይታ ወደ ተሰበሰቡበት ስትሄድ፤ ባለቤቷ አስፓልት ዳር የእግረኛ መንገድ ላይ በግንባሩ ተደፍቶ፤ በጀሮው፣ በአፉና በአፍንጫው በብዛት ደም እየፈሰሰው ባልታወቁ ወንጀል ፈጻሚ ጉዳት ደርሶበት ሕይወቱ አልፎ እንዳገኘችና የእጅ ስልኩ እንደተወሰደ ለፖሊስ ቃሏን ሰጥታለች።

### ዐቃቤ ሕግ

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 671/2/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ተከሳሾች የማይገባቸውን ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከላይ በተጠቀሰው ቀን፣ ቦታ እና ጊዜ ሟች እሰይ ገ/ሕይወትን 1ኛ ተከሳሽ ተስፋዬ መሀመድ በጠረባ በመምታት የእግረኛ መንገድ ጠርዝ ላይ እንዲወድቅ ሲያደርግ፤ 2ኛ ተከሳሽ አማኑኤል መሠለ በበኩሉ እያወራበት የነበረውን ቴክኖ ተች እስክሪን የእጅ ስልክ የዋጋ ግምቱ 3,800/ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ብር የሆነውን አንስቶ በመውሰዱ፤ እንዲሁም ሟች 1ኛ ተከሳሽ ሟችን እግሩን ጠልፎ ሲጥሉት ራሱ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ሕይወታቸው ያልፍ ሆኗል። በመሆኑም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ከባድ የውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ አደራጅቶ ክስ መስርቶባቸዋል።

### ውሳኔ

ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በተከሳሽ ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስጠት በችሎቱ ተሰይሟል። ፍርድ ቤቱም በዚህ ቀን በዋለው ችሎት ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ 1ኛ ተከሳሽ በ18 (በአሥራ ስምንት) ዓመት እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ በሀያ (20) ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ውሳኔ አሳልፏል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አንዳንዴ እንዲህ ነው !

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ከሰሞኑ በተለያዩ የማኅበራዊ ገፆች አንድ ቪዲዮ ደጋግሞ ሲመላለስ አስተዋልኩ። አንዳንዴ እንዲህ መሰሉን ጉዳይ መመልከቴ ብርቅ አይደለም። አሁን ያየሁትን እውነታ ግን እንደዋዛ ጨረፍ አድርጌ ማለፍ አልሆነልኝም። ደግሜ ደጋግሜ አየሁት። እናም ከልብ አዘንኩ።

ጉዳዩ እንዲህ ነው። አንዲት የታክሲ ተሳፋሪ ወጣት በድንገት ከእጇ መጥፋቱን ባወቀችው ስልኳ ምክንያት ክፉኛ ታለቅሳለች። እንደው ለማለት ያህል «ታለቅሳለች» ልበል እንጂ ሁኔታዋ ከሚባለው በላይ በእጅጉ አሳዛኝ ነው።

ማጋነን ባይሆንብኝ የልጅቷ ሁኔታ በድንገት የቅርብ ቤተሰቡን ሞት የተረዳ ያህል ከባድ ነው። ትጮኻለች፣ ትወድቃለች፣ ትነሳለች፣ በአጠቃላይ የምትይዘው፣ የምትጨብጠው ፣ ጠፍቷታል። አሁንም ሁኔታዋን ሳስበው ከልብ አዝናለሁ።

እንደሚመስለኝ የእጅ ስልኳ ድንገቴ መጥፋት የተከሰተው በተሳፈረችበት ታክሲ ውስጥ ነው። ምን ዋጋ አለው! እሷ የባነነችው ሰዎቹ ጉዳያቸውን ፈጽመው ወንዝ ከተሻገሩ ፣ ሌላውን ከጀመሩ ሆነ እንጂ።

ምንአልባትም ይህች ልጅ ለሀገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ ትሆናለች፣ ምንአልባትም የምትሻውን ሁሉ የምታገኝበት የመክፈጫ ቁልፍ ያለው ከሞባይሏ ሆድ ይሆናል። ምናልባትም....... ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን መዘርዘር ይቻላል።

አዎ! በየጊዜው ልክ እንደእሷ ሁሉ ሀሳብ ጉዳያቸው በድንገት የባከነባቸው፣ ሳያስቡት ውጥን ዕቅዳቸው፣ ጭምር አብሮ የተሰረቅባቸው ወገኖች በሽ ናቸው። በእነ እንቶኔ የስርቆት ዘዴ ተታለው ፈቅዶ የመስጠት ያህል የእጃቸውን ያስረከቡ፣ እየረቀቀ ለመጣው የዝርፊያ ስልት መሞከሪያ የሆኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ቤትና ጊዜ ይቁጠራቸው እንጂ በየጊዜው የሚያስገርሙ የስርቆት ታሪኮችን ሰምተናል፣ እየሰማንም ነው ።

ሀቁን ለመናገር እነዚህን እውነታዎች በየአጋጣሚው ደጋግመን ሰምተናቸዋል። በሌላ አነጋገር በየቀኑ በሌሎች ላይ ሆኑ፣ ተፈጸሙ የሚባሉ የስርቆት ሥልቶችን አሳምረን እናውቃቸዋለን። እንዲያውም አንዳንዴ ራሳችን ሳንቀር የምናወራቸው፣ በወጉ የምንተርካቸው ጭምር ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህን ስንል ደግሞ ከማወቅም አልፈን ለሚሰሙን ሁሉ ከችግሩ «ተጠንቀቁ» ብለን ማሳሰቢያውን በመቸር ነው። አንዳንዴ ግን በወጉ አውቀናቸዋል፣ በምንላቸው ማታለያዎች ተሸውደን የችግሩ ዋንኛ ሰለባዎች ሆነን እንገኛለን። ትናንት ማሳሰቢያውን ለሌሎች እንዳልሰጠን፣ እንዳላስጠነቀቅን ሁሉ «ነቅተንበታል» ባልነው ወጥመድ እኛው ተጠልፈን እንወድቃለን።

እስከዛሬ በርካቶች ፍጹም ሊያስነቁ በማይችሉ የማታለያ ዘዴዎች ተጭበርብረዋል። የዝርፊያው ከዋኞች በጉዳዩ ሰፊ ጥናት አድርገው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውም አብዛኞችን ለችግር ዳርጓል። ብዙዎቻችን እንደምንገምተው ደግሞ የጉዳዩ ተዋናዮች በቆሸሸ ልብስ የሚታዩ፣ የተጎሳቆሉና አፍላ የሚባሉ ወጣቶች አይደሉም። በተቃራኒው ጨዋታውን የሚዘውሩት ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ነፍሰጡር መሳይ እናቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ የቡድን አባላት የዝርፊያውን ሂደት በማህበር ተደራጅተው ከያዙት በአንድም በሌላም የራሳቸው ተግባርና የሥራ ክፍፍል ይኖራቸዋል። ብዙ ጊዜ ዝርፊያውን በማታለል አስልተው ሲፈጽሙት በሌሎች ዘንድ ፍጹም ጥርጣሬን በማያሳድሩ ሰዎች እንደመሆኑ ድርጊቱም ተጠንቶበት የሚሠራ ይሆናል።

ብዙ ጊዜ እነዚህ የተደራጁ ቡድኖች ጥናታቸውን የሚተገብሩት በታክሲ ውስጥ ነው። በስፍራው ሲገኙ ደግሞ ከተሳፋሪዎቹ አብዛኞቹ እራሳቸው ይሆናሉ። ጥቂት ሰለባዎቻቸው ወንበር ይዘው ጉዞ በጀመሩበት አጋጣሚ ታዲያ ገንዘብ፣ ጌጣጌጥና ሞባይሎቻቸውን ከእጃቸው ለማስገባት የትወናው መድረክ ለእነሱ ቀላል የሚባል ነው።

የፈረደበት በሰዓትና በቦታው አይገኝ እንጂ በመረባቸው የገባ ተሳፋሪ ብዙ ይደርስበታል። ሽማግሌዎች ብለን የምናከብራቸው፣ የዝርፊያው ቡድን መሪዎች ይሆናሉ። ነፍሰጡር መስለውን የምንንከባከባቸው ኪስ ለማጠብ እጃቸውን ያሰላሉ።ለምቾቷ አስበን ወንበር ያጋራናት ወጣት አሳልፋ ትሰጠናለች። ትወናው ተጀምሮ እስከሚያልቅ አንዳች ያልጠረጠረ ያለውን አስረክቦ፣ ኪሱን አሳጥቦ ይወርዳል።

አንዳንዴ ነገሮች በዚህ ብቻ ላያልፉ ይችላሉ። በእነዚህ ዘራፊዎች እጅ የገባ ሁሉ በዝምታ ያለውን አስረክቦ የማይወጣበት አጋጣሚም ይኖራል። ባስ ባለ ጊዜ ዘራፊዎቹ ጥቃት አድራሺዎች ናቸው። ከኪስ ያገኙትን ኪሳቸው ካኖሩ በኋላ አሳቻ ቦታ ገፍትሮ ለመጣል ልባቸው ይጨክናል። ዝርፊያውን እየፈጸሙ የነቃባቸው ተሳፋሪ ካለ ደግሞ ውሳኔያቸው ከዚህ ሊከፋ ይችላል።

እስከዛሬ በርካቶች በተለያዩ የማጭበርበር ስልቶች ጉድ ሆነዋል። ከዘመነኞቹ «ሿሿ» ተብዬዎች ልማድ መለስ ስንል የቀደሙትን የማጭበር በር ስልቶች እናስታውሳለን። እነዚህኞቹ ብዙ ጊዜ የሰዎችን ሥነልቦና ተጠቅመው በደካማ ጎን የሚፈጸሙ ናቸው።

ይህ ዓይነቱ ስልት በአብዛኛው የሰዎችን ውስጠት የሚቆጣጠር ከመሆኑ ጋር በርካቶች ሲታለሉና ሲዘረፉበት ቆይተዋል። ይህን ርዕስ ጉዳይ ስናነሳ በብዙዎቻችን አዕምሮ ውል የሚልብን የሎተሪ ደርሶኛልና የ«መታወቂያ የለኝም» ጉዳይ ነው።

ልክ እንደሱ ሁሉ በተለምዶ «ቁጭ በሉ» በሚል ስልት ሰዎችን ከአንድ ቦታ ጎልተው ገንዘብና ወርቆቻቸውን በመያዝ ዝርፊያ ስለሚፈጽሙ አታላዮች አንድ ሺህ አንድ ጊዜ የሰማን አንታጣም። ይህ የማጭበር ስልትም ካላጋነንኩት ዓመታትን ያስቆጠረ ዘዴ ነው።

ችግሩ ይህን ጉዳይ ጠንቅቀን ማወቁ ላይ አይደለም። በጣም አስገራሚው ነገር ዓመታትን ስንሰማው በኖርነውና እኛም ሌሎችን ባስገነዘብንበት ስልት መልሰን መታለላችን እንጂ። ለዚህም ይመስላል ዛሬም በርካቶች ከዓመታት በፊት «አውቀነዋል፣ በልተነዋል» ባሉት የዝርፊያ ስልት የሚሸወዱት። ለዚህም ነው አሁንም ድረስ የእነ «ቁጭበሉ» እና «የሎተሪ ደርሶኛል» ጉዳይ ያልደበዘዘው ።

ለነገሩ የጉዳዩ ፈጻሚዎች የየጊዜው ስልት እንደየዘመኑ ይለያያል። ዛሬ «አወቅንባቸው» ብለን ብንጠነቀቅ ነገ መልኩን ቀይረው ጉድ ይሠሩናል። አሁን «አንሸወድም» ብለን ብንጀግን ቆይተው አቅም ዕውቀታችንን ያስጥሉናል።

ትናንት የታክሲ መስኮትን «ዝጉልን» በሚል ስልት ገንዘብ ሞባይል የተላፉ ተሳፋሪዎችን ታሪክ አሳምረን ሰምተነዋል። ነገ ተመሳሳዩ ሙከራ በእኛ ሲደገም ግን እንደነበረን መረጃ አስቀድመን አንጠረጥርም። እንደተባልነው ጥግ ተቀምጠን መስኮት ልንከፍት እንጣራራለን። በሽተኛ ለመምሰል የተወነችውን ሴት ልናግዝ እንጎነበሳለን።

ምንአልባትም በጽሑፌ መግቢያ ላይ የጠቀስኩላችሁ ሴት ጉዳይ ከዚሁ ሀሳብ የተዛመደ ሊሆን ይችላል። በታክሲ ጉዟችን ለብዙ የዝርፊያ አጋጣሚዎች ሰለባ የምንሆንባቸው ጉዳዮች የሰፉ ናቸው። አብዛኞቹን የስማችን ያህል እናውቃቸዋለን። ሌሎቹም ቢሆን ከጆሯችን የዕለት ወሬ የራቁ አይደሉም። ነገርግን እንደ አዲስ በነዚህ ድርጊቶች ስንጠለፍ እንውላለን።

መቼም የሰው ልጅ በተፈጥሮው በማንነቱ ጉዳይ ሙሉ ሆኖ አያውቅም። ምን ጀግና፣ «ጠንቃቃ ነኝ» ቢል በአንዳች አጋጣሚ ጎድሎ መገኘቱ አይቀሬ ነው ። ለዚህም ይመስላል አብሮት ባለው ጉዳይ ባዕድ መሆኑ። አይቶ ማስተዋል፣ አስተውሎ መጠንቀቅ ሲችል መዘናጋቱ። አንዳንዴ እንዲህ ነው። «የፈሩት ይደርሳል፣ የተጠነቀቁለት ይሰበራል» እንዲሉ።

# ዓለም አቀፍ

## አፍሪካ ኅብረት የጋቦንን አባልነት አገደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአፍሪካ ኅብረት የመንግሥት ግልበጣ የተደረገባትን ጋቦን ከአባልነት አግዷል። ይህም ከ2020 ወዲህ ስምንተኛ መፈንቅለ መንግሥት በተደረገባት ሀገር የተወሰደ የመጀመሪያ እርምጃ ሆኗል።

መንግሥት ግልበጣው የቦንጎ ቤተሰብን የስድስት አስርት ዓመታት የሥልጣን ቆይታ እንዲያከትም አድርጓል። በቀጣናው መንግሥት ፈንቅለው ሥልጣን እንደያዙ ጁንታ ሁሉ የጋቦን ወታደራዊ መንግሥትም ሥልጣኑን ማጠናከር ይፈልጋል፤ ምንም እንኳ ዓለም አቀፍ ውግዘት ቢበረታበትም።

በሚቀጥለው ሰኞ የመፈንቅለ መንግሥቱ አቀናባሪ ጀኔራል ብሪክ ኦሊጉ ንጉማ ቃለ መሀላ ይፈጽማሉ ተብሏል። የአፍሪካ ኅብረት የሰላምና ደህንነት ም/ቤት ሐሙስ የመጀመሪያ እርምጃ በመውሰድ፤ ጋቦንን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን እስክትመልስ ድረስ ከኅብረቱ እንቅስቃሴና ተሳትፎ አግዷታል።

ጋቦንን በአባልነት የያዘው የማዕከላዊ አፍሪካ የፖለቲካ ጥምረትም የመንግሥት ግልበጣውን አውግዟል። ጥምረቱ ምላሽ ለመስጠትም አስቸኳይ ስብሰባ መጥራቱን አስታውቋል፤ ምንም እንኳ የቆረጠውን ቀን ባያሳውቅም።

መንግሥት ገልባጮች የጋቦን የምርጫ ውጤት በታወጀ በደቂቃዎች ልዩነት ሥልጣን መቆጣጠራቸውን ረቡዕ ሌሊት አሳውቀዋል።





## የብሪታንያ መሣሪያ አምራች ለዩክሬን መሣሪያ ለማቅረብ በኪየቭ ቢሮ ከፈተ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዩናይትድ ኪንግደም ታዋቂ የመከላከያ ኩባንያ ቢኤኢ ለዩክሬን መሣሪያና ትጥቅ ለማቅረብ ስምምነት ፈርሟል።

ኩባንያው በዩክሬን ሕጋዊ እንቅስቃሴ ለማድረግም በኪየቭ ቢሮ ከፍቷል። ድርጅቱ እርምጃው አጋሮችን ለማግኘት በቀጥታ መሥራትን እንደሚፈቅድለት ገልጾ፤ ቀላል መሣሪያዎችን በኪየቭ ለማምረትም ዓይኑን ጥሏል።

ቢኤኢ ዩናይትድ ኪንግደምና ሌሎች ሀገራት ለዩክሬን የላኳቸው አብዛኞቹን መሣሪያዎች ማምረቱን ቢቢሲ ዘግቧል። የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ ከየካቲት 2022 ጀምሮ ዩናይትድ ኪንግደም የኪየቭ ከፍተኛ መሣሪያ አቅራቢ ሆናለች።

የዩክሬይን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ሀገራቸው ውስጥ የጦር መሣሪያ ማምረቻ መክፈት ቅድሚያ የሚሰጠው ልማት መሆኑን በቀድሞው ትዊተር በአሁኑ ኤክስ ላይ አስፍረዋል። ፕሬዚዳንቱ ይህን ያሉት ከኩባንያው ሥራ አስፈጻሚ ቻርለስ ውድበርን ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ነው።

ኪየቭ የጦር መሣሪያና የሌሎች የመከላከያ ትጥቅ አቅርቦትን ለማሳደግ ልዩ ፍላጎት አላት። የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ከጀመረ ወዲህ የአክሲዮን ድርሻው በ75 በመቶው ያሻቀበው ቢኤኢ፤ ለዩክሬን ጦር ሥልጠናና የጥገና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ሥነ-ኮከብ እና የኢትዮጵያ አበርክቶት

ግርማ መንግሥቴ

**ኮከብህ ከኮከቤ የገጠመ ለታ፣**
**ለማሪያም መቀነት ለገብርኤል ኩታ፣**
**(ድምፃዊት ፍቅረአዲስ ነቅአጥበብ)**

በአሁኑ ጊዜ የሥነ-ኮከብ ጥናት ሳይንስ ለብዙዎች ብርቅ አይደለም። ብርቅ አይሁን እንጂ ቀላል ደሞ አይደለም። በብዙዎችም የሚሞከር ነው ማለት አይቻልም፡፡ የኮከብ ቆጠራ እንዲህ እንደምናወራው ቀላልና "የጠንቋይ ስራ አይደለም" የሚሉ ተከራካሪዎች ኮከብ ቆጠራ በፕላኔቶች እና በከዋክብት አንፃራዊ አቀማመጥ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው የሚያስምሩበት።

የወደፊቱን ለመመልከት፣ ለወደፊቱ ስለሚጠብቁ ክስተቶች እና ማስጠንቀቂያዎች ለመማር ፋይዳው ብዙ ነው ባይ ናቸው። ኮከብ ቆጠራ ከፍተኛ የሆነ የእውቀት ዘርፍ እንደሆነና በከፍተኛ የትምህርት ተቋምና የጥናት መስኮች ውስጥ ጥናት ይደረግበታል፡፡ ተመራማሪዎችም በዚህ ዘርፍ እስከ ከፍተኛ አካዳሚክ ማዕረግ ድረስ ይዘልቁበታል።

አስትሮሎጂ "የጠንቋይ ስራ" አለመሆኑን የምንረዳው ‹‹ጥንቆላ›› አስማትና ምትሀት ከአስትሮሎጂ ጋር ተቀላቅለው (ለጥፋትና ለማጭበርበሪያ ዘዴ) ያዳበሩት በአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ነበሩ፡፡ ይህም የአስትሮሎጂ ጥናት ላይ የራሱን መጥፎ ጥላ አጥልቷል። ‹‹በአሁኑ ጊዜ ማጂካል (ምትሀታዊ) አስትሮሎጂ ጊዜ ያለፈበትና ምንም ጥቅምና እውቀት የሌለበት እንደሆነ ታውቋል›› ሲሉ ዶክተር አብነት ስሜ በመፅሃፋቸው ገፅ 283 ላይ አስፍረዋል፡፡

የዶ/ር አብነት ስሜ መፅሃፍ መግቢያ አረፍተ ነገር እንደሚለው አስትሮሎጂ ኮከቦች (12ቱ ነገደ ከዋክብት) በሰው ልጆች ስብእና ላይ ያላቸውን ተፅእኖ የሚያጠና ሲሆን በርካታ ዘርፎችም (ለምሳሌ የህክምና አስትሮሎጂ) ቀደምት የጥናት መስክ መሆኑን ያመላክታል።

በተለያዩ ርእሶች፣ ለምሳሌ "የልደት ቀንዎ ስለ እርስዎ ምን ይናገራል?"፣ "የተወለደቡት ቀን እና ኮከብዎ ስለ እርስዎ ምን ምን ባህሪያትን ይገልፃል?"፣ "የእርስዎን ተፈጥሯዊ ምንነት ያንፀባርቃሉ የሚባሉት የ ‹‹ዞዲያክ›› ምልክቶች እነማን እንደሆኑና በመሳሰሉ ርእሶች የተለያዩ ፀሀፍት የተለያዩ መፃህፍትን ለንባብ አብቅተዋል፡፡ እለታዊውም ሆኑ ሳምንታዊ ጋዜጦች፤ ሳምንታዊም ሆኑ ወርሀዊ መጽሔቶች ለ ‹‹ሆሮስኮፕ›› ልዩ ቦታን ሰጥተው ሲያስነብቡ ነው የኖሩት። ዛሬም እንደዚሁ፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየን፣ ያረዳድ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር፣ ጉዳዩ እንዲህ እንደምንለው ቀላል አለመሆኑን ነው።

እንደ "የእሳት ደህንነት ኢንሳይክሎፒዲያ" መረጃ ከሆነ ዞዲያክና ምልክቱ "የአንድን ሰው ባህሪ እና ዕጣ ፈንታ ለመረዳት ቁልፍ ይሰጣል፡፡ ቆጠራው በፕላኔቶች እና በከዋክብት አንጻራዊ አቀማመጥ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ነገን ለመመልከት ያግዛል፡፡ ምልክቶቹ (12ቱ) የእኛን የተፈጥሮ ምንነት ያንፀባርቃሉ፡፡ በአንድ ወይም በሌላ የዞዲያክ ምልክት ስር ስለተወለደ ሰው ስውር እና ምናልባትም የማይታወቁ ባህሪያትን፣ ተሰጥኦዎችን፣ ችሎታዎችን ለማወቅ፣ በህይወት ውስጥ ግንዛቤን እንድናገኝ ይረዳናል።

ስለራሳችን፣ ስለምናውቃቸው እና ስለጓደኞቻችን ብዙ አስደሳች እና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችለናል። ራሳችንን ሊከሰቱ ከሚችሉ አደጋዎች ለመጠበቅ ያግዛል፡፡ ይህ የኢንሳይክሎፒዲያው ብያኔ በሌሎች በርካታ ምሁራን ስራዎች ውስጥም ተንፀባርቆ የሚገኝ ብያኔ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ዶክተር ሮዳስ ያበረከተው "አንድሮሜዳ" መፅሃፍም ይንንኑ ያረጋግጣል፡፡

ይህ ከባህረ ሀሳብ፣ ቀን መቁጠሪያ፣ ፍካሬ ቁጥር (ኒሞሮሎጂ) እና የመሳሰሉት ጋር ቀጥተኛ ዝምድናና ተደጋጋፊነት ያለው የጥናት መስክ እንዲህ እንደ ዛሬው በዓለም ላይ ከመናኘቱ በፊት፣ በጋዜጦችና ኢንተርኔት ገፆች ከመሰራጨቱ አስቀድሞ እነ ማን ጋር ነበር?፣ የእነ ማንስ አእምሮ አፈለቀው? ምን ምን ገፅታዎችስ ነበሩት? የሚሉትን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ የኮከብ ጉዳይ በበርካታ ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ሁሉ እየገባ የአንዳንድ አበይት ጉዳዮች መገለጫ ሆኖ ሲያገለግል ይታያል። ለዚህም አስረጂዎቹ "ኮከባችን አልገጠመም"፣ "ኮከባችሁ ባይገጥም ነው"፣ "ኮከባችን ገጥሟል" የሚሉት አገላለፆች ናቸው። እነዚህ ደግሞ ለፍቅር፣ ለ"የፍቅር ኬሚስትሪ"ም (ከላይ የፍቅረአዲስን ዜማ - ናፍቆት፣ መሻትና ስዕለት (ለማሪያምና ለገብርኤል ስለት) ልብ ይሏል) ለወዳጅነትም ሲያገለግሉ ይታያል። እዚህ ጋር "Astrology: Love and Lifestyle" በሚል ርዕስ የተዘጋጁትን የአንጄላ ማኮርሚክ ስራዎች ቅጽ 1 አንድና ቅጽ 2 ማመሳከር ጉዳዩን በአግባቡ ተረድቶ ለማለፍ ያግዛል።

የኮከብ ቆጠራ ፍልስፍና የግለሰብ ኮከቦችን እንዴት አድርጎ እንደሚገልፃቸው፤ የአገላለፅ ዘዴና ስልቱ እንዴት እንደሆነ መመልከቱም ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ካፔዎችን (የዞዲያክ ምልክታቸው ካፕሪኮርን (Capricorn Zodiac) የሆኑትን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል፡፡

"ካፕሪኮርን (ከታህሳስ 23 — ጥር 20 የተወለዱ) ሰዎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ሰዎች መንፈሰ ጠንካራ፣ የማይበገር አመለካከት ያላቸው እና ሰዎች እንዲህ አድርጉ ብለው እንዲመክሯቸው የማይፈልጉ ናቸው። በዚህ ወር የተወለዱ ሰዎች ጎበዝ፣ ነገር ግን ሌሎችን የማይሰሙ፣ ጥሩ አለቃ የሚወጣቸው፤ በተፈጥሮ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የማስተማር ብቃት ያላቸው ሲሆኑ ጠንካራ የስራ ስነ-ምግባርን የተላበሱ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች የማይታመን ትዕግስት እና ጽናት አላቸው። ረጅሙ ጉዞ እንኳን የሚጀምረው በአንድ ትንሽ እርምጃ እንደሆነ፤ የመጀመሪያው እርምጃ ሁል ጊዜ በጣም ከባድ መሆኑን ስለሚያውቁ ሁል ጊዜ ግባቸው ላይ ይደርሳሉ። የመሰላቸውን ለመናገር ወደ ኋላ የማይሉም ናቸው።

ሌሎችንም በዚሁ መንገድ መግለፅ የዚህ ጥንታዊ ልሂቃን ፍልስፍና የሆነው ኮከብ ቆጠራ (አንድ ሰው የተወለደበትን ቦታ ጂኦግራፊያዊ መጋጠሚያዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድ ሰው በተወለደበት ጊዜ ከዞዲያክ ምልክቶች ጋር በተያያዘ የፕላኔቶች ሥፍራ) አይነተኛ መለያ ነው።

ኮከብ (Astro - "logy" ሲጨመርበት "Astrology" በመሆን ወደ ጥናት መስክነት (ሥነ-ኮከብ ወይም የኮከቦች ሳይንሳዊ ጥናት) ከፍ የሚል ሲሆን፤ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ የባህርይ፣ የተግባር፣ የማንነት መገለጫ የሚመስለን ቁጥራችን ቀላል አይደለም። እንደ ባለሙያዎቹ ድምዳሜ ከሆነ ይህ "ስህተት" ነው። ማንኛውም አካል ኮከብ አለው፤ በዛ ኮከቡና ኮከብ ቆጣሪው (ሆሮስኮፕ) አማካኝነት ባህሪይው፣ አመሉ፣ ማንነቱ፣ ተክለ ሰውነቱ፣ ጤናው ይመዘናል፡፡ ይለካል፤ ይፈተሻል። ከዶ/ር አብነት ስሜ "ፍካሬ ኢትዮጵያ" መጽሐፍም የምንረዳው ይህንኑ ነው።

ፍካሬ ኢትዮጵያ እንደሚያስነብበን ከሆነ፣ የመጀመሪያው ሰው "አዳም" እና "መከላከያ ሚኒስቴር" ኮከባቸው ኤሪስ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ቪርጎ ሲሆን፤ የከተማ ልማት ሚኒስቴር ካፕሪኮርን ነው። ኤሪሶች ኮከቡ "አዳም" በመሆኑ ምክንያት "ዓለም የእኛ ናት፤ መግዛትም ያለብን እኛ ነን" የሚል አስተሳሰብና አቋም ያላቸው መሆኑ ይነገራል።

በፈጠራው ዓለም ውስጥም ኮከብ የሚሰራ ሲሆን የፍቅር እስከ መቃብሮቹ ገፀባህሪያትም የየራሳቸው ኮከቦች አሏቸው። በዚሁ መጽሐፍ ላይ ሰፍሮ እንደምንመለከተው ጉዱ ካሳ አኳሪየስ ሲሆን፤ ሰብለወንጌል ደግሞ ስኮርፒዮ ናት።

በኃይማኖት (መላእክት) ዘንድም ኮከብ የሚሰራ ሆኖ የምናገኘው ሲሆን፣ ጴጥሮስ ኤሪስ፤ እንድሪያስ ካንሰር፤ ፊሊጶስ ቪርጎ፤ ቶማስ ስኮርፒዮ፤ ማቴዎስ ካፕሪኮርን ሆነው እናገኛቸዋለን። (በዘኒከማሁ፣ ገጽ 384 — 385) እንደተፃፈው፡፡

ወደ አገራትና ከተሞችም ስንመጣ በተመሳሳይ የየራሳቸው ኮከቦች ያላቸው ሲሆን፣ አገረ ግብፅ እና ለንደን ከተማ ጄሚኒዎች፤ ደቡብ አፍሪካ እና ደብረሊባኖስ ፓይሰስ ናቸው። ኢትዮጵያስ?

ዶክተር አብነት በመፅሃፋቸው ገጽ 26 እንዳሰፈሩት ኢትዮጵያ በዋና ኮከቧ አኳሪየስ ስትሆን በአሴንዳንቷ (በስርቀተ ፀሀይ ወይም በመሬት ኮከቧ) ኤሪስ ነች። በሁሉም ነገር ቀዳሚ የመሆን እና የአትንኩኝ ባይነቷ ባህርይ ከዚህ የሚነሳ ነው። በዚህ የአኳሪየስ ዘመን የኤሪስ ኮከብ ባለቤት የሆኑ ልጆቿም በኢኮኖሚው፣ በሥነ-መንግሥቱ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ከመሬት እስከ ማርስ የሚደርስ እመርታን እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል። የኤሪሶችን ችቦ ፓይሰሶች፤ የፓይሰሶችን ችቦ ደግሞ አኳሪየሶች ይቀበላሉ። ያኔ ኢትዮጵያም "ኢትዮጵያ" ትሆናለች።

በበርሊኑ ጉባኤ (እ.ኤ.አ 1884 እና እ.ኤ.አ 1885) አፍሪካን የመቀራመት ውል አሁንም እየተስተዋለ ነው የሚሉ ወገኖች እየበዙ ነው። ለምሳሌ ሊ ዌንግራፍ የተባሉ ፀሀፊ በ"Extracting Profit: Imperialism, Neoliber¬alism and the New Scramble for Africa" (እ.ኤ.አ 2016) ስራቸው ይህንኑ ነው የሚነግሩን፡፡ በዚሁ መሰረት ዋና ዋና የአፍሪካ ተቀራማቾች እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ጀርመን ሲሆኑ፣ የሶስቱም ኮከብ ኤሪስ ነው።

ወደ ጥንታዊው ፍልስፍና ስንመለስ ደግሞ የዓመቱ አስራ ሁለት ወራት በዞዲያክ ህብረ ከዋክብት የተከፋፈሉ መሆናቸውን ያስታውሳል፡፡ በአገር ደረጃ የሚጠቀሱት አራት አገራት ኢትዮጵያ፣ ኢራቅ፣ ቻይና እና ጃፓን ናቸው። የሌሎቹን ትተን ኢትዮጵያን ብንመለከት እንኳን ከጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤትነት ምድብ ስር ከአናት እንድትገኝ ካደረጓት አንዱ ይኸው የኮከብ ቆጠራ ሳይንስ እውቀቷ ነው።

ዛሬ ካፕሪኮርን፣ ጂምኒ፣ አኳሪየስ ወዘተ እያልን በዘመን አመጣሽ ስማቸው እናቆላምጣቸው እንጂ ጥንትም በኢትዮጵያ አስትሮሎጂ አዋቂዎች ዘንድ የነበሩና ሐመለ እሳት (ኤሪስ)፣ ስውር መሬት (ቶረስ)፣ ገውዝ ነፋስ (ጄሚኒ)፣ ሸርጣን ውሃ (ካንሰር)፣ አሰድ እሳት (ሊዮ)፣ ሰንቡላ መሬት (ቪርጎ)፣ ሚዛን ነፋስ (ሊብራ)፣ አቅራብ ውሀ (ስኮርፒዮ)፣ ቀውስ እሳት (ሳጁታሪየስ)፣ ጀዲ መሬት (ካፕሪኮርን)፣ ደላዊ ነፋስ (አኳሪየስ)፣ ሑት ውሃ (ፓይሰስ) በሚል የሚታወቁ ነበሩ።

የኮከብ መመሳሰል የተግባር መመሳሰልን ያስከትላል የሚል ድምዳሜ ይህ ጸሐፊ አላጋጠመውም። አያጋጥመው እንጂ በበርካታ ተመሳሳይ ኮኮብ ባላቸው አካላት መካከል የተግባር ተመሳስሎ ሲያጋጥም ግን ይታያል፡፡ ለምሳሌ ዶክተር አብነት እንደጠቀሱት እኛም እንደምናውቀው፣ ፊታውራሪ መሸሻ እና አፄ ኃይለሥላሴ ስርአትን ከማስቀጠል አኳያ)።


ይህንን እንበል እንጂ፣ ይህ የተግባር ተመሳሳይነት አንድ አይነት ተግባርን ከመፈፀም ጋር ሊያያዝም፣ ላይያያዝም ይችላል። ትልቁ ተመሳስሎ እሱ አይደለም። ወሳኙ የመመሳሰል ሁኔታ የሚታየው በአንድ ተግባር ጎላ ብሎ መታየት፣ ወይም ታዋቂ በመሆን ነው፡፡ ለምሳሌ "ጀግና" መሆን። የጀግንነት መገለጫው በተሰማሩበት ሙያ ጀግኖ ሆኖ መገኘት እንደ መሆኑ መጠን በሙያቸው ጀግና የሆኑ፤ "አንቱ"ም የተባሉ በርካቶች ሲሆኑ፤ ይህም ከኮከባቸው ጋር እየተያያዘ ሲገለፅ ይታያል። ጀግና ያልሆነውም እንደዛው ጀግና አለመሆኑ ይተነተናል።

በበርካታ ጥናቶች ላይ ስንመለከት እንደ ኖርነው፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ያበረከተችው አለ ከማለት ያላበረከተችው የለም ማለቱ ይቀላል። ሌላው ቀርቶ ከዚህ ከሥነ-ኮከብ ጥናት አኳያ ያለውን ብቻ ብንመለከት የአስተዋፅኦዋ መነሻ አሻራ ከ"ዓውደ ነገሥት" መጽሐፍ ይጀምራል። እዛ ላይ ሁሉም ተብሏል፡፡ ሁሉም ተገልጿል። ምናልባት በአሁኑ ዘመን መነፅር ተመልክተን ይህ ይጎላል፤ ይህ ይበዛል ካላልን በስተቀር።

በዶክተር አብነት መፅሀፍ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ከሰጣቸው የመረጃ ምንጮቹ አንዱ ይሄው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሊቃውንት ውጤት የሆነው ዓውደ ነገሥት ነው። ይህንኑ ተንተርሰው የውጪው ዓለም ቀደምት ምሁራን አስፈላጊውን ጥናትና ምርምር ካደረጉ በኋላ ስለዚሁ መፅሀፍና ስለ ኢትዮጵያ ብሎም ኢትዮጵያዊያን አስተዋፅኦ በጉልህ ያሰፈሩት በዚሁ መጽሐፍ ላይ እንደ ወረደ፣ በመገኛ ቋንቋው በመጽሐፉ አባሪነት ተያይዞ ይገኛል።

ዶክተር አብነት በመፅሃፋቸው ገጽ 386 ላይ በ"ድህረ ቃል" ስር "አልበርት ፓይክ ስለ ኢትዮጵያ የአስትሮሎጂ ጥበብ ጀማሪነት" በ1871 ያሰፈሩትን፤ በገጽ 389 ላይ "ጆን ጃክሰን ስለ ኢትዮጵያ የአስትሮሎጂ ጥበብ ጀማሪነት ("The Ethiopians were the first who invented the science of Stars" (1926) በሚል ርእስ) የፃፈው" እና ሌሎችንም በዋቢነት አስፍሮ እናገኛለን።

በዚህ ውስጥ የተጠቀሱትም ሆነ ያልተጠቀሱ ሌሎች በርካታ ስራዎች መረዳት የሚቻለው ኢትዮጵያ በየዘርፉ የነበራትን እውቀት ብቻ ሳይሆን የነበራትን ተፅእኖ ፈጣሪነት፤ የነበራትን የፍልስፍና ደረጃ፤ የነበራትን ዓለም አቀፍ ብስለት፤ ከሁሉም በላይ የነበራትን የተፈጥሮ እውቀት ነው። አሁን ጥያቄው "እንዴት አድርገን ያንን እናስቀጥል?" የሚለው ነው ራስ ምታቱ። እንዴት እናስቀጥል፣ ወይስ "ትልቅ ነበርን፤ ትልቅም እንሆናለን" በሚለው ተስፋ እንቆዝም? ነፍሳቸውን በገነት ያኑረውና አማረ ማሞ እንዳሉት ጉዳዩ ያነጋግራል፤ ያወያያል፤ ያመራምራል።




ሽክ
ብለናል
5.5%
የደስደስ ነው
ስፔሻል ይሁንልን
BEDELE
SPECIAL
PREMIUM BEER OF ETHIOPIA
EXPORT QUALITY
BEDELE
SPECIAL

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የትራፊክ ፍሰቱን ማሳለጥ የጀመረው መንገድ

በኃይሉ አበራ



መንገዱ በሁለቱም አቅጣጫ በአንድ ጊዜ ስምንት መኪኖችን ማስተናገድ ያስችላል

የሀገሪቱን የወጪ ገቢ ንግድ እንቅስቀሴ በማሳለጥ አገልግሎት ሲሰጥ የኖረ መንገድ ነው፤ ከአዲስ አበባ ከተማ መውጫና መግቢያ በር መንገዶች አንዱ ሆኖ ሲያገልግል ኖሯል፡፡ እየጨመረ የመጣውን የትራፊክ ፍሰት መሸከም አቅሙን ለማሳደግና አገልግሎቱን ይበልጥ በተሳለጠ መልኩ እንዲችል ለማድረግ በየጊዜው በአዲስ መልክ ሲገነባ፣ ሲጠገን ቆይቷል፡፡ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ፋይዳውን ታሳቢ በማድረግ በአዲስ መልክ መገንባት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲያስገነባው የቆየው ይህ የቃሊቲ ቱሉዲምቱ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ሰፊና እየጨመረ የመጣውን የትራፊክ ፍሰት ለማስተናገድ የሚያስችሉ ትላልቅ ማሳለጫ ድልድዮች እንዲኖሩት ተደርጎ ነው ወደ ግንባታው የተገባው፡፡ ይሁንና ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሳይጠናቀቀ ዓመታት ማለፉን ተከትሎ፣ በህዝቡ ዘንድ ሰፊ ቅሬታ ሲነሳበትም ነበር፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንባታውን ለማጠናቀቅ በወሰደው እርምጃ አሁን አብዛኛው ስራው ተጠናቆ ለትራፊክ ክፍት ተደርጓል፡፡ የከተማ መንገዶች ባለስልጣን መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ግንባታው ተጓትቶ የቆየው የመንገዱ ግራ ክፍል አንድ ዙር አስፋልት እንዲለብስ በማድረግ ነው መንገዱ ሙሉ ለሙሉ ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆን የተደረገው፡፡ የመንገዱ ተገልጋዮችም የመንገዱ ለትራፊክ ክፍት መሆን መጀመር እፎይታ እንደሰጣቸው እየገለጹ ናቸው፡፡

አቶ ዳዊት ካሳዬን በዚሁ መንገድ ትራንስፖርት ሲጠብቁ አገኘናቸው። ከቃሊቲ ውሃ ልማት አካባቢ ቱሉ ዲምቱ አካባቢ ሁሌም በትራንስፖርት ይመላለሳሉ። ባለፉት ዓመታት ከቃሊቲ አደባባይ እስከ ቱሉ ዲምቱ አደባባይ ያለው የመንገድ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ሳቢያ ይደርስባቸው በነበረው እንግልት እሳቸውና የአካባቢው ነዋሪዎች በእጅጉ ሲማረሩ ኖረዋል።

በተለይ አቃቂ-ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አካባቢ የነበረው መንገድ በዝናብ ወቅት ጭቃማ፣ በጸሀይ ወቅት ደግሞ አቧራማ ሲሆን ፈተናው ከባድ እንደነበር ያስታወሳሉ፣ የመንገድ መዘጋጋቱ ደግሞ ሌላው ፈተና ነበር። ይህን ሸሽት ተሽከርካሪዎች በጋርመንት በኩል በፍጥነት መንገድ ማገናኛው መንገድ አማራጭ መጠቀም እንደነበረባቸው ጠቅሰው፣ በዚህ ሁኔታም ለአራት እና ለአምስት ዓመት ያህል ሰፊ የትራንስፖርት እንግልት ውስጥ መቆየታቸውን ያመለክታሉ።

በእነዚያ ሁሉ ዓመታት ከቤት ወደ ሥራ፣ ከሥራ ወደ መኖሪያ ስፍራ በጊዜ ለመንቀሳቀስ ለእነ አቶ ዳዊት በእጅጉ አዳጋች ነበር። አሽከርካሪዎችም ወደዚህ መስመር ለመምጣት ፈቃደኛ አልነበሩም፤ ተገልጋዩ ህብረተሰብም ባጃጅ ሳይቀር በአማራጭ ለመጠቀም እና አቆራርጦ ወደ ቤቱ እንዲሁም ወደ ስራው መሄድ እንደነበረበት ይገልጻሉ። ይህም ለተጨማሪ ወጪ ያጋልጥ እንደነበርም ነው ያመለከቱት።

ለእነ አቶ ዳዊት አሁን የመንገዱ ግንባታ በአብዛኛው በመጠናቀቁ የትራፊክ ፍሰቱ ሰላማዊ ሆኖላቸዋል። መንገዱ ክፍት ስለሆነ ረጅም መስመር የሚጭኑ ተሽከርካሪዎችን ማግኘት እየቻሉ ናቸው። ከነበረው ችግር አኳያ አሁን ያለው የመንገዱ ሁኔታ ምቹ እና በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑም በመስመሩ መንቀሳቀስ አቋርጦ የቆየው የአውቶብስ አገልግሎት ወደ ስራ መመለስ ጀምሯል፤ አዳዲስ አውቶቡሶችም ተመድበዋል። በመሆኑም የተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት እየታየ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በግንባታው እንዲሁም ግንባታው በተቋረጠበት ወቅት የትራፊክ ፍሰቱ የተጨናነቀ እንደነበር አስታውሰው፣ በጠዋት 12 ሰዓት ከቤት በመውጣት አርፍዶ ሥራ ቦታ የሚደረስበት ሁኔታ በርካታ እንደነበር ይገልጻሉ። አሁን ወደ ሥራ እና የተለያዩ ጉዳዮች እንዲሁም ወደ ቤት በጊዜ መድረስ እየተቻለ መሆኑን ተናግረው፣ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ፕሮግራም አድርገን በወጣንበት ሰዓት የፈልግንበት መድረስ እየቻልን ነው ሲሉ አቶ ዳዊት ይገልጻሉ።

አቆራርጠው ለመሄድ ሲሉ በተበላሹ መንገዶች ይጓዙ የነበሩ ተሽከርካሪዎችም ከጉዳት እየዳኑ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የመንገዱ ሙሉ ለሙሉ ለትራፊክ ክፍት መደረግ በመንገዱ አለመጠናቀቅ ሳቢያ በተሽከርካሪዎች ላይ ይደርስ ከነበረው ጉዳትና የመለዋወጫ ግዢ እንደሚታደጋቸው ያብራራሉ።

አሁን ነጋዴውም ሆነ ሌላው ማህበረሰብ ምርጫውን ወደ ቃሊቲ ቱሉዲምቱ መንገድ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ የንግድ ቤቶች ተፈላጊነትም እየጨመረ መሆኑን እና አካባቢውም የተሻለ እድገት ይኖረዋል የሚል እምነት



አቶ አስናቀ ሽመልስ፤

እንዳላቸው ተናግረዋል።

በመስመሩ በቂ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት እንደሌለ አቶ ዳዊት ጠቅሰው፣ በተለይ በሥራ መውጫ እና መግቢያ ሰዓት በቂ አውቶቡሶችና የትራንስፖርት አማራጮች አለመኖራቸውን ይገልጻሉ። በዚህ ሳቢያ አሁንም የተወሰነ እንግልት ይታያል ብለዋል።

በዚህ መንገድ ላይ የራይድ አገልግሎት ሲሰጡ ያገኘናቸው ለ15 ዓመታት ያህል በአሽከርካሪነት መሥራታቸውን የተናገሩት አቶ አስናቀ ሽመልስ በበኩላቸው፣ መንገዱ የወጪ ገቢ ትራንስፖርት የሚተላለፍበትና በርካታ የትራፊክ ፍሰት የሚያስተናግድበት መሆኑን ይገልጻሉ። መንግሥት ይህን አይነቱን መንገድ በፍጥነት ገንብቶ ወደ ስራ ማስገባት እና በወቅቱ መጠገን እንደነበረበትም ጠቁመዋል።

ይህ መንገድ ከግንባታ ጋር በተያያዘ በተጨናነቀበት ወቅት የጋርመንቱ መንገድ እያስተነፈሰው ነበር የሚሉት አቶ አስናቀ፣ የግራ መንገዱ ሙሉ በሙሉ በማይሰራበት ወቅት 10 ኪሎ ሜትር የማይሞላው መንገድ ከሁለት ሰዓት በላይ ጊዜ ይወስድ እንደነበርም ይገልጻሉ። ይህም ክልል የሚኬድበትን ያህል ጊዜ እንደሆነ ያብራራሉ። ለረጅም ጊዜ መንገዶቹ ተቆፋፍረው መጓዝ እስከማይቻልበት ደረጃ መደረሱን አስታውሰው፣ ቃሊቲ መናኸሪያ የሚል የራይድ ጥሪ ቢገባም ማንም አይቀበለውም ነበር ይላሉ። ይህ በመሆኑም ተጠቃሚውም ይጉላላል፤ ትራንስፖርት ማግኘት አይቻልም ነበር ሲሉ ያመለክታሉ። አሽከርካሪውም ጊዜውን፣ ገንዘቡን እንዲሁም ንብረቱን ያባክን እንደነበር ያስታውሳሉ። በሌላ አካባቢ ሁለት ሶስት ጉዞዎች ማድረግ የሚቻልበት ጊዜ እዚህ መንገድ ላይ ይባክን ነበር ብለዋል።

ለብዙ ዓመታት ከነበረው የመንገዱ ሁኔታ አኳያ አሁን ላይ ያለው ሁኔታ ጥሩ ነው የሚሉት አቶ አስናቀ፣ መንገዱ ግንባታው አልቆ ለትራፊክ ክፍት ቢደረግም፣ አሁንም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፓርኪንግ እንዲሁም የእግረኛ መንገድ ግንባታ አለመጠናቀቁ ለአደጋ ያጋልጣል ሲሉ አስገንዝበዋል፤ ሙሉ በሙሉ ባላለቀ አስፋፓልት ላይ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ መንገዱ ከወዲሁ እንዳይጎዳ ቀሪ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ሊጠናቀቁ ይገባል ነው ያሉት።

ቃሊቲ ቶታል አካባቢ ያገኘናቸው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የትራንሰፖርት ስምሪት እና ትራፊክ ቁጥጥር አስተባባሪ የሆኑት አቶ ደመላሽ ብርሃኑም ፤ የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ መንገድ መጠናቀቅ እና ለትራፊከ ክፍት መሆን የትራፊክ ፍሰቱን በተወሰነ መልኩ ማቀላጠፍ መጀመሩን በመግለጽ የአስተያየት ሰጪዎቹን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡

መንገዱ ላይ ለታከሲ ተብሎ የተዘጋጀ ማቆሚያ ተርሚናል አለመዘጋጀቱን በችግርነት ያነሳሉ፡፡ ተርሚናል



አቶ በለጠ ገብረማርያም ፤

አለመዘጋጀቱ ታክሲዎችን፣ ሀይገሮችን እና አውቶቡሶችን ለይቶ በየመስመራቸው ለማስተናገድ ግን ችግር እየፈጠረበን ነው ሲሉ ጠቅሰው፣ ተርሚናል ባለመኖሩ ተሳፋሪው ለመሳፈር ሲጋፋ እንደሚታይም ነው ያመለከቱት። በዚህ የተነሳ ስምሪቱን መቆጣጠር ሲገባን ከስራችን ውጪ ሰልፍ ወደማሰለፍ እየገባን ነው ሲሉ ይገልጻሉ። በዚህም ለአደጋ የመጋለጥ እድሉ ሰፊ መሆኑን ጠቅሰው፣ በመንገዱ ግራ እና ቀኝ በኩል መለስተኛ ተርሚናል ተከልሎ መስመር ቢሰመር የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአቃቂ ቃሊቲ ትራንስፖርት የቡድን መሪ አቶ በለጠ ገብረማሪያም በበኩላቸው መንገዱ የመውጫ በር እንደመሆኑ መጠን ብዙ ተጠቃሚ እንዳለው ጠቅሰው፣ በተለይ ብዙኃን ትራንስፖርት ላይ በሰፊው መሰራት እንዳለበት አመልክተዋል። በመስመሩ ከዚህ ቀደም የነበሩ 27፣ 110፣ 114 የአንበሳ አውቶቡሶች ወደ አገልግሎቱ ቢመለሱ አንዲሁም ሸገር ባሶች በብዛት እንዲመደቡ ጠይቀው፣ ተርሚናሉ የተሳለጠ እንዲሆን መስራት እንደሚገባ አመልክተዋል። ይህ ሲሆንም የትራንስፖርት እና ትራፊከ ፍሰቱን ይበልጥ የተሻለ ያደርገዋል ብለዋል። ተሳፋሪውም አውቶቡስ ቆሞ እያለ ታክሲ በመጠበቅ መሰለፍ እንደሌለበት ተናግረዋል።

ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁት አንድ አስተያየት የሰጡን ትራፊከ ፖሊስም የአስተያየት ሰጪዎቹን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ የመንገድ ግንባታው መጠናቀቅና ክፍት መደረግ የነበረውን ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ እያቀለለው መሆኑን ተናግረዋል። የመንገድ መብራት ዝርጋታ አለመጠናቀቅ፣ የመንገድ ምልክቶች አለመስራት፣ የፍጥነት ገደብ አለመኖር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የአሽከርካሪው መንገዱን ጠብቆ የማሽከርከር ችግር እና ለእግረኛ ግምት አለመስጠት እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮች መሆናቸውን አመልክተዋል።

መንገዱን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሞሀመድ አህመድ የቃሊቲ ማሰልጠኛ ቱሉ ዲምቱ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ተቋርጦ መቆየቱን አስታውሰው፣ ይህም የህብረተሰቡ የረጅም ጊዜ ቅሬታ መነሻ ሆኖ መቆየቱንና ቅሬታውም በከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ ምላሽ ማግኘቱን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉትም፤ አሁን የመንገዱ ግንባታ ተጠናቅቆ ለትራፊክ ክፍት ተደርጓል። በዚህም ህብረተሰቡ ደስተኛ ሆኗል። የትራፊክ መጨናነቁ፣ የተሽከርካሪዎች መጎዳቱ እና የህብረተሰቡ እንግልት እየተቀረፉ መጥተዋል። ቀሪ የእግረኛ መንገድ፣ የመንገድ መብራት እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎች እስከ ታህሳስ ወር ድረስ ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃሉ የሚል የመንግስት አቋም አለ። የመንገድ አካፋዩን አረንጓዴ የማድረግ ስራ ለማህበራት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው።

የአቃቂ አካባቢ አርሶ አደርም ምርቱን ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወስዶ ለመሸጥም ሆነ የኢንዱስትሪ ግብአቶችን ለማጓጓዝ የትራንስፖርት ፍሰቱ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ምርቶችንም ወደ ውጭ ለመላከ የመንገድ መሰረተ ልማቱ መጠናቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል። የመንገዱ ግንባታ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ላይ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው። የተሳለጠ መንገድ ሲኖር የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው የተሻለ ይሆናል፤ ሆቴሎች ወደ አካባቢው ይመጣሉ በቱሪዝም በኩልም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ሲሉም ያብራራሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚኒኬሽን ቢሮ አስተባባሪነት በከተማዋ ግንባታቸው እየተካሄደ ያለው የመንገድ ፕሮጀክቶች በመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ከትናንት በስቲያ በተጎበኙበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ እንደገለጹት፤ ለቃሊቲ ማሰልጠኛ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የሚውል ገንዘብ አበዳሪ የነበረው የቻይናው ኤግዚም ባንክ ለአምስት ዓመታት ብድሩን መልቀቅ ባለመቻሉ ግንባታው ለመጓተት ተዳርጎ ቆይቷል፤ ችግሩን ለመፍታት የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት የመንገዱን ግራ ክፍል ሙሉ በሙሉ የአንድ ዙር አስፓልት በማልበስ ለትራፊክ ክፍት እንዲሆን ተደርጓል።

መንገዱ ወደፊት ለብዙኃን ትራንስፖርት ማስተናገድ በሚያስችል መልኩ ለወደፊት ማስፋፋት እንዲያስችል መሀል ላይ 11 ሜትር ስፋት ቦታ የተተወለት መሆኑን ጠቅሰው፣ ጭስ አልባ ትራንስፖርትን ግምት ውስጥ በማስገባት በሁለቱም አቅጣጫ የሳይክል እና የእግረኛ መንገድን ግምት ውስጥ ያስገባ 6 ሜትር ስፋት ያለው ቦታ እንዳለውም ተናግረዋል።

መንገዱ በአጠቃላይ ስምንት መኪኖችን በሁለቱም አቅጣጫ ማስተናገድ የሚችል እና በሁለት ነጥብ አራት ቢሊየን ብር እየተገነባ የሚገኝ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰዋል። በ2016 ከጥር ወር በፊት ቀሪ ስራዎቹን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑንም አመላክተዋል።

ኢንጂነር ሞገስ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት በድምሩ ከ500 ቢሊየን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቁ መንገዶች ዲዛይኖች እየተሰሩ ናቸው። በሚቀጥሉት ዓመታት የመንገድ ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁም የትራፊኩን ፍሰት በማሳለጥ የመንገድ ደህንነትን በማረጋገጥ የጉዞ ወጪን እና ጊዜን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ያስችላሉ። የመንገድ መሰረተ ልማት ከሊህቅ እስከደቂቅ የሚስተናገድበት፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ብዜቱን የሚያፋጥን መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም የከተማ አስተዳደሩም ከፍተኛውን የካፒታል በጀት እየመደበለት መሆኑን ተናግረዋል።

የባለሥልጣኑ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እያሱ ሰለሞን በቅርቡ እንደገለጹት፤ 11 ኪሎሜትር የሚሸፍነው እና 50 ሜትር የጎን ስፋት ያለው የቃሊቲ-ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ፕሮጀክት በወሰን ማስከበር እና ከፋይናንስ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት በተለይ የመንገዱ ፕሮጀክቱ የግራ ክፍል ግንባታ ተጓትቶ ቆይቷል።

ከፕሮጀክቱ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድዮች አንዱ የሆነው ቃሊቲ ማሰልጠኛ ቀለበት መንገድ አካባቢ 140 ሜትር ርዝመት ያለው ተሻጋሪ የትራፊከ ማሳለጫ ድልድይ ግንባታ አስቀድሞ መካሄዱን ጠቅሰው፣ ድልድዩ የማጠናቀቂያ ሥራዎች እየተሰሩለት መሆኑን ገልጸዋል። መንገዱ የወጪ ገቢ ኮሪደር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የከተማዋዋን ደቡብ እና ምሥራቅ አቅጣጫ የትራፊክ ፍሰት በከፍተኛ ሁኔታ ማቀላጠፍ እንዲያስችል ተደርጎ መገንባቱን አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሠላም ተገቢውን ዋጋ በመስጠት ከግጭት እንውጣ!

ሠላም ለአንድ ማኅበረሰብም ሆነ ሀገር ከሚኖረው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ አንጻር ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ማኅበራዊ እሴት ነው። ስለ ሠላም የሚዘረጉ እጆችንም ሆነ፣ ለሠላም የተገዙ አስተሳሰቦችን ለመቀበልና ለመተግበር ፈቃደኝነት ማጣትም ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ከፍያለ ነው። ከዚህም የተነሳም ለሠላም ተገዥ መሆን ራስን ሊመጣ ካለ ጥፋት መታደግ ነው ። ይህ እውነት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እንደ አዲስ የሚነገር አይደለም። በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ላስከፈሉን ግጭቶችና ጦርነቶች ተዳርገን ብዙ ዋጋ ከፍለናልና።

ሠላም በትውልዶች መካከል ዘመን ላስቆጠረው ትልቅ ሀገርና ታላቅ ሕዝብ የመሆን መሻታችን መሠረት መሆኑን መረዳት ተስኖን፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችን መሠረት ያደረጉትን መከባበርና ይቅር መባባልን ዋጋ ሳንሰጥ በደነደነ ልብ ሀገርን አኬልዳማ ከማድረግ መታደግ ሳንችልም ቀርተናል።

ከዚህ የተነሳም የታሪካችን ሰፊው ትርክት የግጭት እና የጦርነት ሆኗል። መዘዙም በዓለም በድህነታቸውና በኋላቀርነታቸው ከሚጠቀሱ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ እንድንሆን አድርጎናል። ለብዙዎች የሚተርፍ ጸጋ ተሸክመን በሠላም እጦት ወደሚጨበጥ ሀብት መለወጥ ባለመቻላችን ተመጽዋች ሆነን ኖረናል። እንደ ትውልድም በራሳችን ታሪክ ቀና ብለን ለመሄድ የምንችልባቸው ብዙ ዕድሎችና ድሎች እያሉን በእዚህ ለመጠቀም እንዳንችል አድርጎናል።

ይህ ለሠላም ግንባታ የሚሆኑ ብዙ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ሆነን፣ እንደ ትውልድ ለእነዚህ እሴቶቻችን ተገቢውን ከበሬታ በማጣታችን እያጋጠመን ያለው የሠላም እጦት፣ ዛሬም ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ስለመሆኑ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን እያጋጠመን ያለው ፈተና፣ ፈተናው እየፈጠረብን ያለው ቁዘማ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ከትናንት ያልተገቡ ማኅበራዊ ትርክቶቻችን እየተቀዱ፣ ዛሬን እያበላሹብን ያሉት ልብ አደንዳኝ አስተሳሰቦችን አሁን ላይ ቆመን ማረም ካልቻልን፣ እንደ ሀገር አሁን ላይ ካለንበት ድህነትና ኋላ ቀርነት ሊያወጡን የሚችሉትን ዕድሎች በአግባቡ ተጠቅመን ወደ ምናስበው ዕድገትና ብልጽግና ልናመራ አንችልም።

የትኛውም አስተሳሰብ (ሀሳብ) በተቃርኖ የተሞላ፣ ይህም ተፈጥሯዊ መገለጫ መሆኑን በመገንዘብ የአስተሳሰብ ልዩነቶችን እንደ ጸጋ መቀበል የሚችል የአእምሮ ውቅር መፍጠር፣ ይህም የትውልዶች የአስተሳሰብ መሠረት የሚሆንበትን መንገድ መፍጠርና በመንገዱ በመጓዝ በተጨባጭ ተሞክሮ የታጀበ የአዲስ የወንድማማችነትና እህትማማችነት ትርክት ልንፈጥር ይገባል።

በተለይም አሁን እንደ ሀገር ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ካለን ሀገራዊ መሻት፣ መሻቱ ከፈጠረው ሕዝባዊ ንቅናቄ አንጻር፣ ስለ ሠላም ያለንን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ እንደ ሕዝብ ለሠላም መክፈል ያለብንን መስዋዕትነት በቁርጠኝነት በመክፈል ከመጣንበት የግጭት አዙሪት ልንወጣ የሚያስችለንን ሀገራዊ እውነታ ፣ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅብናል!፡፡

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አትሌቲክሱ«አንዱን ጥሎ፣ አንዱን አንጠልጥሎ» እንዳይሆን

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ኢትዮጵያ ከስያሜዋ በስተጀርባ በወርቅ የደመቀ የአኩሪ ታሪክ ባለቤት ናት፡፡ ይህች ድንቅ ሀገር ዘመናትን የተሻገረው የጀግንነት ገድሏ ከበርካታ ጎራ ያሰልፋታል፡፡ በቅኝ ያለመገዛቷ እውነት ከራሷ የማንነት አውድ አሻግሮ ለመላው አፍሪካ የማይፈዝ የነፃነት ዐሻራውን አሳርፏል፡፡

ሀገራችን ከዚህ የማይፋቅ ታሪኳ ባሻገር ስሟን በክብር ከፍ የሚያደርግ ሌላም ታሪክ አላት፡፡ ዓመታትን ያለድካም የዘለቀው የአትሌቲክሳችን ስፖርት፡፡ ይህን የኢትየጵያውያንን ታሪክ ደጋግመን ስናወሳ አይረሴው እውነት ዓመታትን የኋሊት ይመልሰናል፡፡ ወደ ፈረንጆቹ ወርሀ መስከረም 1960፡፡

በዚህ ዘመን አፍሪካ ከቅኝ ግዛት ዕንቅልፏ በወጉ አልነቃችም፡፡ ጥቂት የሚባሉት ሀገራትም ካረፈባቸው የምዕራባውያን የጡጫ ሕመም ያላገገሙበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ ስሜት ግን በመላ ኢትዮጵያውያን ውስጠት ፈጽሞ አይታወቅም፡፡ እንዲህ ይሆን ዘንድ ታላቅ መስዋዕትነት ተከፍሏልና በነፃዪቱ ሀገር የነፃነት አየር በነፃነት እየነፈሰ ነው፡፡

በሌላው ገጽ ደግሞ በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ ሌላው አዲስ ምዕራፍ ሊከወን መንገድ ይዟል፡፡ ነፃነትን በመንጠቅ ድንበር ጥሰው፣ ባህር ተሻግረው በመጡት ባዕዳን ምድር፡፡ ቅኝ ሊያስገዙ፣ አቅም ሊነፍጉ በሞከሩት ጣሊያኖች መሬት ሮም ከተማ ፡፡

በዚህ ቀን ፀሐይ ከመጥለቋ አስቀድሞ አንድ ታላቅ ፍልሚያ ሊካሄድ ጊዜው ደርሷል፡፡ ከመላው ዓለም የተውጣጡ ዝነኛ የማራቶን ሯጮች ውድድሩን ሊጀምሩ በመሟሟቅ ላይ ናቸው፡፡ በሁሉም ገጽታ የአሸናፊነት ስሜት እየተነበበ ነው፡፡ ከሰዓታት በኋላ ምን እንደሚፈጠር ማንም የሚያውቅ የለም፡፡

በወቅቱ በነበሩት ውድድሮች ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፎች ሜዳሊያ ይሉትን አልወሰደችም፡፡ መላው አፍሪካም እንደዚያው፡፡ ነገሩ ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢመስልም ውድድሩ ገና አልተቋጨም፡፡ በዕለቱ ለተወዳዳሪዎች የሚሆኑ ምቹ ጫማዎች ታድለው አልቀዋል፡፡ ሁሉም ለእግሩ የሚመቸውን መጫሚያ አጥልቆ እየተቁነጠነጠ ነው፡፡

ከሁሉም ተወዳዳሪዎች መሀል ይህ ያልተሟላለት ኢትዮጵያዊው አትሌት አበበ ቢቂላ ነገሩ ያስገረመው አይመስልም፡፡ የአዲዳስ ኩባንያው ተወካይ ለእሱ እግር የሚገጥም ጫማ አለመኖሩን በግልፅ አርድቶታል፡፡ ይህ ቃል ግን ለአበበ ትርጉም እየሰጠው አይደለም፡፡ ፈጽሞ ተስፋ አልቆረጠም፡፡ ወሳኙን ፍልሚያ በባዶ እግሩ ሊያካሂድ ከራሱ ጋር መክሮ፣ ዘክሮ ከውሳኔ ደርሷል፡፡

ይህን እውነት ለሚሰሙት ሁሉ የማይዋጥ ሀቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢትዮጵያዊው ግን ከራሱ ተማምሎ ጨርሷል፡፡ ምናልባትም ለእሱ በባዶ እግር መሩለም አዲስ አይደለም።ይህ ታሪክ የአያት ቅድመ አያቶቹ ነው፡፡ ጠላትን ድል የነሱት የወታደር ጫማ አጥልቀው አልነበረም። ለሀገራቸው ክብር በዱር በገደሉ እሾህ ጋሬጣው አድምቷቸዋል፡፡

እነሆ! አሁንም ጊዜው ራሱን ደግሟል፡፡ በወራሪዎቹ ምድር የባዶ እግር ታሪክ ዕውን ሊሆን ደቂቃዎች እየተቆጠሩ ነው፡፡ አሁን አበበ እግሮቻቸው በምቹ ጫማዎች ከረገጡ ተወዳዳሪዎች ጎን በቁርጠኝነት ተሰልፏል፡፡ በመወደሪያ ትራኩ ጫማ አልባ እግሮች ለሩጫ እንደተዘጋጁ ናቸው። ሁሉም ይህን እያስተዋለ በንቀት ፈገግታ ተውጧል። በድንገት ታላቁ የማራቶን ውድድር መጀመሩን የሚያበስረው ሽጉጥ ተተኮሰ፡፡

በርካታ ጥንድ እግሮች በፍጥነት ተፈተለኩ፡፡ በእኩል የሚራመዱ ቅልጥሞች፣ ጥቁርና ነጭ ታፋዎች፣ መንትያ መሳይ ጫማዎች ጎልተው ተስተዋሉ፡፡ ከሁሉም ተነጥለው የሚታዩት የአበበ ቢቂላ ባዶ እግሮች ፈጽሞ አልሰነፉም፡፡ ፈጥኖ እንደሚሰግር ፈረስ ወደፊት ነጎዱ፣ ገሰገሱ፡፡

አበበ የሚፋለመው ከራሱ ጋር ሆኗል፡፡ ስለ ባለጫማዎቹ ሯጮች ፈጽሞ የሚያስብ አይመስልም፡፡ አሁንም ትንፋሹን ሰብስቦ፣ ፊቱን አቀጭሞ እየጋለበ ነው፡፡ ከበስተጀርባው በርካታ ትከሻዎች አጅበውታል፡፡ ሁሉም አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የለበሰውን ጥቁር አንበሳ በፍርሀት እየከተሉት ነው። የዓለም ዓይና ጆሮ በእሱ ላይ አተኩሯል፡፡

አበበ በማይታመን ፍጥነት በርካቶችን ከኋላው አስከትሎ የአርባ ሁለት ኪሎሜትሩን ውድድር ሊያጠናቅቅ ተቃርቧል፡፡ ሽንፈት፣ ተስፋ መቁረጥና ድካም በአይታመኔ አሸናፊነት እንደታጀቡ የባዶ እግር ዐሻራ ከመጨረሻው ትራክ ደርሷል፡፡ ጭብጨባው እንደጋለ ነው፡፡ ተመልካቹና ጋዜጠኞች አብዝተው ይጮሀሉ፡፡

የኋላ ኋላ ምሽቱ በድል ብርሃን ታጀበ፡፡ ባለ ባዶ እግሩ ኢትዮጵያዊ ጀግና አበበ ቢቂላ ዓለምን ጉድ አሰብሎ እጅን በአፍ አስጫነ፡፡ የመጨረሻዋ ክር በፈርጣማ እጆች ስትበጠስ ኢትዮጵያ በሮም አደባባይ ዳግም አሸነፈች። አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ከፍ ብሎ ተውለበለበ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በጣሊያኖች አጀብ ጎልቶ ተሰማ፣ ደማቁ የድል ብስራት በመላው ዓለም አስተጋባ፡፡

እነሆ በዚህ የተጀመረው አስደናቂ ገድል እርምጃውን አልገታም፡፡ ከዓመታት በኋላ በሀገረ -ቶኪዮና ሜክሲኮ አበበ ዳግም ድልና በማሞ ወልዴ የማራቶኑ ድል ተደጋግሟል፡፡ ጥንካሬና ድል የኢትዮጵያውያን ስያሜ እስኪመስል ማራቶን ዘመናትን ተሻግሮ በእነ ገዛኸኝ አበራም ኦሊምፒክ ላይ ከፍ ብሎ ነገሰ፡፡

ይህ የአትሌቲክስ ድል በማራቶን ብቻ አልተገታም። የኢትዮጵያውያን ብቃት የሚታወቁበት የረጅም ርቀት 5ሺ እና 10 ሺህ ሜትር ውድድር ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ገናና ሆና መታየት ያዘች፡፡ በአንጻሩ ኬንያ ደግሞ በመካከለኛና ረጅም ርቀት ውድድር እውቅናውን አገኘች፡፡ የሁለቱ ሀገራት የአንገት ለአንገት ትንቅንቅ በመላው ዓለም ትኩረትን ሳበ፡፡

የኬንያና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተለይተው በሚታወቁባቸው ውድድሮች አሸናፊነትን መነጣጠቅ ልምዳቸው ሆነ፡፡ በ2019 የዶሀ የዓለም ሻምፒዮና የ3ሺ ሜትር መሰናክል ኬንያዊው ኪፕሮቶ ለሜቻ ግርማን በሽርፍራፊ ማይክሮ ሰከንዶች በልጦ አሸናፊነትን ያዘ፡፡

ለሜቻ በ3ሺ መሰናክል ለኢትዮጵያ የብር ሜዳሊያ ያስገኘ የመጀመሪያው አትሌት ነው፡፡ በተመሳሳይ በኬንያዊቷ ፌይዝ ኪፕየጎን እና በጉዳፍ ጸጋዬ የ1ሺ 500 ሜትር ውድድር አሁንም ኬንያ ብቸኛውን ወርቅ ያገኘችበትና ኢትዮጵያ የብር ሜዳሊያ የወደሰችበት አጋጣሚ ሆኖ ተመዘገበ፡፡

በ2019 በኳታር ዶሀ በነበረው የዓለም ሻምፒዮና ኢትዮጵያ ሁለት ወርቅ፣ አምስት ብርና አንድ ነሐስ ማግኘት ችላለች፡፡ በ1992 ዓ.ም በባርሴሎና በተካሄደው የ10ሺ ሜትር ውድድር ደራርቱ ቱሉ ለሀገሯ ወርቅ አስገኝታለች፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት 18 የዓለም ሻምፒዮናዎች በማራቶን 12 ሜዳሊያዎችን ወስዳለች፡፡ በዘንድሮው ዓመት በሀንጋሪ ቡዳፔስት በተካሄደው 19ኛው የዓለም ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በሴቶች ማራቶን የወርቅና ብር ሜዳሊያን ነጥቃለች፡፡ በተመሳሳይ በወንዶች ማራቶን ውጤታማ እንደምትሆን ቢጠበቅም በልዑል ገብረሥላሴ አንድ የነሐስ ሜዳሊያ ብቻ ማግኘት ተችሏል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት ሻምፒዮናዎች በእያንዳንዱ ውድድር የወርቅና ብር ሜዳሊያዎችን ያጠለቁት አትሌቶች ዘንድሮ ከአሸናፊነት ጥግ መድረስ አልተቻላቸውም። ምንም እንኳን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ማሸነፍ ማለት ወርቅ ማጥለቅ ብቻ ቢመስለንም የዘንድሮው ውጤት ድሉን ስለማፍዘዙ ግን መሸፋፈን አይቻልም፡፡

ኢትዮጵያውያን ገነው በሚታወቁበት የ5 ሺህ ሜትር ፍጻሜ በሁለቱም ፆታ አሸናፊነት ሳይቀናቸው ቀርቷል፡፡ ዮሚፍ ቀጀልቻን ጨምሮ፣ ሀጎስ ገብረሕይወትና በሪሁ አረጋዊ ውድድሩን እንደተጠበቀው በድል አልፈጸሙም። ይህ ቀደምት ታሪክ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የመካከለኛ ርቀት አትሌቶች ድል መሆን ጀምሯል፡፡

ይህ ክፍተት በሴቶቹም ተመሳሳይ ርቀት እየተስተዋለ መምጣቱን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በ3 ሺህ መሰናክል የሴቶች ፍጻሜ ዘርፌ ወንድማገኝ አራተኛ ስትሆን በትውልደ ኬንያዊቷ የባህሬን አትሌት ያቪ ዊንፍሬድ ወርቁ ሲወሰድ ኬንያውያኑ ብርና ነሐሱን ተጋርተውታል፡፡

በዘንድሮው የሀንጋሪ ውድድር የታየውን የአትሌቲክስ ክፍተት ከወዲሁ መደፈን ይገባል፡፡ እንዲህ መሆን ካልቻለ ሀገርን ከወጣችበት የክብር ከፍታ ዝቅ ሊያደርግ የሚችል መንገራገጭ እንደሚኖር ምልክቱ እየታየ ነው፡፡ የአትሌቲክሱ መንደር ራሱን ይፈትሽ፡፡ አሁንም ትኩረት፣ አስተውሎትና የጋራ ምክር ሊኖር ይገባል፡፡

እነሆ! አትሌቶቻችን ውድድሩን አጠናቀው ወደሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ ዛሬም ኢትዮጵያ ስለጀግኖቿ ታላቅ ክብር ትሰጣለች፡፡ እነሱ ውስጥ ጥንካሬ ብርታትና ጀግንነቱ እንደሚቀጥል ተስፋ አለ፡፡ እንደ ኬንያ ያሉ የቅርብ ተፎካካሪዎቻችን በአዳዲስ የአጭር ርቀት ውድድሮች ጭምር ተፎካካሪ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያም በተለይም እንደ 3ሺ ሜትር መሰናክል ባሉ ርቀቶች አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍታለች፡፡ ይህ ብቻውን ግን ስኬት አይደለም፡፡ የቀደመው ውጤታማነት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንጂ ቦታውን መልቀቅ የለበትም፣ የውጤት ደረጃውም ሊዥጎረጎር አይገባም፡፡ አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ የስኬት ጉዞ ጎዶሎ ይሆናልና፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ነገን - በጭላንጭል

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አዲሱ ዓመት ተቃርቧል፡፡ ሁሉም በየቤቱ ስለጓዳው ማሰብ እየጀመረ ነው፡፡ ዓውደ ዓመት በመጣ ቁጥር ይህን ማቀዱ ብርቅ አይደለም፡፡ በተለይ ጊዜው አዲስ ዓመት ከሆነ ዝግጅቱ ለየት ይላል፡፡ ይህ በዓል ሁሌም የጋራ ነው፡፡ ሀይማኖት፣ ወገን አይመርጥም፣ ሰው ከሰው አይነጥልም፡፡ ሁሉም በእኩል ተቀብሎ በአንድ ያከብረዋል፡፡

እነሆ ! በዚህ ጊዜ እናቶች ጓዳቸውን ያስባሉ። አባወራዎችም ግዴታቸውን አያጡትም፡፡ ስለ ቤታቸው፣ ስለቤተሰባቸው ሲሉ ከበጉ፣ ከቅርጫው፣ መንደር፣ አይጠፉም፡፡ ልጆች ደግሞ የልምዳቸውን ያውቁታል። አዲሱ ዓመት ሁሌም ገዳቸው ነው፡፡ ከአዲስ ልብስ፣ ከአዲስ ጫማ ያገናኛቸዋል፡፡ ይህን ጊዜ ሲጠብቁት በአዲስ መንፈስ ጓግተውና ናፍቀው ነው፡፡

ወይዘሮ ዓለም ድረሴ በእስከዛሬዎቹ ዓመታት ከእነዚህ እውነታዎች አልራቁም፡፡ አዲስ ዓመት ለእሳቸው የአዲስ መንፈስ ጅማሬ ነው፡፡ ዓመቱን ለፍተው፣ ደክመውበት ሲጠናቀቅ የላባቸውን ይቋጥሩበታል፡፡

ይህ ጊዜ የለፉበት፣ የደከሙበትን ጊዜ አሳልፎ ከአዲስ መንገድ ሲያደርሳቸው ኖሯል፡፡ ሁሌም ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ እንደበታቸው በምስጋና እንደተሞላ ነው፡፡ ደጋግመው ‹‹ተመስገን›› ይላሉ፡፡ ዝናቡን፣ ዶፉን፣ ጨለማውን ወስዶ ከብራው፣ ከጸሀዩ ያደረሳቸውን ፈጣሪ አብዝተው ያመሰግናሉ፡፡

**ወይዘሮዋና ዘንድሮ**

ዓለም ዘንድሮ እንዳለፉት ዓመታት ደስተኛ አልሆኑም። አንድ ጉዳይ ውስጣቸው ገብቷል፡፡ በየቀኑ ሀሳብ ያስጨንቃቸዋል፡፡ አሁን በዓል ዓውደ ዓመቱ ጉዳያቸው አልሆነም፡፡ ከእሱ አልፎ ስለነገ አብዝተው ያስባሉ፡፡ ምን እሆናለሁ? የት እደርሳለሁ? ይሉት ጉዳይ አብሯቸው መዋል ማደር ከያዘ ሰንብቷል፡፡ ይተክዛሉ፣ ያስባሉ፣ ይጨነቃሉ፡፡

ዘንድሮ እንደቀድሞው ዳቦውን፣ ዶሮውን የሚሉበት አቅም ከእሳቸው የለም፡፡ ጓዳቸውን ሞልተው፣ ጎረቤቱን፣ ወዳጅ ዘመዱን አይጠሩም። ዓመቱን መሻገራቸው፣ ሰላም መድረሳቸው እንደ ሁልግዜው አመስጋኝ አድርጓቸዋል፡፡ የሆነባቸውን ሲያስቡት ግን እጅግ ይከፋሉ፡፡ አሁን ነገሮች ከአቅማቸው በላይ እየሆኑ ነው፡፡

ወይዘሮ ዓለም የጉልት ነጋዴ ናቸው፡፡ ለዓመታት በቤት ኪራይ ኖረዋል፡፡ ሁለቱ ልጆቻቸው ከእሳቸው ጋር ክፉ ደግ ያሳለፉ ናቸው፡፡ ያለ አባት ሲያሳድጓቸው የአቅማቸውን አድርገው፣ የእጃቸውን አሟልተው ነበር። ከጊዜያት በኋላ ግን ትከሻቸው አልቻለም፡፡

አንደኛው ልጅ ከዘመድ ቤት ተጠግቶ እንዲኖር ወሰኑ። እንዲያም ሆኖ ዝም አላሉም፡፡ ሰው እንዳያስቸግር፣ እሱም እንዳይቸገር የአቅማቸውን መሸንጥ ያዙ፡፡ ለጊዜው በመጠኑ ሀሳብ ቀለለ፡፡ ከሴቷ ልጅ ጋር ህይወት በመልካም ቀጠለ፡፡ ኑሮ ቢከብድም አላማረሩም፡፡ ከጉልታቸው እየዋሉ በምስጋና አደሩ፡፡

ዓለም ጉልት ሲሸጡ የሚይዙት ብዙ አይደለም። የእጃቸው ሲያልቅ በመጠኑ አምጥተው ደንበኞችን ይጠብቃሉ፡፡ እንደሌሎች በርከት ለማድረግ አቅሙ የላቸውም፡፡ እንደምንም የጠረቃቸውን ገቢ አንድ ሁለት ብለው ለቤት ኪራይ ያውላሉ፡፡

አንዳንዴ ገበያ እንደታሰበው አይቀናም፡፡ ከእሳቸው ይልቅ ገበያተኛው የተሻለውን ይመርጣል፣ ያማርጣል። እንዲህ ሲያጋጥም ፀሀይ ሲመታቸው ውሎ የረባ ሳይሸጡ ይገባሉ፡፡ ማግስቱን ከያዙት የጉልት አትክልት የተበላሸውን ይጥላሉ፡፡ የተረፈውን መራርጠው መንገደኛውን፣ ደንበኞችን ይናፍቃሉ፡፡

ሁሌም ዓይን ዓይን የሚያዩበት ገበያ እንደታሰበው ላይቀና ይችላል፡፡ ጠያቂ ከተገኘ ከምርቃቱ ጨማምረው፣ ካለው አክለው ለነገው ያስባሉ፡፡ እንደወጡት ከቀናቸው ‹‹እሰየው›› ነው፡፡ የያዙትን ይዘው በምስጋና ያድራሉ፡፡

ዓለምና የጉልት ስራ እንዲህ ሲደጋገፉ ዓመታትን ዘልቀዋል፡፡ ከዚህ ቀድሞ ልጆች ለማሳደግ ያልሰሩት፣ ያልሞከሩት አልነበረም፡፡ ከሰው ቤት እየዞሩ ልብስ አጥበዋል፣ እንጀራ ጋግረዋል፡፡ አሻሮ ቆልተዋል፡፡ የሚያገኙት ጥቂት ገንዘብ በወቅቱ ቤታቸውን ደግሞ ልጆችን አስተምሯል፡፡

ይህ አይነቱ ሥራ ከብዙዎች አገናኝቶ አስተዋውቋቸዋል። ቆይቶ ግን አቅማቸውን ፈተነው። ከእሳት ጋር ውሎ ማምሸቱ ለጤናቸው ጠንቅ ቢሆን አማራጮች ፈላለጉ፡፡ የኑሯቸው ሁኔታ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ዛሬን ልረፍ፣ ነገን ልተው አይሉበትም፡፡ እያመማቸው፣ እየተቸገሩ ለህይወታቸው ታገሉ፡፡ አንድ ቀን ግን ራሳቸውን ከጉልት ገበያ ውስጥ አገኙት፡፡

ዓለም ስራውን አልጠሉትም፡፡ ካሳለፏቸው የድካም ዓመታት የጉልቱ ውሎ የተሻለ ሆነ፡፡ እንዲያም ሆኖ ስራው ስጋት አለው፡፡ የሚይዙት ዕቃ ከአቅማቸው የመጠነ ነው። ‹‹አብልጨ ልሸጥ›› ካሉ ጥሩ መነሻ ይፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ አይችሉም፡፡ እንዲህ ካልሆነ ደግሞ የቤቱ ነገር ይጎድላል፡፡ የገቢው ጉዳይ ያሳስባል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በየቀኑ ስራው ሕጋዊ አይደለም የሚሉ ደንብ አስከባሪዎች ምቾት አይሰጧቸውም። የያዙትን ዘርግተው ቁጭ ከማለታቸው ቆመጥ የያዘ፣ አንድ አይነት የለበሰ ግብረኃይል ደርሶ ድራሻቸውን ያጠፋዋል፡፡ አንዳንዴ ችግሩ በዚህ አያበቃም፡፡ ደንቦቹ ድንገት ከደረሱ የጉልቱን አትክልት ከመሬቱ፣ ከጭቃው ቀላቅለው ይበትኑታል፡፡ ቀርቦ ልለምን፣ ልማጸን የሚል ካለ ምላሹን ከዱላ ያገኘዋል፡፡

ወይዘሮ ዓለም ይህን አጋጣሚ ደጋግመው አልፈውታል። ብዙ ግዜ ከደንቦች ተሯሩጠው የእጃቸውን ተነጥቀዋል፡፡ አልቅሰው፣ አንብተው፣ ከእግር ወድቀው አስመልሰዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ ታግለው ቤት ሲደርሱ ስለ ነገው ይጨነቃሉ፡፡ ዛሬን ካላሰቡ ነገ ይደርስባቸዋል፡፡ ይህ የጉልት ቸርቻሪዋ ወይዘሮ ዓለም የየዕለት ገጠመኝ ነው፡፡

**የቀን ደግ**

ከቀናት በአንዱ ይህን ችግር የሚፈታ በጎ

... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የመርሳት ህመም (Dementia)

ሁላችንም ማለት በሚቻልበት ሁኔታ በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች ነገሮችን እንረሳለን፡፡ ለመርሳታችን በዋነኝነት እንደምክንያትነት የሚጠቀሰው፤ ለነገሮች ትኩረት ሰጥተን ባለመከታተላችን እንደሆነ ይገመታል። ነገር ግን ምን ያህሎቻችን ነን ይህ የመርሳት ወይም የመዘንጋት ችግር ደረጃው ከፍ ካለ ህመም ሊሆን እንደሚችል የምናውቀው? በዛሬው እትማችንም በስፋት የምናነሳው ስለዚሁ የመርሳት ህመም ወይም በህክምና አጠራሩ ዴሜንሽያ ነው፡፡

የመርሳት ህመም ከአዕምሮ ህመሞች አንዱ ሆኖ ቀስ በቀስ የማስታወስ ችሎታን የሚቀንስ የህመም አይነት ነው፡፡ ህመሙ በብዛት የሚከሰተው በእድሜ የገፉ ሰዎች ላይ ይሁን እንጂ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ግለሰቦችም ሊያጠቃ ይችላል፤ ነገር ግን በዕድሜ ከገፉት አንፃር ሲታይ ሥርጭቱ አነስተኛ ነው፡፡
ህመሙ ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ በሆኑ ግለሰቦች ላይ እስከ አምስት በመቶ የሚሆኑትን የሚያጠቃ ሲሆን እድሜያቸው ከ85 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ ደግሞ ከ20 እስከ 40 በመቶ የሚሆኑትን ሊያጠቃ ይችላል፡፡ አሁን ላይ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶችም እንደሚያሳዩት፤ በዓለም ላይ ከ55 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የመርሳት ህመም አለባቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆኑት አነስተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ በየዓመቱም 10 ሚሊዮን የሚሆኑ አዳዲስ ሰዎች በመርሳት ህመም ይጠቃሉ፡፡

ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ በእድሜ የገፉ ሰዎችም ቁጥር እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ እ.ኤ.አ በ2030 የመርሳት ህመም የሚያጋጥማቸው ሠዎች ቁጥር ወደ 78 ሚሊዮን ከፍ እንደሚልና በ2050 ደግሞ 139 ሚሊዮን እንደሚደርስ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡
ለመርሳት ህመም የሚያጋልጡ የተለያዩ የህመም ዓይነቶች ቢኖሩም ብዙዎቹ ግን የዕድሜ መግፋትን ተከትሎ የሚመጡ ናቸው፡፡ ለህመሙ እንደመነሻ ከሚጠሱት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉትን ለአብነት ማንሳት እንችላለን፡፡




- **የአልዛይመር ህመም፡-** ይህ ህመም በዋናነት የሚመጣው በአንጎል ውስጥ የተለያዩ የማይፈለጉ ፕሮቲኖች ጥርቅም ከመፈጠራቸው ጋር ተያይዞ በሂደት ጤናማ የአንጎላችን ህዋሳት በሚገባ ስራውን እንዳያከናውኑ ሲያደርግ ነው፡፡ የአልዛይመር ህመም ለመርሳት ህመም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡
- የኤች አይ ቪ ኤድስ ህመም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተጓዳኝ በሽታዎች በማጋለጥ የአንጎል ህዋሶችን በአግባቡ ስራቸውን እንዳያከናውኑ በማድረግ የመርሳት ህመምን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- አንጎላችን ተደጋጋሚ አካላዊ ጥቃት ሲደርስበት፡ - ለምሳሌ ቦክሰኞች በተደጋጋሚ የጭንቅላት ምት ከደረሰባቸው ለመርሳት ህመም ተጋላጭነታቸውን ይጨምረዋል፡፡
- ከሌሎች የአዕምሮ ህመሞችና ከድባቴ ህመም ጋር ተያይዞ የሚመጣ የመርሳት ህመምም አለ፡፡
- ለህመሙ አጋላጭ የሆኑ ሌሎች አካላዊ ህመም አይነቶች ውስጥ የቪታሚን እጥረት፤ የእንቅርት ህመም፤ የደም መርጋት ችግር፤ የተለያዩ የአንጎል ዕጢዎችና የመሳሰሉ ህመሞች በተለይ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ለመርሳት ህመም የሚያጋልጡና በህክምና ለውጥ ሊመጣባቸው የሚችሉ የአካላዊ ህመም አይነቶች ናቸው፡፡
- ለረዥም ጊዜ ማጨስና አልኮልን አዘውትሮ መጠጣትም ለህመሙ ተጋላጭነትን ይጨምራል፡፡
- በዘር ሀረግ ውስጥ የዚህ ህመም ተጠቂ ካለም የቤተሰቡ አባላት ለህመሙ ተጋላጭነታቸው እንደሚጨምር የሚያሳዩ ጥናቶች አሉ፡፡

**የህመሙ ምልክቶች**

- **የመርሳት ችግር፡-**ይህ ያስቀመጡትን እቃ ከመርሳት ጀምሮ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሥም እስከ መርሳት ሊደርስ የሚችል ሲሆን ጥቂቶቹ ያስቀመጡትን ዕቃ፣ ቀጠሮ፣ እቃ ገዝቶ መልስ መቀበልና የሚያውቁትን ሰው ስም መርሳት ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡
- **ግራ መጋባት፡-** ያሉበትን ቦታ በቀላሉ መረዳት ስለሚሳናቸው ከቤት ወጥቶ በዛው መቅረት ወይም ወደ መኖሪያ ቤታቸው መመለስ አለመቻል
- ለብዙ ዓመታት ሲጠቀሙት የነበሩትን ዕቃ ለመለየት መቸገር
- ለመናገር ፈልገው ቃላቶችን ማጣት ወይም ቃላቶችን ፈልገው ለማግኘት ብዙ ጊዜ መፍጀት
- ከህመሙ በፊት በየቀኑ በቀላሉ የሚያከናውኗቸውን ስራዎችን ለማከናወን መቸገር፡-
- ለምሳሌ ጫማ ማሰር፣ ቁልፍ መቆለፍና የመሳሰሉ ነገሮች ለማከናወን ይቸገራሉ፡፡
- በተጨማሪም ያለምክንያት መዞር፤ ቁጡ መሆንና በጩኸት መናገር፤ ተጠራጣሪ መሆን፤ ለሌላ ሰው የማይሰሙ ድምፆች፣ የማይታዩ ምስሎች መከሰትና እንቅልፍ ማጣት ሊታዩባቸውም ይችላል፡፡

**ለታማሚዎች ሲደረጉ የሚገቡ እንክብካቤዎችና ጥንቃቄዎች**

አንድ በዕድሜ የገፋ የቤተሰብ አባል የማስታወስ ችሎታው እየቀነሰ ሲመጣና ከተለመደ ባህሪይ ወጣ ያለ ባህሪይ ማሳየት ሲጀምር ቶሎ ወደ ህክምና ተቋም መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ ግለሰቡ መፃፍና ማንበብ የሚችል ከሆነ ከግለሰቡ መኖሪያ ክፍል ውስጥ የግድግዳ ሠዓት ወይንም የቀን መቁጠሪያ ካሌንደር ቢኖር ይመረጣል፡፡

ታማሚው የሚንከባከቡ ግለሰቦችና የሚኖርበት ክፍል ቶሎ ቶሎ ባይቀያየር ይመረጣል፡፡ የማታ እንቅልፋቸውን ለማሻሻል ቀን ላይ እንዳይተኙ፣ የማታ ፀሃይ እንዲሞቁ ወይም ወደ ማታ አካባቢ በሙቅ ውሃ እንዲታጠቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ህሙማኑ ከቤት ወጥተው እንዳይጠፉ የግቢ በር መቆለፍና ቁልፉን ከበሩ ላይ ማንሳት፣ ድንገት ከጠፉ በቀላሉ ለማግኘት እንዲጠቅመን በልብሳቸው ላይ ስልክ ቁጥራችንን መፃፍ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሚያበሳጩ ሁኔታዎች ማራቅና አለማበሳጨትም አስፈላጊ ነው፡፡

# ነገን -...

ከ16ኛ ገጽ የዞረ

ቀን ነጋላቸው፡፡ ለወይዘሮ ዓለም በመሳቀቅ ለሚሯሯጡበት ህይወት መፍትሄው ተገኘ፡፡ እሳቸውን ጨምሮ ሌሎች ‹‹ህገወጥ ናችሁ›› የተባሉ በሚመለከታቸው አካላት ማረጋገጫ ‹‹ህጋዊ ሆናችኋል›› ተባሉ፡፡ በሁሉም ዘንድ ደስታ ነገሰ፡፡ እፎይታም ሆነ፡፡

እንዲህ መሆኑን ተከትሎ ሁሉም የጉልት ሴቶች በቡድን ተደራጁ፣ የሥራ ቦታም ተሰጣቸው፡፡ ወዲያው በደረታቸው ባጅ አንጠልጥለው፣ ህጋዊ ግዴታን ተከተሉ፡፡ ጊዜ ቆጥረው፣ ግብር መክፈል፣ ኃላፊነት መወጣት ያዙ፡፡ ያለ ችግር ሽንኩርት ቲማቲም፣ ድንች፣ ጎመን መሸጥ፣ መቸርቸር ያዙ፡፡

ዓለም እንደሌሎች ባይሆንም በአቅማቸው ገዝተው መቸርቸር ልምዳቸው ሆነ፡፡ ብዙ ባያተርፉም ለቤት፣ ለጓዳቸው አላጡም፡፡ በምሥጋና ውሎ ማደር፣ ነገን በተስፋ መጠበቅ ልምዳቸው ሆነ፡፡ ኑሮ እንዳሰቡት ባይሞላም አልከፋቸውም፡፡ ያላቸውን አቻችለው፣ ፈጣሪን አመስግነው ህይወትን ቀጠሉ፡፡

**«ነበር« እንደዋዛ!**

ቀናት፣ ወራት ዓመታት በጎ ሆነው አለፉ፣ ያለችግር ስጋት የተራመዱባቸው መንገዶች ለወይዘሮ ዓለም ነገን አሻግረው አሳይዋቸው፡፡ የዛሬን ይዘው የትናንቱን አሰቡት፡፡ ስራን አጥብቀው ከያዙት መጪው ጊዜ እንደማይከብዳቸው ገመቱ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በፊት ግን ይህን ታሪክ ሽሮ አንገት የሚያስደፋ ክፉ አጋጣሚ ሆነ፡፡ ሰርተው የሚያድሩበት፣ እንጀራ የሚያገኙበት ቦታ ሊፈርስ ስለመሆኑ ጭምጭምታ ሰሙ፡፡ ጆሯቸውን አላመኑም፡፡ ጉዳዩ እያስደነገጣቸው፣ ሁኔታውን አጣሩ፡፡ ከጠየቋቸው ሰዎች የጉዳዩን እውነታ አረጋገጡ፡፡ በድንጋጤ ስለራሳቸው አሰቡ፡፡

አሁን እንደቀድሞው ከደንቦች አይሯሯጡም፡፡ ገቢያቸው ብታንስም ህጋዊ ሆነው፣ ግብር እየከፈሉ፣ በአግባቡ እየሰሩ ነው፡፡ ይህን ሲያስቡ ውስጣቸው መለስ አለ፡፡ የሰሙት ዕውን እንደማይሆን ለራሳቸው ነግረው በ‹‹እግዜር ያውቃል›› ልማድ ተጽናኑ፡፡ በእፎይታ አምሽተው አደሩ፡፡

ማግስቱን ስፍራው ሲደርሱ የተባለው እውነት ሆኖ አገኙት፡፡ አሁን የእሳቸውን የጉልት ቦታ ይዞ የሌሎች ገበያ ቦታ እየፈረሰ፣ እየተናደ ነው፡፡ ደነገጡ፣ ጮሁ፡፡ ለምን? ስለምን? ሲሉ ያገኟቸውን ጠየቁ። ሰሚ አላገኙም፡፡ እንደሳቸው የሆኑ ሌሎች ሴቶች ተቀላቀሏቸው፡፡

ሁሉም ኑሯቸውን እያሰቡ፣ ቀጣይ ህይወታቸውን ገመቱ፡፡ የአብዛኞቹ ዕጣ ፈንታ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁሉም ሌላ ገቢ የላቸውም፡፡ ልጆች አሳዳጊ፣ ቤተሰብ አሳዳሪ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ በቤት ኪራይ ይኖራሉ፣ ህይወት ስሜታቸው ቢያመሳሳል በእኩል አነቡ፣ አዘኑ፡፡

**ስ...... «ይድረስ ለቤቱታ....«**

ጊዜ አልፈጁም፡፡ ሰብሰብ ብለው ለሚመለከታቸው ህጋዊ መሆናቸውን እየጠቆሙ ሁሉን ሊያስረዱ ሞከሩ። አቤቱታቸው ሚዛን አልደፋም፣ ውሀ አላነሳም፡፡ በሁሉም ዘንድ ፊት ተነሱ፣ ከስፍራው ተባረሩ፡፡

ይባስ ብሎ በወጉ ከስፍራው ያልተነሱ፣ ለመሸጥ የተዘጋጁ አትክልቶቻቸው በመኪና ሲጫኑ ተመለከቱ። የአብዛኞቹ በሳጥንና በማዳበሪያ የተሞሉ ናቸው፡፡ እነሱን ሊያስጥሉ፣ ሊያተርፉ በተማጽኖ ተለማመጡ፡፡ አዲስ ነገር አልሆነም፡፡ ተገፍትረው ከቦታው ራቁ፡፡

እማዋራዋ ዓለም ሌላ ገቢ የላቸውም፡፡ ልጆቹ ቢያድጉም ህይወትን የሚለወጥ ሥራ ላይ አይደሉም፡፡ ከዓመታት በፊት በሞት ካጧቸው አባወራ የወረሱት አንዳች ጥሪት የለም፡፡ በአንድ ጊዜ ሰማይ በእናታቸው የተደፋ ያህል ጨነቃቸው፡፡ በየወሩ እያሰሉ ከሚከፍሉት የቤት ኪራይ የዘለለ ብዙ አይቆጥቡም፡፡ ይህን ካደረጉ ድፍን አንድ ወር ሞልቷል፡፡ አሁን አከራይዋ ከእሳቸው የወር ገቢያቸውን እየጠበቁ ነው፡፡ ዓለም ይከፍሉት፣ ይቆጥሩት ብር ከእጃቸው የለም፡፡

ዛሬን ሞልተው ነገን በተስፋ በሚያድሩበት፣ ከእጅ ወደአፍ እያደረጉ ጊዜያትን ቆጥረዋል፡፡ በየወቅቱ የሚፈትናቸው የኑሮ ውድነት የየዕለት ሀሳባቸው ነው፡፡ አንዱን ሲሞሉ ሌላው መጉደሉም ብርቃቸው አይደለም፡፡

እሳቸው ቢታመሙ፣ ችግር ቢገጥማቸው ከመሀረብ የሚተርፍ፣ ከዕለት ጉርስ የሚሻገር ተቀማጭን አያውቁም፡፡ ሁሌም ዛሬን ባገኙት ይኖራሉ፡፡ ነገን እንደአመጣጡ ያልፋሉ፡፡ አሁን ግን የገጠማቸው ችግር ከሌላው ዓመት ብሷል፡፡ በዋዛ መፍትሄ የሚሰጡት፣ እንደቀልድ ሰምተው የሚያልፉት አልሆነም። ጨንቋቸዋል፡፡ ሀዘናቸው ከዕንባ በላይ ሆኖ ሲያሳስብ፣ ሲያስተክዛቸው ይውላል፡፡

ዓለም በዚህ ወቅት ብዙ ጉዳይ ያሳስባቸዋል፡፡ የሚሰሩት ከሌለ፣ ገንዘብ አያገኙም፡፡ ገንዘብ ካጡ ቤት ኪራይ መክፈል፣ ኑሮን መቋቋም አይሆንም፡፡ እናም ይላሉ ‹‹ያለኝ ምርጫ ጎዳና ላይ መውጣት፣ ከመንገድ መውደቅ ነው››

ወይዘሮዋ ይህን ቢሉም ሀሳቡ ቀላል እንዳልሆነ ያውቃሉ፡፡ ጎዳና ለእሳቸውም ሆነ ለደረሰች ልጃቸው ፈጽሞ አይበጅም፡፡ ይህ ህይወት እንደ ቤት ኪራይ ፈልገው የሚገቡበት፣ መርጠው የሚኖሩበት ዕድል አይሰጥም፡፡ አሁን ለጊዜው በአስኮ አዲስ ሰፈር አንድ ጥግ ከደንቦች እየተሯሯጡ ያቅማቸውን መሸጥ ይዘዋል፡፡

ይህ አይነቱ ያልተመቸ ውሎ በእሳቸው ዕድሜ ፈጽሞ አይመችም፡፡ ከእጃቸው ያለውን ጥቂት የጉልት ሸቀጥ ሸጦ ለመግባት በየቀኑ አይሆኑት የለም። እሳቸው እንዲህ ባይሆን ይወዱ ነበር፡፡ ሆኖም ምርጫ የላቸውም፡፡ ከክረምቱ ተጋፍተው፣ ከደንቦቹ ተፋጠው ለዕለት ጉርስ ለመያዝ ሽሚያ ጀምረዋል፣ ቀናትን ቆጥረዋል፡፡

ወይዘሮዋ ያሉበት የህይወት ትግል ከዓመታት በፊት ያሳለፉትን ችግር ያስታውሳቸዋል፡፡ ያለፈው ታሪክ ‹‹ ይገፃዋለሁ›› ባሉት ህጋዊነት የተፈታ ቢመስላቸው ችግራቸውን ችለው፣ ነገን ተስፋ አድርገው መኖር ችለው ነበር፡፡ ዛሬ ግን ነገን ስለሚያሻግራቸው ጭላንጭል ተስፋ እርግጠኛ አልሆኑም፡፡

አሁን አዲስ ዓመት ተቃርቧል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም እንደ ቤት እንደ አቅሙ ለመሆን ጓዳውን ያያል፡፡ በዛም አነሰም በዓውደ ዓመት ‹‹አንዳች የለም ›› ተብሎ ቤት አይዘጋም፣ እሳቸው ግን ስለቤትና ኑሮ ስጋት ገብቷቸዋል። ያልሞላው ውሎ የኪራይ ገንዘብ አጉድሎባቸዋል፡፡ ዛሬ ነገ ሲሉ ያቆዩት ክፍያ ቀን እየቆጠረ፣ ጊዜ እየጨመረ ነው።

ዓለም ምን ቢቸግራቸው ለዓውደ ዓመት ቤታቸው ጎድሎ አያውቅም፡፡ የአቅማቸውን አድርገው፣ ያላቸውን ንፁህ ለብሰው በደስታ ያሳልፉታል፡፡ በግ፣ ቅርጫው ቢቀር ለቡና፣ ዳቦው አያጡም፡፡ ለወዳጅ ዘመድ ቀናት የሚጋብዝ ድግስ ባይኖርም ከዶሮው፣ ከጠላው ማለታቸው አይቀርም፡፡

እንዲህ ባደረጉ ቁጥር ጎዶሏቸው ሞልቶ፣ ጨለማቸው በርቶ ይታያቸዋል፡፡ ቤታቸው የኪራይ ቢሆንም በምስጋና ማደር ልምዳቸው ነው፡፡ አቻ ጎረቤቶች ጠርተው፣ ካላቸው አቃምሰው ‹‹እንኳን አደረሰን፣ አደረሳችሁ›› ማለትን ያውቁበታል፡፡ ይህ አይነቱ አጋጣሚ እስከዛሬ ራሳቸውን የሚችል አንገት እንዳላቸው ሲነግራቸው ኖሯል፡፡

አሁን ሴት ልጃቸው አድጋለች፡፡ ዕድሜዋ ሲጨምርና ኑሮ ሲከፋ ከሰው ቤት ተመላላሽ መስራት ጀምራለች። እንዲያም ሆኖ ህይወት አንዳች ለውጥ አላመጣም፡፡ መቼም ቢሆን፡፡ የልጆቻቸው ከፍ ማለት ለእናትዬው ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ ሁሌም እነሱን የሚያስቡት ልክ እንደ ልጅነታቸው ልጆች መሆናቸውን ብቻ ነው፡፡

ወይዘሮ ዓለም ሰርቶ ለማደር፣ አግኝቶ ለመኖር ዛሬም ጉልበታቸው ብርቱና ዝግጁ ነው፡፡ በየቀኑ የት ልሂድ? እንዴት ልኑር ? ይሉት ሀሳብ ግን በየአፍታው ያስጨንቃቸዋል፡፡ እናም ‹‹ዕድል ይሰጠን፣ ሰርተን እንብላ›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ ዛሬም የህጋዊነታቸው መፍረስና የእነሱን ተበትኖ መቅረት ህሊናቸው አልተቀበለም፡፡ አንድ ቀን የሚሰበስባቸው አካል፣ ‹‹አይዟችሁ›› የሚል መልካም ልቦናን ይጠብቃሉ፡፡ ተስፋቸው ለምልሞ ኑሯቸው እንደሚቀናም ያስባሉ። ነገን በጭላንጭል የሚያዩት ጉልት ቸርቻሪዋ ዓለም ድረሴ፡፡

# ቁጭት የወለደው ስኬት-ከሳውዲ እስከ ባቢሌ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

«ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው» የሚባለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ ከራሳቸው አልፈውም ቤተሰባቸውን፣ የአካባቢያቸውን ማህበረሰብና የሀገሪቱን ዜጎች ህይወት የመቀየር ትልቅ አቅም ስለአላቸው ነው፡፡ እርግጥ ነው ሴቶች ከተማሩ ቱሩፋቱ ብዙ ነው፡፡ የመማሩን ዕድል ካገኙ ከወንዶች ባልተናነሰ መልኩ በሚሰማሩባቸው የሥራ ዘርፎች ሁሉ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ መሥራት የሚችሉበት ዕድል ከተዘጋ ይህ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸው ይቀጭጫል፡፡

የሴቶችን በተለያዩ መስኮች ተሳታፊነት ማሳደግ የግድ እንደሆነ አብዝቶ የሚነገረውም በዚህ ሁሉ ምክንያት ነው፡፡ በአፍሪካ ያለውን እውነታ ብቻ ብንመለከት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት ሴቶች አዳዲስ በተባሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ተሳታፊ እንደሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ይህንኑ ይጠቁማል፡፡

ሴቶችን ወደፊት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት በተለይም በአፍሪካ በርካታ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሴቶች ምሳሌ ሆነው ታይተዋል፡፡ በኢትዮጵያም እንዲሁ ከተለመደው ውጭ ሴቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተሰማሩ ብቻ ሳይሆኑ፣ በተሰማሩባቸው መስኮች ትርጉም ያለው ሥራ ሲሰሩ ይስተዋላል፡፡

ኢትዮጵያዊ ሴት መሆን አያሌ መሰናክሎችን መጋፈጥ ቢሆንም፣ ይህን ፈተና ተቋቁመው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በመሰማራት ትርጉም ያለው ሥራ የሠሩ፤ እየሠሩ ያሉ በርካቶች ናቸው፡፡ የዕለቱ የስኬት እንግዳችንም በርካታ ሥራ ከሠሩና ምሳሌ መሆን ከቻሉ ኢትዮጵያዊ ሴቶች ተርታ ትመደባለች፡፡

እንግዳችን በአረብ አገር ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ቆይታለች፡፡ በቆይታዋ የአገሯ ስም ከረሃብተኝነት ጋር ተያይዞ ሲነሳ ትሰማለች፡፡ ይህን አምኖ ለመቀበል በብዙ ተቸግራለች፡፡ የአርብቶ አደር ልጅ የሆነችው ይህች ኢትዮጵያዊት፣ ሌላው ቢቀር ወተትና ቅቤ እንዲሁም ማር በልታና ጠጥታ ማደጓን ታውቃለችና ኢትዮጵያ በረሃብተኝነት መፈረጇ ቁጭት አሳደረባት፡፡

ቁጭቷን ለመወጣትም ጥርሷን ነክሳ ጥሪት ቋጥራ ወደ አገሯ መመለስ እንዳለባት በማመን የአረብ አገር ቆይታዋ ትርጉም ያለው እንዲሆን የበለጠ መውተርተር ውስጥ ገባች፡፡ የአረብ ሀገር ቆይታዋን ገታ አድርጋ ወደ እናት አገሯ ትመለሳለች፡፡

በአሁኑ ወቅት በትውልድ አካባቢዋ ባቢሌ ወረዳ በግብርናው ዘርፍ ተሰማርታ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማልማት ሥራ ላይ ተሰማርታለች፡፡ በዚህም ከቤተሰቦቿም ባለፈ የአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ባህልን ይበልጥ እንዲገነዘብ በግብርና ስራዋ አስተምራለች፡፡

ባቢሌ ወረዳ ተወልዳ፤ ድሬዳዋና ሀረር ያደገችው የዛሬ እንግዳችን ወይዘሮ ፈትያ ሙሐመድ ትባላለች። ወይዘሮ ፈትያ፤ ቤተሰቦቿ ከከብቶቻቸው ጋር ከቦታ ቦታ ኑሯቸውን ይመሩ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ የአርሶና አርብቶ አደር ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንም፣ ወይዘሮ ፈትያ ወተት፣ ቅቤና ማር ያጣችበትን የልጅነት ጊዜ አታስታውስም፡፡ ለዚህም ከአያቶቿ ጋር ማደጓ ሳይጠቅማት እንዳልቀረ ትናገራለች።

ወይዘሮ ፈትያ፤ ገና የአሥራ ሦስት ዓመት ታዳጊ እያለች ነው ወደ አረብ አገር የሄደችው፡፡ በአብዛኛው ሴት እህቶቻችን ወደ አረብ አገር በሚሄዱበት አግባብ በቤት ሠራተኝነት ሳይሆን በትዳር ነበር የሄደችው። በአሥራ ሦስት ዓመቷ በአካባቢው ባህልና ወግ መሰረት ባል ይመጣላታል፡፡ ቤተሰብ ያመጣውን ባል ልጅ መቀበል የግዱ ነውና በወቅቱ ማን ይሁን ማን ለማታውቀው የሳውዲ ዜግነት ላለው አረብ ተድራ ነው ወደ አረብ አገር ያቀናችው፡፡

ማስተዋል በማትችልበት በልጅነት ዕድሜዋ ትዳር ይዛ ወደ አረብ አገር የተጓዘችው ወይዘሮ ፈትያ፤ በአረብ አገር ቆይታዋ ከህይወት ብዙ ትምህርት መቅሰም ችላለች። ይህም ስለ አገሯ ሁኔታ የበለጠ ማወቅና መረዳት አስቻላት፡፡ ሀገሯ ረሃብተኛ መባሏን በወቅቱ ልጅ በመሆኗ አልተረዳችውም ነበር፡፡ እንዲያውም «ረሃብተኛ ማለት ምን ማለት ነው፤ ወተት ጠጥተን በቅቤና በማር አድገን ለምን ረሃብተኛ ተባልን» የሚል ጥያቄም በልጅነት አዕምሮዋ ተፈጥሮባት እንደነበር ታስታውሳለች፤ ይህም አብዝቶ ይቆጫት፣ ያንገበግባት ጀመር፡፡



ወይዘሮ ፈትያ ሙሐመድ

ፎቶ እዮብ ተፈራ

ወይዘሮ ፈትያ፤ እያደገች፣ እየበሰለች እና እያስተዋለች ስትመጣ አገሯ ኢትዮጵያን ከሌሎች አገራት ጋር በማነጻጸር አገሬ ምን አጣች፤ ምንስ ጎደላት የሚሉ ጥያቄዎችን እያነሳች ቀስ በቀስ በራሷ መመለስ ጀመረች፡፡ ገና በለጋነት ዕድሜዋ በቤተሰብ የመጣላትን ትዳር አሜን ብላ በመቀበል ወደ ሳውዲ ማቅናቷም ለበጎ እንደሆነ በማመን ቁጭቷን የምትወጣበትን መንገድ በማሰላሰል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጀመረች፡፡

«አብዛኛው የሙስሊም እምነት ተከታይ ቤተሰብ ለሴት ልጁ ትዳር በማምጣት ይታወቃል» የምትለው ወይዘሮ ፈትያ፤ በወቅቱ በአካባቢው ከነበሩ ታዳጊ ሴቶች እርሷ በቁንጅናዋ ሳቢያ ተመርጣ እንደተዳረች ታስታውሳለች፡፡ አረብ አገር አማቾቿን በተቀላቀለች ጊዜም አማቾቿ ቁንጅናዋን አድንቀው ሲያበቁ፤ «ይችን ቆንጆ ከየት ነው ያመጣት፤ ከየት አገኛት» የሚል ጥያቄያቸውን ያነሱ ነበር፡፡ የጥያቄያቸው መልስ ደግሞ «አረብ አይደለችም ሀበሻ ናት» የሚል ብቻ አልነበረም «ከዛ ከረሃብተኛ አገር ከኢትዮጵያ ነው የመጣችው» የሚል ቅጥያም ነበረው፡፡ ይሄኔ በቁንጅናዋ መደነቋ ያስደሰታት ወይዘሮ ፈትያ፤ «ከኢትዮጵያ ከረሃብተኛ አገር መጣች»መባሏ ግን በእጅጉ ይቆጫት እንደነበርና ዛሬም ድረስ ስታስበው እንደሚሰማት አጫውታናለች።

በወቅቱ መልስ መስጠት ባትችልም ያደገችበትን ወተትና ቅቤ እያስታወሰች «ግን ለምን፤ ይህን ያህል ረሃብተኛ ነን እንዴ?» በማለት እራሷን ትጠይቃለች። ይሁንና በቆይታዋ ሀገሯን ከእነሱ አገር ስታነጻጽር አገራቸው አሸዋ እንደሆነና አፈር እንኳን የሌላቸው መሆኑን ትረዳለች፤ ለከተማቸው ማስዋቢያ ከሌሎች አገራት አፈር ገዝተው እንደሚያመጡም ታውቃለች። ሶስትና አራት ሺ ሜትር ርቀት ያለው ጉድጓድ ቆፍረው የፈላ ውሃ እንደሚያወጡ፣ እሱኑ በታንከር አጠራቅመውና አቀዝቅዘው እንደሚጠቀሙ፡፡ ያስተዋለችው ወይዘሮ ፈትያ፤ የኢትዮጵያ ረሃብተኝነት አልታይሽ አላት፡፡

በዚህ ወቅት ታዲያ «እኔኮ አገሬ ዝናቡ የማያቋርጥበት፣ አረንጓዴ ለምለም የበዛበት፣ ምቹ አየር ያለበት፣ መሬቱ ጫር ጫር ቢደረግ ሁሉን የሚያበቅልበት፣ ለምለም አገር ናት » በማለት ኢትዮጵያ አገሯን አስባ ታዲያ ለምን ረሃብተኛ ተባልን ስትል ራሷን ሞገተች፡፡ ችግር ነው ያለችውን አንድ ሁለት ብላ መለየት ጀመረች። በወቅቱም በእሷ አቅም ለይታ ላስቀመጠችው ችግር የምትችለውን ለማድረግና መፍትሔ ለመሆን ስትዘጋጅ በአረብ አገር የሚኖራትን ቆይታ ማራዘም አንዱ መንገድ ሆኖ ታያት፡፡

ወይዘሮ ፈትያ፤ አረብ አገር በነበራት ቆይታ ብልጭልጭ ነገር ሳያታልላት ገንዘብ ማጠራቀም እንደጀመረች ትናገራለች፡፡ ከትዳር አጋሯ እንዲሁም ከዘመዶቹ የምታገኘውን ገንዘብ በሙሉ በመጠኑ ተጠቅማ ቀሪውን ማጠራቀም ጀመረች፡፡ በአብዛኛው ለወርቅ፣ ለአልባሳት፣ ለቤት ዕቃ መቀየሪያ፣ ለልጆች አልባሳትና መዝናኛ ጭምር የሚሰጣትን ገንዘብ በመጠኑ በመጠቀም ብዙ ነገር ሳያምራት፤ ብዙ ገንዘብ ማጠራቀም ቻለች፡፡

ከአገር አገር ተጓጉዞ መዝናናት በአረቦቹ የተለመደ ቢሆንም ወይዘሮ ፈትያ፤ ግን ጉዞውን ቀነስ በማድረግ ገንዘቧን ማጠራቀም ቀጠለች፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን ከቤተሰቧ ጋር ለጉብኝት ሱዳን ባቀናችበት ወቅት ሱዳኖቹ ከ30 እስከ 40 ሜትር ከሚደርስ ጉድጓድ ውስጥ ውሃ ሲያወጡ ተመለከተች፡፡ ውሃ ማውጣት ብቻም አይደለም፤ የወጣውን ውሃ የውሃ መሳቢያ ሞተር ገጥመው ወደ እርሻቸው ሲለቁ አስተዋለች፡፡ በዚህ ወቅት በአገሯ በየሰው ደጅ አቋርጦ የሚሄደውን ወራጅ ውሃ እንዲሁም ወንዞችን አስታወሰች፡፡

«ሱዳኖቹ እንዳደረጉት ሁሉ የአገሬ ህዝብም ወንዞቹንና ወራጅ ውሃውን ቢጠቀም የት ይደርስ ይሆን?» ስትል እራሷን ጠየቀች፡፡ ቀጠል አድርጋም «እንዲህ መሥራት ከቻልን ከድህነት መውጣት እንችላለን» የሚል መልስ ለጥያቄዋ ሰጠች፡፡ ስለዚህ አለች ወይዘሮ ፈትያ፤ «ስለዚህ ይህን ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ መውሰድ አለብኝ» በማለት ለራሷ ቃል ገባች፡፡ ቃሏን ወደ ተግባር ለመለወጥ ጊዜ አላጠፋችም፤ ከመቅጽበት ወደ አገሯ ኤምባሲ በማቅናት አገሯ ላይ የግብርና ሥራ መሥራት እንደምትፈልግና ቴክኖሎጂውንም ወደ አገሯ የማስገባት ፍላጎት እንዳላት አስረዳች፡፡ ኤምባሲውም ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መራት፡፡

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የት ቦታ ላይ መሥራት እንደምትፈልግ በጠየቃት ጊዜም በኦሮሚያ ክልል ባቢሌ ወረዳ ላይ መሥራት ፍላጎቷ እንደሆነ ትገልጻለች። ባቢሌ ጠረፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሽፍታ ያለበት አካባቢ እንደሆነና ሴት ሆና እንደማትችል ይነገራታል፡፡ ይሁንና ወይዘሮ ፈትያ፤ ባቢሌ የትውልድ ቦታዋ እንደሆነና አካባቢውን እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ ጠንቅቃ የምታውቅ በመሆኑ ባቢሌ ካልሆነ አሻፈረኝ ትላለች፡፡ «የአገሬንና የአካባቢዬን ሰዎች በተለይም ሴቶችን የማስተምራቸው ነገር አለኝና በዚሁ አካባቢ መሬት ይሰጠኝ» ብላ የሙጥኝ በማለቷ ሃምሳ ስድስት ሄክታር መሬት ተሰጥቷታል፡፡

የእርሻ መሬቱን ባገኘችበት ቅጽበት ጊዜ ሳታጠፋ ወደ ሱዳን በማቅናት ውሃ ከጉድጓድ አውጥተው በሞተር ወደ እርሻቸው ሲለቁ የተመለከተቻቸውን ባለሙያዎች ከነቴክኖሎጂያቸው በዶላር ቀጥራ ወደ ኢትዮጵያ ባቢሌ አመጣቻቸው፡፡ በእርሻ ቦታዋ መኖሪያ ቤት ሰርታላቸው ቆይታቸውን እዛው አድርገው አሥር የውሃ ጉድጓዶች እንዲያወጡላት አድርጋለች። ሱዳኖቹ ውሃውን በሚያወጡበት ጊዜ የአካባቢውን ወጣት አሰባስባ እየከፈለች ውሃ አወጣጡን እንዲማሩና ቴክኖሎጂውን እንዲያስቀሩ በማድረግ ትልቅ ሚና ነበራት፡፡

ከጉድጓዱ የወጣው ውሃም ሞተር ተገጥሞለት እስከ አንድ ሺ ሜትር ድረስ ተለቅቆ የእርሻ ቦታን ሲያጠጣ የተመለከተው የአካባቢው ማህበረሰብ ቴክኖሎጂውን እየተጠቀመ የግብርና ሥራውን በትጋት ማቀላጠፍ ችሏል፡፡ እርሷ ወደዚህ ሥራ ከመግባቷ አስቀድሞ ማንም የአካባቢው ሰው የግብርና ሥራን እንደማይሠራ ያስታወሰችው ወይዘሮ ፈትያ፤ በአሁኑ ወቅት ግን አካባቢው ላይ የእርሻ ሥራ በስፋት ተለምዶ ወጣቱ፣ አዛውንቱና ሴቱ የግብርና ሥራን በየጓሮው እያቀላጠፈው መሆኑን አጫውታናለች፡፡

«ባቢሌ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ በስፋት የሚታወቀው በአርብቶ አደርነት ቢሆንም ለምግብነት የሚሆን ማሽላን በመጠኑ ያመርታል፡፡ ያም ቢሆን ግን አጥጋቢ ምርት አያገኝም» የምትለው ወይዘሮ ፈትያ፤ ከሚያገኙት የማሽላ ምርት ይልቅ አገዳውን ለከብቶቻቸው ይመግቡ እንደነበረ ታስታውሳለች፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአርብቶ አደርነት ይታወቅ የነበረውን አካባቢ ማህበረሰቡ ወደ ግብርና ሥራ እንዲገባ ፈርቀዳጅ በመሆን ትልቅ አበርክቶ አድርጋለች፡፡ በዚህም ፍጹም ደስተኛ እንደሆነችና ኢትዮጵያውያን ጠንክረን ከሠራን ከድህነት መውጣት እንደምንችል ትናገራለች፡፡

ወይዘሮ ፈትያ፤ ለሃያ ስምንት ዓመታት በሳውዲ በነበራት ቆይታ ገንዘብ አጠራቅማ ዛሬ ከራሷ አልፋ የአካባቢውን ማህበረሰብ መቀየር የሚያስችላትን የግብርና ሥራ ብትሠራም «ከረሃብተኛ አገር ከኢትዮጵያ ነው የመጣችው» የመባሏ ነገር ግን ዛሬም ድረስ ይቆጫታል፡፡ ያም ቢሆን ታዲያ ቁጭቷን በሥራ ለመወጣት እየታተረች ሲሆን፤ የዛሬ 16 ዓመት ወደ አገሯ መጥታ የጀመረችው የግብርና ሥራም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ነው ያጫወተችን፡፡

ወይዘሮ ፈትያ በሃምሳ ስድስት ሄክታር መሬት ላይ አትክልትና ፍራፍሬ አምርታ ለገበያ የምታቀርብ ሲሆን፤ ከፍራፍሬ ምርት በዋናነት አፕል ማንጎ፣ ቫላንሺያ የተባለው አንደኛ ደረጃ ብርቱካን፣ ፓፓዬና ዘይቱን ታመርታለች፡፡ ከአትክልትም እንዲሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተለመደ ባሚያ ወይም የሰውነት ግራሶ የተባለውን ምርት ጨምሮ ቲማቲምና ሽንኩርት በስፋት አምርታ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ ታቀርባለች፡፡

አምርታ ከመሸጥ ባለፈ የአካባቢው ማህበረሰብ ቴክኖሎጂውን ተጠቅሞ ውሃ ከጉድጓድ በሞተር በማውጣት በየጓሮው አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት እንዲችልና ከብቶቹንም ውሃ ማጠጣት የሚችሉበትን ዕድል በመፍጠር ማህበራዊ ኃላፊነቷን መወጣት የቻለች ታታሪ ናት፡፡

የሥራ ዕድልን አስመልክቶ በቋሚነት 70 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለች ሲሆን፤ በጊዜያዊነት ደግሞ 150 የሚደርሱ ዜጎች በልተው ለማደራቸው ምክንያት ሆናለች፡፡ በቁጥር ከተቀመጠው የሥራ ዕድል በላይ በአካባቢው ለሚገኙ ሰዎች የግብርና ሥራን ማስተማር የቻለቸው ወይዘሮ ፈትያ፤ ከግብርናው ባሻገር ሴቶች ምርቱን ተረክበው ወደ ገበያ እንዲያወጡ በማድረግ በርካታ ሴቶችን ወደ ንግድ ማስገባት ችላለች።

ከግብርና ሥራ በተጨማሪ ምርትን ወደ ገበያ አውጥቶ በመሸጥ መጠቀም እንደሚቻል ለባቢሌ ወረዳ ያስተማረችው ወይዘሮ ፈትያ፤ በቀጣይም ግብርናውን አጠናክራ በመቀጠል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ምርቶቿን እሴት ጨምራ በፋብሪካ የማቀነባበር ዕቅድ አላት፡፡ እኛም ዕቅዷ እንዲሳካ እየተመኘን የነበረንን ቆይታ አበቃን፡፡

# ስፖርት





# ጀግኖቹ በፓሪስ ኦሊምፒክ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ቃል ገብተዋል

**ዓለማየሁ ግዛው**

በ19ኛው የቡዳፔስቱ ዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳትፎ ከዓለም ስድስተኛ፣ ከአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቅ የቻለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን ከትናንት በስቲያ በፌዴሬሽኑ ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡ ሀገሩ ሲገባ ደማቅ አቀባበል እንደተደረገለት ይታወሳል፡፡

በቡዳፔስት ሞቃታማ አየር ንብረት እንዲሁም በአትሌቶች ቅንጅት ማነስ የታጡ ሜዳሊያዎች ብዙዎችን አስቆጭተዋል። የፌዴሬሽኑ አመራሮች፣ አሰልጣኞችና አትሌቶችም ይህን ቁጭት በሽልማት ስነስርዓቱ ወቅት አንፀባርቀዋል፡፡ በዚህም በቀጣዩ 2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ የታዩ ድክመቶችን አርሞ የስፖርት ቤተሰቡ የሚጠብቀውን ውጤት ለማስመዝገብና ለመካስ ከወዲሁ ቃል ገብተዋል፡፡

በዓለም ቻምፒዮና ያጋጠሙትን ችግሮች በመቅረፍ በፓሪስ ኦሊምፒክ ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብና ቃልን በተግባር ለመለወጥ እንደሚሰሩም አሰልጣኞችና አትሌቶች ተናግረዋል፡፡

በማራቶን ኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳለያ እንድታስመዘግብ የቡድን ስራውን በፊት አውራሪነት የመራችው አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው በመጨረሻዎቹ ኪሎ ሜትሮች በመድከማ የነሐስ ሜዳሊያ ለጥቂት አምልጧታል፡፡ ይህች ኮከብ አትሌት በውድድሩ ላበረከተችው አስተዋፅኦ ልዩ ተሸላሚ ሆናለች።ያለምዘርፍ በሽልማት ስነስርዓቱ ላይ ባደረገችው ንግግር ውድድሩ በጣም ጥሩ እንደነበር ገልፃለች፡፡ «ከፊት እየመራን ስለነበር አረንጓዴውን ጎርፍ ለመድገም አስበን ነበር። ግን አልሆነም ሀገሬ ወርቅ በማግኘቷ ደስተኛ ነኝ» ያለችው ያለምዘርፍ በውድድሩ የገጠማት ፈተና ለሀገሯ ባይሆን ላትጨርሰው እንደምትችል ተናግራለች፡፡ በውድድሩ ወቅት የነበረውን ከባድ ሙቀት ልትቋቋመው ካለመቻሏ የተነሳም አምስተኛ ሆና ማጠናቀቀን እንኳን ሀኪሞች ነበሩ የነገሯት።



**በቡዳፔስት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የተሳተፈው ቡድን በፌዴሬሽኑ ሽልማት ተበርክቶለታል ፣**

ያም ሆኖ ብርቱዋ አትሌት የኢትዮጵያ ህዝብን ለመካስ ለፓሪስ ኦሊምፒክ ጠንክራ እንደምትሰራም ጠቁማለች፡፡

ኢትዮጵያ ካገኘቻቸው ሁለት ወርቆች አንዱን በእልህ አስጨራሹ የ10ሺ ሜትር ፍልሚያ ማስመዝገብ የቻለችው አትሌት ጉዳፍ ጸጋዬ በበኩሏ፣ በ5ሺ ሜትር በደረሰባት ጉዳት ውጤታማ መሆን ባትችልም በ10ሺ ሜትር ባስመዘገበችው ድል ደስተኛ እንደሆነች ጠቅሳለች፡፡ በመሆኑም ወርቅም ሆነ ብር ቢመዘገብ ለሀገር በመሆኑ በፓሪስ ኦሊምፒክ የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንደምትዘጋጅ አስረድታለች፡፡ ለውጤቱ መመዝገብምም አሰልጣኞቿን አመስግናለች፡፡

በማራቶኑ ውጤት እንዲመዘገብ ከፍተኛ ሚናን ከተጫወቱት አሰልጣኞች አንዱ ገመዶ ደደፎ፣ ለቀድሞ አትሌቶችና አሰልጣኞች ያለውን ክብርና ምስጋና በመግለፅ «በትንሽ ስህተት አሸንፈናልም ተሸንፈናልም» በማለት በሴቶች የተመዘገበውን ትልቅ ድልና በወንዶች ለጥቂት ከእጅ ስለወጣው የብር ሜዳሊያ ተናግሯል፡፡ ውጤቱ የመጣውም በአትሌቶች ከፍተኛ መሰዋዕትነት እንደሆነ ገልጧል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንትና የቡድኑ መሪ አትሌት ገዛኸኝ አበራ እንደተናገረው፣ ቡድኑ ከወር በላይ ተሰባስቦ ዝግጅት አድርጓል። በመሆኑም አትሌቶቹ ወደ ውድድሩ ስፍራ እስከ ሚጓዙበት ጤንነታቸውና አቋማቸው ጥሩ የሚባል ነበረ። በውድድሩ ቦታ ያለው ከፍተኛ ሙቀት ግን ኢትዮጵያ በምትታወቅበት የ5 እና 10ሺ ሜትር ርቀት ውጤት ማምጣት እንዳትችል አድርጓል። በዚህም በቀጣይ ቴክኒካል የሆኑትን ጉዳዮች በማስተካከል ለኢትዮጵያ ውጤት ለማምጣት የእርምት ርምጃ ይወሰዳል። በፓሪስ ኦሊምፒክ ሜዳሊያ ባልተመዘገበባቸው ርቀቶች ከወዲሁ ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግና የተስተዋሉ ችግሮችን በማስተካከል ህዝቡን ለመካስ እንደሚሰሩም አረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ፣ ቡድኑ ያደረገውን ተሳትፎና አጠቃላይ ቆይታ አስመልክታ ባደረገችው ንግግር በቡዳፔስቱ የተስተዋለውን እና በፓሪስ ኦሊምፒክ መደረግ ስለሚኖርበት ጉዳይ አጽንዖት ሰጥታለች፡፡ በውድድሩ ስፍራ በነበረው የአየር ጸባይና በአትሌቶች ቅንጅት ማነስ የተፈለገው ውጤት ባይመዘገብም በፓሪስ ኦሊምፒክ ውጤት እንዲመጣ አስፈላጊው ድጋፍ እና ዝግጅት እንደሚደረግ ቃል ገብታለች። ለዚህም ተገቢውን ዝግጅት ለማድረግና ለመደገፍ ጥረት እንደምታደርግ ተናግራለች፡፡

ቡድኑ በቡዳፔስት ላስመዘገበው ውጤት ማበረታቻና ለፓሪስ ኦሊምፒክ ማነቃቂያ እንዲሆን ወርቅ፣ ብርና የነሐስ ሜዳለያን ላስመዘገቡት አትሌቶችና አሰልጣኞች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ ወርቅ፣ ብር እና የነሃስ ሜዳሊያን ላስመዘገቡ አትሌቶች የ60፣ 40ና 30 ሺ ብር ሽልማት ተበርክቷል፡፡ አትሌት ያለምዘርፍ የኋላውና ጸሃይ ገመቹ በልዩ ተሸላሚነት የ50ሺ ብር ሽልማት ተበርክቷል፡፡ በተጨማሪም ለአሰልጣኞችና ለውጤቱ መመዝገብ ሚና ለተጫወቱ አካላትም ሽልማትና እውቅና ተሰቷል